## አራተኛ ቀን

ሙላቱ ጥልቅ የእግዚአብሔር ፍቅር አለው:: የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ዋና መሪ እንዲሆን ሲመረጥ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱን በትሕትናና በእውነተኛነት ለመምራት የሚችለውን ጥረት ሁሉ አድርጓል:: ለተወሰነ ጊዜ ነገሮች በጥሩ ሁኔታ ይከናወኑ ነበር:: አንድ ቀን ግን ለአንድ ወንጌላዊ የደመወዝ ጭማሪ መደረግ አለበት ወይስ የለበትም? በሚለው አሳብ ላይ እርሱና አንድ ሌላ መሪ ሊስማሙ አልቻሉም:: ይህንን አለመስማማት በፍጥነት ሊፈቱት ባለመቻላቸው፣ የጥላቻ ስሜቶች ከዕለት ዕለት እየጨመሩ ሄዱ:: ሌላኛው መሪ ሙላቱ ለወዳጆቹና ለጎሳው አባላት የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን በመስጠት ላይ ነው የሚል ወሬ ያነዛ ጀመር - ምንም እንኳ ነገሩ ውሸት ቢሆንም:: ሙላቱ ያ መሪ ሐሜት እየነዛበት መሆኑን ሲሰማ፣ የበለጠ አዘነ:: ለወዳጆቹም የደረሰበትን ችግር ተናገረ:: ወዲያውም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ሰዎች በአሳብ ተከፋፍለው ተገኙ::

> 29ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል በትንሽ ጉዳይ የተጀመረ ክፍፍል ከትልቅ ደረጃ ላይ ሲደርስ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) ትንሹ ችግር አድጎ እንዴት ብዙ ሰዎችን እንደ ነካካ ግለጽ::

ምንም እንኳን ሁሉም ክርስቲያኖች በስምምነትና በአንድነት ለመኖር ቢፈልጉም፣ በክርስቲያኖች መካከል የመጎዳት ስሜትና ክፍፍል መፈጠራቸው አልቀረም:: ይህ በተለይ በመሪዎች መካከል አዘውትሮ የሚከሰት ችግር ነው:: መሪዎች የተለያዩ ዓይነት ሁኔታዎች ስለሚያጋጥሟቸው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በመንፈሳዊ መንገድ ለመምራት ይችሉ ዘንድ እነዚህን ችግሮች እንዴት መፍታት እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው::

1. ብዙውን ጊዜ ሰዎች በመሪዎች ላይ ያማርራሉ:: ሙሴ እስራኤላውያንን በሚመራበት ጊዜ፣ ችግር በገጠማቸው ጊዜ ሁሉ ሙሴን ይወቅሱት ነበር (ለምሳሌ፣ ዘጸአ. 17:1-7):: ዛሬም ሰዎች ችግር በገጠማቸው ጊዜ፣ ስለ መሪዎቻቸው ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን ይናገራሉ:: ብዙ ሰዎች ለገጠማቸው ችግር ሁሉ መሪዎች መፍትሔ ሊኖራቸው ይገባል የሚል የተሳሳተ አመለካከት



አላቸው:: ችግራቸው ወዲያውኑ በማይፈታበት ጊዜ፣ በመሪዎቻቸው ላይ ማማረር ይጀምራሉ:: ወይም ደግሞ የተላለፈውን ውሳኔ የማይደግፉ ከሆነ፣ መሪዎች ይህንን ውሳኔ የሰጡት እንደ ጎሰኝነት ባሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች ተነሣሥተው ነው ብለው ያስባሉ:: በአብዛኛው ሰዎች ስለ ችግሩ የሚናገሩት ለመሪው ለራሱ አይደለም:: ከዚህ ይልቅ፣ ውስጥ ለውስጥ ስለ ጉዳዩ እያወሩ ሐሜት ያስፋፋሉ:: ይህ በተለይ በመሪዎችና በሕዝቡ መካከል ከፍተኛ መተማመን በማይኖርበት ጊዜ የሚፈጠር ችግር ነው:: መሪዎች ሐሜቱን በሚሰሙበት ጊዜ ያዝናሉ:: መሪዎቹ ይህንን ጉዳይ እንዴት እንደሚቋቋሙ ካላወቁና ይቅር ማለት ካልቻሉ፣ ሕይወታቸው መራራ ይሆንና ለእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሰጡት የመሪነት አገልግሎት ውጤታማ ሳይሆን ይቀራል::

2. የመሪዎች አለመስማማት አዲስ ነገር አይደለም:: ብዙ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ላይ ሰዎች የተለያዩ አቋሞችን ይይዛሉ:: በመሪዎች መካከል መተማመን በማይርበት ጊዜ፣ መሪዎች አሳባችን ተቀባይነት አላገኘም ብለው ይከፋሉ:: አንድ ሰው በሳል ያልሆነን ሰው አሳብ በማይቀበልበት ጊዜ፣ በግል ጥቃት እንደ ተሰነዘረባቸው ቆጥረው ያዝናሉ:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአሳብ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ካላወቁ፣ የስሜት መጎዳቱ በፍጥነት አድጎ ለክፍፍልና መራርነት መንገድ ይጠርጋል:: መሪዎች ሳይስማሙ ቀርተው ጸብ በሚፈጥሩበት ጊዜ፣ ይህ ችግር በፍጥነት ወደ ምእመናኑ ይተሳለፋል:: ይህም የሚሆነው ሰዎች መሳሳቱን ሳይቀር እያወቁ ዘመዳቸውን ወይም ጓደኛቸውን በመደገፍ ወገናዊነትን ስለሚያሳዩ ነው::

3. ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ቡድኖች የሚፈልጉት ነገር ባለመሳካቱ ያዝኑና በአመራር ላይ ባሉት ሰዎች ላይ ንዴታቸውን ለመግለጽ ይፈልጋሉ:: ይህንን ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 6:1 ውስጥ ልንመለከት እንችላለን:: በዚህ ክፍል ከይሁዳ ውጭ የተወለዱ አይሁዶች ለመበለቶቻቸው ተገቢው ድጋፍ እንዳልተሰጣቸው አሰበው ነበር:: የሰዎቹ ቁጣ የተሰነዘረው

በሐዋርያቱ ላይ ይመስላል:: ዛሬ የአንድ ጎሳ አባል የሆኑ ሰዎች የሌሎችን ያህል ተቀባይነት አለን ወይም እንስተናገዳለን የሚል አሳብ ላይኖራቸው ይችላል:: ወይም ሴቶች በወንዶች ዝቅተኛ ግምት እንደ ተሰጣቸው ይሰማቸዋል:: ወይም ደግሞ ወጣቶች ከሽማግሌዎች ጋር አይስማሙም:: ምንም እንኳን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ እነዚህ ውጥረቶች ባንወያይም፣ ውጥረቱ እውነተኛውን አንድነት ያጠፋዋል:: መሪዎች በቡድኖች መካከል የሚከሰቱትን ግጭቶች የሚፈቱበትን መንገድ ካላወቁ፣ ሰይጣን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል ሊፈጥር ይችላል:: ይህም የቤተ ክርስቲያኒቱን ውጤታማነትና ምስክርነት ያዳክማል::

> 30ኛ ጥያቄ:- ሀ) ከላይ ለተጠቀሱት ሦስት ነጥቦች ለእያንዳንዳቸው ምሳሌዎችን በመጥቀስ በቤተ ክርስቲያናችሁ እንዲህ ዓይነት ክፍፍልና የስሜት መጎዳት ሲፈጠር የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) የእያንዳንዱ አለመስማማት ውጤት ምን ነበር? ሐ) ችግሩ የተፈታው እንዴት ነው? ችግሩ ካልተፈታ፣ አለመስማማቱ ያስከተላቸው ቀጣይነት ያላቸው ውጤቶች ምን ምንድን ናቸው? መ) እግዚእብሔር በእነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ከመሪዎች ምን የሚጠብቅ ይመስልሃል?

## ክህሎት ስምንት:- የበደሉንን ይቅር ማለትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭቶችን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መንገድ መፍታት::

ይቅር ማለት መማር ያለብን ክህሎት ነው ማለቱ ትክክል ላይሆን ይችላል:: ያለን ባሕርይ ነው ማለትም አይቻልም:: ነገር ግን፣ በአገልግሎታችን ላይ የሚያጋጥሙንን ጉዳቶችና ሥቃዮች በፍጥነትና በተደጋጋሚ ይቅር ማለት አለብን:: ይህ ካልሆነ፣ ሰይጣን በሕይወታችን ውስጥ የመራርነትን ተክል ይተክላል:: ይህም አድጎ ይውጠናል:: መራር መሪ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጠቃሚ አገልግሎት ሊያበረክት አይችልም:: የሚነካው ሰውና ነገር ሁሉ በመራርነቱ ይመረዛል:: በዚህ ክፍል ይቅርታንና ግጭት ማስወገድን እንደ ክህሎት የጠቀስነው የአመራር አካል በመሆናቸው ነው:: የአመራር አገልግሎት በምንሰጥበት ጊዜ፣ ሁልጊዜም የሚጎዱን ሰዎች አሉ:: በመንፈሳዊ መንገድ መምራታችንን



ስመቀጠል ከፈለግን፣ የሚበድሉንን ሰዎች ይቅር ልንል ይገባል:: ሰዎች በሆነ መንገድ በሌሎች ሰዎች ሊጎዱ ስለሚችሉ፣ ይቅር ማለት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ይህ ካልሆነ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነት ሊኖር አይችልም::

በነገሮች ላይ የተወሰኑ አመለካከቶች ያሉን ኃጢአተኛ ሰዎች ስለሆንን፣ ግጭቶች መከሰታቸው የማይቀር ነው:: እነዚህን ግጭቶች ካልፈታን፣ ጥሩ ግንኙነቶች አይኖሩንም:: እንደ መሪዎች ሰዎች እንዲታረቁ ለማድረግም ከእነርሱ ጋር መሥራት ይጠበቅብናል:: ስለሆነም፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ በማኅበረሰቡ ውስጥ ጨውና ብርሃን ይሆን ዘንድ ለማገዝ መሪዎች ግጭቶችን የማስታረቅ ክህሎት መማር አለባቸው::

## በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጤናማ ግንኙነቶችን ለማስፈን መሪዎች ሊያዳብሩ የሚገባቸው አራት ችሎታዎች:-

ለማንኛውም አመራር ቁልፉ በክርስቶስ አካል ውስጥ ስምምነት ያለው ግንኙነት እንዲሰፍን ማድረግ ነው:: ጳውሎስ ስለዚህ ሲናገር፣ *«በአንድ አሳብ ተስማሙ፣ አንድ ፍቅር፣ አንድም ልብ፣ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ»* ብሏል (ፊልጵ. 2:2):: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የዚህ ዓይነት ጤናማ ግንኙነት ለማስፈን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አራት ችሎታዎች ያስፈልጓቸዋል::

1. መልካም ግንኙነቶችን የመፍጠር ችሎታ:: በአመራር ላይ ካሉት ሰዎች የሚኖር መተማመንና መከባበር ምእመናን የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን በፈቃደኝነት እንዲከተሉ ያደርጋል:: (ይህ በትምህርት 12 ውስጥ ቀርቧል::)

2. የመልካም ተግባቦት ክህሎት:: በቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምእመናን መካከል መልካም ግንኙነት ከሌለ፣ መሪው መልካም ግንኙነት ሊመሠርት ወይም ቤተ ክርስቲያኒቱን እግዚአብሔር ወደ ወጠነው ግብ ሊመራ አይችልም:: ክህሎት ስላለው ተግባቦት በትምህርት 13 እና 14 ውስጥ ተመልክተናል::

3. በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መሪዎችን የሚጎዱትን ሰዎች ይቅር የማለት ክህሎት ወይም ውሳኔ አለ። (ማስታወሻ፦ ይህ ዛሬ የምናጠነው ነው።)

4. በመሪዎች፣ በመሪዎችና በምእመናን፣ ብሎም በክርስቲያኖች መካከል የሚከሰቱትን ግጭቶች የመፍታት ብቃት አለ። ግጭቶችን እንዴት ክህሎት ባለው መንገድ መፍታት እንደምንችል ካላወቅን፣ በእግዚአብሔር ሕዝብና በሌሎች መሪዎች መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ልናደርግ አንችልም። ስምምነትና አንድነት ከሌለ ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ የሚፈልገውን ያህል ውጤታማ ሊሆን አይችልም። (ማስታወሻ፦ ግጭትን ስለ ማስወገድ በሚቀጥለው ሳምንት እናጠናለን።)

31ኛ ጥያቄ፦ ሀ) አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ እነዚህን ችሎታዎች ማወቁ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) መሪዎች እነዚህ አራት ክህሎቶች በማይኖራቸው ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እንደሚከሰት ግለጽ።

## መሪዎች የበደሏቸውን ሰዎች ይቅር ማለትን መማር አለባቸው።

32ኛ ጥያቄ፦ ሀ) 2ኛ ዜና 7:14፤ ነህ. 9:17፤ ኤር. 36:3፤ ማቴ. 6:12-16፤ 18:21-35፤ ማር. 11:25፤ ሉቃስ 6:37፤ 17:1-4፤ ኤፌ. 4:32፤ ቈላ. 3:13 አንብብ። ሀ) እነዚህ ጥቅሶች ስለ ይቅርታ ምን ያስተምሩናል? ለ) ሌሎችን ይቅር ካላልን፣ እግዚአብሔር እኛን ይቅር ስለ ማለቱ የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው? ሐ) ብዙ አማኞች እነዚህን ጥቅሶች ከሕይወታቸው ጋር የማያዛምዱት ለምን ይመስልሃል?

1. መሪዎች ሌሎች ክርስቲያኖች ሊጎዱአቸው እንደሚችሉ ተረድተው ራሳቸውን ማዘጋጀትና ልባቸውን ከመራርነት መጠበቅ አለባቸው።

አንድ ነገር ይደርስብናል ብለን ካሰብን፣ በሚከሰትበት ጊዜ ያን ያህል አንደነቅም። ለዚህ ነው ጴጥሮስ ሰዎች የችግር ጊዜ ይደርስብናል ብለው እንዲጠባበቁ የተናገረው። ስደት በሚደርስባቸው ጊዜ እምነታቸው እንዲናጋ አልፈለገም (1ኛ ጴጥ. 4:12)። ምንም እንኳን መጥፎ ዜናዎችን ከሰዎች ለመደበቅ



ብንሞክርም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን መጥፎ ነገሮች እንዳይደርሱባቸው ሰዎችን አስቀድሞ ያስጠነቅቃል። በክርስቶስ ምክንያት ሊደርስብን ስለሚችል ስደት አስቀድመን ካወቅን፣ አስቸጋሪዎቹ ነገሮች በሚደርሱብን ጊዜ እምነታችን አይናጋም።

በአመራርም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው። የአመራር ስፍራን የሚቀበል ማንም ሰው ከክርስቲያኖች ዘንድ ጎጂ ነገሮች እንደሚደርሱበት አስቀድሞ ማወቅ አለበት። እንደ መሪዎች፣ የሚያሙን፣ ስለ እኛ ውሸትን የሚናገሩ፣ ውሳኔያችንን የሚጠራጠሩ፣ ወዘተ. . . ወገኖች ያጋጥሙናል። የመሪነትን ስፍራ በመያዛችን ወይም ታዋቂነትን በማግኘታችን የሚቀኑና በዚህም ምክንያት ሊቀናቀኑን የሚፈልጉ ክርስቲያኖችና ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ይህ ደግሞ በቀላሉ ወደ መራርነት ሊመራን የሚችል ነገር ነው። በተቻለህ መጠን ጥሩ ነገር ለማድረግና መንፈሳዊ ሥራ ለመሥራት በምትጥርበት ጊዜ፣ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን በሚናገሩት ሰዎች ላይ መራር መሆኑ ቀላል ነው። ሁላችንም የሌላ እምነት ሰዎች ስለ እኛ መጥፎ ነገሮችን ሲያደርጉ ወይም ሲናገሩ በምንሰማበት ጊዜ እጅግም እንዳናዝን ከዓለም ቁጣ እንደሚሰነዘርብን መጠበቅ አለብን። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ሰው ስለ እኛ መጥፎ ነገር በሚናገርበት ጊዜ (በተለይም የሚቻለንን ያህል ፍትሐዊና እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ ለመምራት የምንጥር ከሆነ)፣ መራርነት ወደ ውስጣችን ሊገባ ይችላል። ይሁንና፣ ይቅር ለማለትና መራርነትን ለማስወገድ ልንጥር ይገባል። በምንም ዓይነት የበቀል አሳብ ሊገባብን አይገባም። የሚጎዱንን ሰዎች ለመበቀል የምንፈልግ ከሆነ፣ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አድርገን ልንመራ አንችልም። ስለሆነም፣ አንድ መሪ ሊያደርግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ ከልብ ይቅር ማለት ነው።

2. መጽሐፍ ቅዱስ አንዳችን ሌላችንን በምንበድልበት ጊዜ ይቅር እንድንባባል ያዝዛል።

ሀ. ብሉይና አዲስ ኪዳን ይቅርታና የሚያስተናግዱበት መንገድ። ብሉይ ኪዳን ሌሎችን ይቅር ስለ ማለት ብዙ

አይናገርም:: እንዲያውም የሰዎች የግንኙነት መሠረቱ «ዓይንን ላጠፋ ዓይን» የሚል ነበር (ዘጸአ. 21:23-24):: እግዚአብሔር እስራኤላውያን የብቀላ ፍላጎታቸውን በአኩል ክፍያ እንዲመጥኑ አስተምሯቸው ነበር:: በመሆኑም፣ አንድ ሰው ሌላውን ሊጎዳ የሚችለው የደረሰበትን ጉዳት ያህል ብቻ ነበር:: የእኔ ግድየለሽነት ወይም ቁጣ የሌላው ሰው ዓይን እንዲጠፋ ካደረገ፣ ግለሰቡና ዘመዶቹ ሊቀጡኝ የሚችሉት ዓይኔን እስከ ማጥፋት ድረስ ብቻ ነበር:: ይህ የበቀል መርሕ የተሰጠው ሰዎች ከደረሰባቸው በላይ ለመበቀል ያላቸውን ፍላጎት ለመገደብ ነበር:: ይሁን እንጂ፣ ብሉይ ኪዳን እግዚአብሔርን የሣለው ይቅርታ የጠየቀውንና እርሱን በመታዘዝ ለመኖር ይችል ዘንድ መንገዱን ለመቀየር የሚፈልግን ሰው ይቅር ለማለት እንደሚፈቅድ አምላክ አድርጎ ነው (ዘኁል. 14:17-20)::

አዲስ ኪዳን ግን ሰዎች በሚበድሉን ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን በጣም የተለየ አሳብ ይሰጠናል:: አዲስ ኪዳን ለበቀል ያለንን የተፈጥሮ ፍላጎት ከመወጣት ይልቅ፣ እግዚአብሔርን በአርአያነት ልንከተለው እንደሚገባን ይነግረናል:: የእግዚአብሔር ልጆችና የኢየሱስ ተከታዮች እንደ መሆናችን መጠን፣ ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እግዚአብሔርንና ኢየሱስን መምሰል አለብን:: እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፣ ተከታዮቹም ቅዱሳን መሆን አለባቸው (1ኛ ጴጥ. 1:15-16):: እግዚአብሔር ጠላቶቹን ስለሚወድ፣ እኛም ጠላቶቻችንን መውደድ አለብን (ማቴ. 5:43-48):: እግዚአብሔር ይቅር ባይ ስለሆነ፣ እኛም እንደ እግዚአብሔር ልጆች ይቅር ባዮች መሆን አለብን (ማቴ. 6:14-15)::

ለ. እግዚአብሔር የበደሉንን ይቅር ካላልን ኃጢአታችንን ይቅር እንደማይል ገልጸአል (ማቴ. 6:14-15):: ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የጸሎት ምሳሌ ሲሰጥ፣ ስለ ይቅርታም አስፈላጊ ትምህርት አካትቷል:: ሌሎችን ይቅር ካልን በኋላ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን እንድንጠይቅ አስተምሮናል:: በቤተ ክርስቲያን ፕሮግራም መዝጊያ ላይ ይህንን ጸሎት ስንጸልይ፣ ብዙ ሰዎች



እምብዛም ቃላቱን ልብ አይሉም:: ነገር ግን በዚህ ጸሎት ውስጥ የቀረበውን ትምህርት ማስተዋሉ ጠቃሚ ነው:-

1) እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲል የምንጸልየው እኛም ሌሎችን ይቅር እንደምንል ቃል በመግባት ነው:: ስለዚህ፣ ሌሎችን ይቅር ለማለት ካልፈለግን፣ እግዚአብሔርም ይቅር እንዲለን አንጠብቅም ማለት ነው::

2) ኢየሱስ ይቅር ሊለን ቃል የገባው ሌሎችን ይቅር በማለታችን ላይ ተመሥርቶ ነው:: ሌሎችን ይቅር የማንል ከሆነ፣ እግዚአብሔር ይቅር አይለንም ማለት ነው::

ይቅርታን ማግኘት ማለት ማዘናችንን ለእግዚአብሔር መናገር ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር ይቅር እንዲለን ከመጠየቃችን በፊት የበደሉንን ሰዎች ይቅር ማለት አለብን:: ስንቶቻችን ነን እስካሁንም ሰዎች ያደረሱብንን በደል የምናሰላስልና የበቀል ስሜት ያለን? አንድ ሰው ስለ እኛ ውሸት ሲናገር፣ በሆነ መንገድ ልንጎዳው እንፈልጋለን:: ውስጣችን ይቆጣና በምናየው ጊዜ ሁሉ በልባችን ውስጥ እሳት ይነድዳል:: ሰዎችን ይቅር ማለትና ያደረሱብንን ጉዳት መርሳት እንዴት ከባድ ነው? ስለሆነም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአንድ ሰው ከተናደድን ወይም አንደ መሪ ስለ እኛ ሐሜት በተናገሩት ሰዎች ላይ ከተቆጣን፣ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር የሚልበትን መሥመር ዘግተናል ማለት ነው::

ሐ. የበደሉንን ሰዎች ይቅር የምንልበት ምክንያት እግዚአብሔር ኃጢአታችን ምንም ያህል የከፋ ቢሆን ይቅር ሊለን ስለ ፈቀደ ነው:: ኢየሱስና በኋላም ጳውሎስ ሰዎች በሚጎዱን ጊዜ ለምን ይቅር ማለት እንዳለብን አብራርተዋል (ማቴ. 18:21-35፤ ቈላ. 3:13):: ሌሎችን በፍጥነትና በነፃ ይቅር ማለት ያለብን እግዚአብሔር ይቅር ስላለን ነው:: ጳውሎስ ለቈላስይስ ሰዎች ሲጽፍ እግዚአብሔር ይቅር ስላላቸው፣ እነርሱም ሌሎችን ይቅር ማለት እንዳለባቸው አስተምሮአል:: ኢየሱስ ይህንን የይቅርታ ትምህርት ያስተማረው በምሳሌ ነበር:: በተደጋጋሚ ኃጢአት በመሥራት በእግዚአብሔር ላይ የምንፈጽመውን በደል ሰዎች

ከሚያደርሱብን በደል ጋር በምናነጻጽርበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር ላይ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ዕዳ እንዳለበት ሰው መሆናችንን እንረዳለን:: ይህንን ገንዘብ ልንከፍል አንችልም:: ተስፋ ልናደርግ የምንችለው የእግዚአብሔርን ሙሉ ይቅርታ ብቻ ነው:: እግዚአብሔርም ንስሐ በምንገባበት ጊዜ፣ በቸርነቱ ይቅር ይለናል:: እግዚአብሔር ይቅር ካለን የማይቆጠር ኃጢአታችን ጋር ሲነጻጸር፣ ሌሎች በእኛ ላይ የፈጸሙት በደል ጥቂት ዕዳ እንዳለበት ሰው እነስተኛ ነው:: ሌሎችን ይቅር ለማለት አለመፍቀዳችን ራስ ወዳድነታችንን ያሳያል:: ይህ ብዙ ኃጢአታችንን በነፃ ይቅር ያለውን የአባታችንን ምሳሌነት አለመከተላችንን ያሳያል:: ወንጌሉን መረዳታችንና በእግዚአብሔር ፊት ምን ያህል ኃጢአተኞች መሆናችንን እንደ ተረዳን የሚታወቀው የበደሉንን ሰዎች ይቅር ማለት ስንችል ነው::

መ. መጽሐፍ ቅዱስ ሌሎችን ይቅር እንድንል ያዝዘናል:: ስለዚህ፣ ይቅርታ የማናደርግ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ በኃጢአት እየኖርን ነው ማለት ነው:: ጳውሎስ ሌሎችን ይቅር እንድንል አዝዞናል (ኤፌ. 4:32፤ ቈላ. 3:13):: ይቅር የማንል ከሆነ፣ ባለመታዘዝ እየተመላለስን ነው ማለት ነው:: ይህ በዝሙት፣ በስካር፣ ወይም በሌሎች ብዙውን ጊዜ በምናነሣቸው ኃጢአቶች እንደ መመላለስ ነው::

33ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙውን ጊዜ አማኞች ይቅር ለማለት የሚቸገሩባቸውን የበደል ዓይነቶች ዘርዝር:: ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ስለ ይቅርታ አስፈላጊነትና ይቅር በማይልበት ጊዜ ስለሚደርስበት ሁኔታ ታስተ ምራለች? ባለፈው ዓመት በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰጠውን ትምህርት ጠቅለል አድርገህ ግለጽ:: ሐ) ኢየሱስ ሌሎችን ይቅር ካላልን እግዚአብሔር ይቅርታ እንደማያደርግልን የሰጠውን ማስጠንቀቂያ የምናምን ከሆነ፣ ሌሎችን ይቅር አንልም እያሉ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር እንዲል ስለሚጠይቁት ሰዎች ይህ ምንን ያሳያል? መ) ይቅርታ ያላደ ረግህለት ሰው አለ? ከሆነ፣ ኃጢአትህን ለእግዚአብሔር ተናዘዝ:: ከዚያም እግዚአብሔር ወደ ግለሰቡ ሄደህ ይቅርታ እንድትጠይቅ ብርታት እንዲሰጥህ ጠይቅ:: በየቀኑ ለምትፈጽማቸው ኃጢአቶች ይቅርታ ሳታገኝ ሌላ ቀን ለምን ይለፍ?



ሠ. ክርስቲያኖች ሌሎችን ይቅር ማለት ያለባቸው ሦስት ዓይነት ሁኔታዎች:: ኢየሱስ፣ ጥፋቱ የማንም ይሁን የማን፣ ተ ከታዮቹ በራሳቸው ተነሣሽነት ይቅርታ እንንዲጠይቁና ግንኙነቱን እንዲፈውሱ ጠይቋል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ በመስጠት ይቅር ማለት ያለብን ሦስት ሁኔታዎች ተመልክተዋል::

<u>በመጀመሪያ</u>፣ ሰዎችን በምንበድልበት ጊዜ ይቅርታ እንዲያደርጉልን መጠየቅ አለብን:: ጥፋተኞቹ እኛ በምንሆንበት ጊዜ፣ ወደ እነርሱ ሄደን ይቅርታ መጠየቅ አለብን:: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንዲለን ከፈለግን፣ ግለሰቡን ይቅርታ የመጠየቁን ሂደት መወጣት አለብን:: ከእግዚአብሔርና ከግለሰቡ ጋር ያለን ግንኙነት ክፍትና ዳግም በፍቅር ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ስለምንፈልግ፣ እርሱ ወደ እኛ እስኪመጣ ድረስ እንጠብቀውም::

አንድን ሰው በምንበድልበት ጊዜ፣ የምንጠይቀው ይቅርታ ከንስሐ ጋር የተዋሃደ ነው:: ንስሐ ጉዳዩን መርሳት ብቻ አይደለም:: ሁልጊዜም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንስሐ የሚከተሉትን ነገሮች ያካተተ ነው::

1) ኃጢአት መፈጸማችንን ከመገንዘብ ይጀምራል:: ምንም ዓይነት ማመኻኛ ሳናቀርብ፣ በበደለን ሰው ላይ ኃጢአት መሥራታችንን እንቀበላለን:: ማመኻኛ በምናቀርብበት ጊዜ፣ ኃጢአቱ የእኛ ጥፋት መሆኑን ባለመቀበል በሌላ ሰው ወይም ነገር ላይ ጥፋቱን ለማላከክ እየሞከርን ነው ማለት ነው:: መታወቅ ያለበት ግን ሁልጊዜም ኃጢአትን የምንፈጽመው በምርጫችን ነው:: ማንም ወይም ምንም ኃጢአትን እንድንፈጽም ሊያስገድደን አይችልም:: ስለሆነም፣ ሁልጊዜም ጥፋቱ የሁኔታዎች ሳይሆን፣ የእኛው ነው::

2) በተግባራችን ያስከተልነውን ችግር ለማስወገድ የምንችለውን ጥረት እናደርጋለን:: የሰረቅነው ነገር ካለ፣ እንመልሰዋለን:: ስለ አንድ ሰው በማማት ስሙን አጥፍተን ከሆነ፣ ሐሜቱን ለሰሙት ሰዎች ነገሩ ትክክል እንዳልነበረ እንናገራለን::

3) የበደልነው ግለሰብ ለተፈጸመው ጥፋት ይቅርታ እንዲያደርግልን እንጠይቀዋለን። ተበዳዩ ጉዳዩን እንዲያነሣውና ከእንግዲህ በመሐል ግርዳ ሆኖ ግንኙነቱን እንዳያውክ እንጠይቀዋለን። ልናደርግ የምንችለው ግለሰቡ ይቅር እንዲለን ብቻ ነው። በልቡ ውስጥ ያለውን የጉዳት ስሜትና ኀዘን እንዲያስወጣ ማስገደድ አይቻልም። እግዚአብሔር የሚጠይቀን ግለሰቡን ይቅርታ እንድንጠይቀው ብቻ ነው። ጳውሎስ እንዳለው፣ ሁልጊዜም በሰላም መኖር ሳይቻል ይችላል (ሮሜ 12:18)። አሁን ጉዳዩ በሌላ ሰው እጅ ስለሆነ፣ ይቅርታ በማድረግ ቁጣውን መተው ወይም በቀልን የመከተል ምርጫው የእርሱ ነው። ግሰሰቡ ይቅርታ ለማድረግ ፈቃደኛ ባይሆን እንኳን፣ እኛ እግዚአብሔርን ታዝዘን ይቅርታ ስለጠየቅን ነፃ ነን።

4) ተግባራችንን በመቀየር ሰዎችን የሚጎዳ ነገር ሳለማድረግ እንጠነቀቃለን። ለአንድ ሰው ወይም ለእግዚአብሔር ንስሐ በምንገባበት ጊዜ፣ ተግባራችንን ለመለወጥ ቃል እየገባን ነው። ግለሰቡ ጉዳዩን እንዲረሳው ከጠየቅን በኋላ፣ የቀድሞ ተግባራችንን በመፈጸም ግለሰቡን የምንጎዳው ከሆነ፣ ንስሐ አልገባንም ማለት ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፣ አንድ ሰው ሲበድለን ወይም በሆነ ምክንያት በእኛ ላይ ሲቆጣ፣ ችግሩን ለመፍታት የመጀመሪያውን እርምጃ መውሰድ አለብን (ማቴ. 5:23-24)። እነርሱ እንዲመጡ ከመጠበቅ ይልቅ፣ እኛ ወደ እነርሱ እንሄዳለን። ኢየሱስ አንድ ሰው እርሱን ለማምለክ በሚሄድበት ጊዜ ከሌላ ሰው ጋር ቅራኔ እንዳለው ካወቀ፣ መጀመሪያ ሄዶ ችግሩን ለማስተካከል መሞከር እንዳለበት ለተከታዮቹ ተናግሯል። ኃጢአቱ ወይም የተበላሸው ግንኙነት ያሳደረብንን ተጽዕኖ በመግለጽ ዕርቅ ለማድረግ መፈለጋችንን መግለጽ አለብን። አሁንም ቢሆን ግለሰቡ ኃጢአቱን እንዲናዘዝልን ወይም ይቅርታ እንዲያደርግልን ልናስገድደው አንችልም። (ማስታወሻ፦ ብዙውን ጊዜ የሚጎዱን ሰዎች በደል እንደ ፈጸሙብን ሳያውቁ ይችላሉ። ሕመሙ ያለው በውስጣችን እንጂ እነርሱ ዘንድ አይደለም። ስለሆነም፣ ከእነርሱ ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ፣ ያደ



ረሱብንን በደል እንዲገነዘቡ በማድረግ እያገዝናቸው እንጂ እየወቀስናቸው አለመሆናችንን ማስረዳት አለብን።) ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ሳደረሱብን በደል ይቅርታ ማድረጋችንን መግለጽ አለብን።

<u>ሦስተኛ</u>፣ አንድ ሰው ሳደረሰብን በደል ይቅርታ በሚጠይቀን ጊዜ፣ ይቅርታ ማድረግ አለብን። አንድ ጊዜ ጴጥሮስ ስንት ጊዜ ይቅር ማለት አለብኝ? የሚል ጥያቄ ለኢየሱስ አቀረበ። የአይሁድ መሪዎች ሦስት ጊዜ ይቅርታ ማድረግ በቂ ነው የሚል አሳብ ስለነበራቸው፣ ጴጥሮስ ሰባት ጊዜ ይቅር ማለት መንፈሳዊ መሆንን ያሳያል የሚል ግምት ነበረው። ኢየሱስ ግን ሰባት ጊዜ ሰባ ጊዜ ይቅር ማለት እንዳለበት ገለጸለት። ይህም ይቅርታችን ገደብ ሊኖረው እንደማይገባ የሚያመለክት ነበር (ማቴ. 18:21-22)። ግሰሰቡ ወደ እኛ መጣም አልመጣምም፣ ይቅርታ ማድረግ ይጠበቅብናል።

## የጎሳ ይቅርታ

ይቅርታ የምናደርገው ለግለሰቦች ብቻ ሳይሆን ይችላል። እንደ ጎሳዎችና አገሮችም ይቅርታን መለማመድ አለብን። በጎሳዎች መካከል ጥላቻና የበቀል ስሜት እስካለ ድረስ፣ አንዲት አገር ሰላም ሊኖራት አይችልም። አንዳንድ ጎሳዎች ከብዙ ትውልዶች በፊት በእነርሱ ላይ የተፈጸመውን በደል ያስባሉ። በመሆኑም፣ የሚበቀሉበትን አጋጣሚ ይጠብቃሉ። ይህ በቀል የሚፈጸመው ለሌላ ጎሳ አባል ሥራ በመከልከል፣ በመጉዳት ወይም የዚያ ጎሳ አባላትን በመግደል ሊሆን ይችላል። በሩዋንዳ ይህ የጎሳ በቀል ከአንድ ሚሊዮን የሚበዙ ሰዎችን ለሞት ዳርጓል። እንዲሁም ደግሞ አገሮች በጦርነት ጉዳት ያደረሰባቸውን አገር ይጠላሉ። የትኛዋም አገር ዜጎቿ ይቅርታን እስካልተማሩ ድረስ ጤናማና አንድነት ያላት ልትሆን አትችልም።

የሚያሳዝነው፣ የጎሳ ጥላቻ በአማኞችም መካከል ሊኖር መቻሉ ነው። ለሽምግልና እንዲመረጡ ድምጻችንን ባለመስጠት፣ ሰጎሳ አባሎቻችን ልዩ ዕድል በመስጠት፣ በሌላ ጎሳ አባላት ላይ የጥርጣሬና የክፋት አሳቦችንና ቃላትን በመግለጽ፣ የጎሳው አባላት

ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች ወንጌሳውያንን ባለመሳክ፣ ወዘተ. . . ጥሳቻችንን ልንገልጽ እንችሳለን። ኅሰኝነት በሌሎች ሰዎች ሳይ ያለንን አመለካከት እንዲቀይር በምናደርግበት ጊዜ፣ እንደ ወንድሞችና እኅቶች በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ተጣምረን መኖር እንዳለብን የሚያስረዳውን እውነት እንጥሳለን።

ከዚህ በታች ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ የተገለጹት አሳቦች ኅሳዊና አገራዊ ይቅርታዎችን ይጨምራሉ። እንዲያውም፣ ዓለም ይህን የይቅርታ ደረጃዎች ካልተከተሉ፣ ሰዎች በሰሳም አብረው ለመኖር እንደማይችሉ እየተገነዘበች ነው። በደቡብ አፍሪካ ጥቁሮችና ነጮች አብረው ለመሥራት መወሰናቸው ዓለም ኢየሱስ ያስተማረውን ለመተግበር በመሞከር ሳይ መሆኗን የሚሳይ ጠቃሚ ምሳሌ ነው። ዓለም እነዚህን የእርቅ ደረጃዎች እየተከተለች፣ የእግዚአብሔር ቃል እውነትና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ያሳቸው አማኞች ኅሳዎችን ለማስታረቅ ጥረት አለማድረጋቸው አሳዛኝ ነገር ነው።

| |
|---|
| 34ኛ ጥያቄ፦ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ኅሳዊ እርቅ አስመሩን የሚሳዩትን ምሳሌዎች ጥቀስ። ለ) ይህ ኅሰኝነት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት እንደሚገኝ ግለጽ። ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አማኞች ኅሳዊ ይቅርታን በማድረግ እርስ በርሳቸው እንደ አንድ ቤተሰብ እንዲተያዩ ለማድረግ ምን ሊያደርጉ ይችሳሉ? |

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ምን እንደ ሆነና እንዳልሆነ መረዳት።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ምንድን ነው? በአንድ ሰው እግር ሳይ ወድቆ ይቅር በለኝ ማለት ነው? ወይስ ጉዳዩ ተረስቷል ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እውነተኛ ይቅርታና ይቅርታ ስሳልሆነው ነገር የሚያስተምረውን አሳብ መረዳቱ ጠቃሚ ነው።

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ያልሆነው፦

ሀ. አንድን ሰው ይቅር አልን ማለት፣ ያደረገው ነገር ስሕተት አልነበረም ማለት አይደለም። አንድ ሰው ስለ እኛ ውሸትን በመናገር ስማችንን ቢያጠፋና ይቅርታ ብናደርግለት፣ ውሸትን መናገሩ ስሕተት አይደለም ማለታችን አይደለም። ኢየሱስ ለፈጸሙት ኃጢአት ይቅርታ ያደርግላቸውና ከእንግዲህ ኃጢአት እንዳይሠሩ ያስጠነቅቃቸው ነበር (ዮሐ. 8:11)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ሁልጊዜም ጥፋቱ ወይም ኃጢአቱ መፈጸሙን አይክድም። ይህ ስሕተት ወይም ድክመት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔርና በእንተ ሳይ የተፈጸመ ኃጢአት ነው። እውነተኛ ይቅርታ የተፈጸመውን ጥፋት አደገኛነት ለመደበቅ አይሞክርም።

ለ. ይቅር በምንልበት ጊዜ፣ ግለሰቡ እኛን ይቅርታ መጠየቅ የለበትም ማለታችን አይደለም። ይቅር ስንል፣ በእኛ በኩል ለችግሩ እልባት እየሰጠን ነው። የተሰማንን ሕመምና መራርነት በማስወገድ ከልባችን የበቀልን ስሜት ለማራቅ መሞከራችንን እናሳያለን። ሌሳኛው ም ግለሰብ ይቅርታን በመጠየቅ በእግዚአብሔር ፊት የራሱን ጉዳይ ማስተካከል ይጠበቅበታል።

ሐ. ይቅር በምንልበት ጊዜ፣ ግለሰቡን ከፈጸመው ነገር ነፃ በማድረግ ቅጣት እንዳያደርስበት እያደረግን አይደለም። እግዚአብሔር በእርሱ ሳይ የሚያመጣውን ማንኛውንም ቅጣት ወይም ፍርድ እናስወግድለትም። አንድን ሰው ከኃጢአት ነፃ ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ሊሰጥ ያሰበውን ቅጣት ሊያነሣ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። እኛ የምንለው ሳደረሳብን ጥፋት ልንቀጣው እንደማንፈልግ ብቻ ነው። በግለሰቡ ሳይ የነበረንን ጥሳቻ፣ ቁጣና የበቀል ስሜት ማንሣታችንን እንገልጻለን።

መ. ይቅርታ ከእርቅ ጋር አንድ አይደለም። እርቅ እውን የሚሆነው ሁሳቱም ወገኖች የሻከረውን ግንኙነት ለማስተካከል ሊስማሙ ነው። እርቅ የሚከናወነው ሁለቱም እውነተኛ ይቅርታ ሲያደርጉ ነው። እግዚአብሔር የሚፈልገው ልጆቹ ከልባቸው እንዲታረቁ ነው። ነገር ግን ይህንን በግድ ማስፈጸም አይቻልም። ሽማግሌዎች አንድ ሰው ይቅርታ እንዲጠይቅና እንዲታረቅ ለማስገደድ መሞከር የለባቸውም። ይሁንና፣ አንደኛው ወገን፣ ሌሳኛው የፈለገውን እርምጃ ቢወስድም፣ ይቅርታ ሊያደርግ ይችሳል።

ሠ. ይቅርታ አደረግን ማለት አንድ ሰው ያደረገብንን ሙሉ በሙሉ እንረሳዋለን ማለት አይደለም። የደረሰብንን በደል ሙሉ በሙሉ ልንረሳ አንችልም። አስቃቂ ትውስታዎች ከአእምሯችን እንዲጠፉ ልናደርግ የምንችልበት መንገድ የለም። ነገር ግን ይቅርታ የፈቃዳችን ውሳኔና ተግባር ነው። ይህ ጉዳዩን እንደገና ላለማንሣት ወይም ጉዳዩ ከግለሰቡ ጋር ባለን ግንኙነት ላይ መሰናክል እንዳይሆን የምንመርጥበት መንገድ ነው።

2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ፦

ሀ. ይቅር በምንልበት ጊዜ፣ ግለሰቡ በእኛ ላይ የፈጸመው ነገር ስሕተትና ኃጢአት መሆኑን እንቀበላለን። የፈጸመብንን በደል ለመሸፋፈን ወይም ማመኻኛ ለማቅረብ እንሞክርም። ከዚህ ይልቅ፣ ላለመበቀልና ግለሰቡ ለፈጸመብን በደል በሆነ መንገድ ዋጋ እንዲከፍል ላለመጠየቅ እንመርጣለን። በግለሰቡ ላይ ሥቃይ ሳናስከትል ሥቃዩን ራሳችን ለመቀበል እንመርጣለን ማለት ነው።

ለ. ይቅር በምንልበት ጊዜ፣ የተፈጸመብንን በደል ላለመመዝገብ እንወስናለን (1ኛ ቆሮ. 13:5)። ብዙውን ጊዜ አንድ ሰው ሲበድለን፣ የተፈጸመብንን በደል እናስታውሳለን። ይቅር ብዬሃለሁ ልንል ብንችልም፣ በልባችን ውስጥ ግለሰቡ ያደረሰብን በደል በዝርዝር ተቀምጦ ይገኛል። እንደገና በሚጎዱን ጊዜ፣ እነዚያን ነገሮች እንደገና እናስታውሳቸዋለን። እግዚአብሔር ይቅር በሚለን ጊዜ ኃጢአታችንን «ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ» ያደርገዋል (መዝ. 103:12)። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እኛም ይቅር ስንል፣ ጉዳዩን አርቀን ልንወስደውና ዳግም ግለሰቡን ተጠያቂ ከማድረግ ልንቆጠብ ይገባል። ይልቁንም፣ እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ይፈታው ዘንድ ጉዳዩን ለእርሱ እናቀርባለን። የመቅጣት መብት ያለው እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም (ሮሜ 12:17-20)።

መ. ይቅር በምንልበት ጊዜ የተከሰተውን ችግር ለሰዎች ከመናገር እንቆጠባለን። ብዙውን ጊዜ ጉዳዩን ለሰዎች የምናውጀው የበደለንን ሰው ለመጉዳት ካለን ፍላጎት በመነሣት ነው። የሐሜት



ሥሩ የሰውን ስም የማጉደፍ ወይም ግለሰቡ ከሌሎች ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት የማበላሸት ፍላጎት ነው። ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ፣ ከእንግዲህ ግለሰቡን ለመጉዳት አልፈልግም ማለታችን ነው። በመሆኑም፣ ግለሰቡ የፈጸመብንን በደል ለሌሎች ከመናገር እንቆጠባለን። እግዚአብሔር በእርሱ ላይ ስለምንፈጽማቸው ኃጢአቶች ለሌሎች አይናገርም። እኛም አንድ ሰው የፈጸመብንን በደል ለሌላው መናገር የለብንም። የሐሜት ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ አጥፊ ከሆኑት ኃጢአቶች አንዱ ነው። በአመዛኙ ሐሜት ችግሩን የበለጠ ያወሳስበዋል። ሌሎች ሰዎች በሚሳተፉበት ጊዜ፣ ችግሩን ለመፍታትና እርቅ ለመፈጸም ሁኔታው አስቸጋሪ ይሆናል። በአሜሪካ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ስለ ሌላ አማኝ ሐሜት የሚነዙትን ሰዎች የሚቀጣ ሕግ አላት። ይህች ቤተ ክርስቲያን ሐሜት እንደ ስካርና ዝሙት ካሉት ኃጢአቶች በበለጠ የቤተ ክርስቲያንን አንድነት የሚያናጋ መርዝ መሆኑን የተገነዘበች ናት።

*35ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የሐሜት ኃጢአት የቤተ ክርስቲያንን ስምምነትና አንድነት ሲያበላሽ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ይህ ሐሜት የተጀመረው ለምን ነበር? ሐሜቱን የጀመረው ግለሰብ ልባዊ ፍላጎት ምን ይመስልሃል?*

ለአንድ ሰው እኛን የሚጎዳ ተግባር ስለ መፈጸሙ መናገር የማያስፈልግበት ጊዜ ይኖራል። አንድ ሰው እኛን መጉዳቱን የማያውቅ ከሆነ፣ በምንጋፍጠው ጊዜ ግራ መጋባቱ የማይቀር ነው። ብዙ ጊዜ ሰዎች ምን እንዳጠፉ ሳያውቁ ሊጎዱን ይችላሉ። ለምሳሌ፣ አንድ ወዳጅህ ሰላም ሳይልህ በአጠገብህ አልፎ ይሄዳል። በዚህም የአንተ ስሜት ይጎዳል። በዚህ ጊዜ ወደ ግለሰቡ በመሄድ በድለኸኛል ማለቱ ዋጋ የለውም። አልፎ ሲሄድ አላየህስ እንደ ሆነ? ወይም ደግሞ በአእምሮው ውስጥ ከባድ ጉዳይ እያሰላሰለ በአካባቢው ላሉት ሰዎች ትኩረት ሳይሰጥ ቀርቶስ እንደ ሆነ? እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ስለ ጉዳዩ ሳያነሡ ግለሰቡን ይቅር ማለቱ ተገቢ ይሆናል።

ሠ. ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ ትኩረት የምንሰጠው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የምሕረትና የጸጋ ባሕርያት ሳይ እንጂ፣ በፍትሕ ላይ አይደለም:: ይቅርታ ምሕረትን ያሳያል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሕረት አያሌ ገጽታዎች አሉት:: <u>በመጀመሪያ</u>፣ ችግር ለደረሰባቸው ሰዎች ምንም ዓይነት ምላሽ ሳይጠብቁ ጥሩ ነገር ማድረግ ማለት ነው:: (ለምሳሌ፣ መበለትን ወይም ወላጅ ያጡትን ልጆች መርዳት::) ሁለተኛ፣ ምሕረት ፍትሕን መጠየቅ ሳይሆን፣ የበደለን ግለሰብ ነፃ እንዲሆን ማድረግ ነው:: ይቅርታ የሚያተኩረው በዚህኛው የምሕረት ገጽታ ላይ ነው:: አንድን ሰው ይቅር ስንል ሳለመቅጣት መወሰናችን ነው:: ከፍርድም ነፃ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን:: ኢየሱስና እስጢፋኖስ በመሞት ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር እንዲል ሲጠይቁ ይህንኑ ማለታቸው ነበር (ሉቃስ 23:34፤ የሐዋ. 7:60):: እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው ሊቀበሉት ከሚገባው ፍርድ ይቅር እንዲላቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን መግለጻቸው ነበር::

ነገር ግን በምሕረት እምብርት ላይ ያለው ጸጋ ነው:: ጸጋ ለማይገባው ሰው አንድ መልካም ነገር ማድረግ ነው:: ስለሆነም፣ አንድን ሰው ይቅር በምንልበት ጊዜ፣ ከሁሉም የተሻለ ነገር እንዲገጥመው መፈለግ አለብን:: ይህ ማለት ይቅርታን የምንሰጠው ግለሰቡን በማይጎዳ መንገድ ነው ማለት ነው:: ግለሰቡን ጠንከር ባለ ወቀሳ ሳይሆን፣ በገርነት እናስተናግደዋለን:: አሳስፈላጊ የሆነ ኀፍረት እንዳናደርስበትም ጥንቃቄ እናደርግለታለን:: ሕዝብ በተሰበሰበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ «ስለ እኔ ለተናገርከው ውሸት ይቅር ብዬሃለሁ፣» እንልም:: ከዚህ ይልቅ፣ በግልና በገርነት ይቅርታን በማድረግ መልካም ነገር እንዲገጥመው መፈለጋችንን እናሳያለን:: በጸጋ የተሞላ ይቅርታ ማለት እግዚአብሔር ግለሰቡን ከመቅጣት ይልቅ እንዲባርከው መፈለግ ማለት ነው:: እግዚአብሔር የጎዳንን ግለሰብ እንዲባርከው እንጸልያለን:: የበደለንን ሰው እግዚአብሔር እንዲባርከው ከልባችን መጸለይ መቻላችን እውነተኛ ይቅርታ ማድረጋችንን ሊያረጋግጥልን ይችላል::



ረ. ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ፣ በልባችን ውስጥ ያለውን መራርነት ለማስወገድ እንፈልጋለን (ዕብ. 12:15):: ይቅርታን የሚያደርገው ሰው ይቅርታን ከሚያገኘው በበለጠ ይጠቀማል:: ይቅርታ በማናደርግበት ጊዜ፣ ልባችን በመራርነት ይሞላል:: ያ መራርነት ደግሞ የምናደርጋቸውን ነገሮችና የምንመሠርታቸውን ግንኙነቶች በሙሉ ይበክልብናል:: መራራ ሎሚ ከመጠጡ በኋላ ቡና መጠጣት የቡናውን ጣእም እንደሚቀይር ሁሉ፣ መራርነታችን ሕይወታችንን ሁሉ ያውከዋል:: ብዙውን ጊዜ መራር ሰው በጓደኞቹ፣ በቤተሰቡና አብረውት በሚሠሩት ሰዎች ሁሉ ላይ ይቆጣል:: በፈራጅነት መንፈስ ተሞልቶ በዙሪያው ባሉት ሰዎች ሁሉ ላይ ንዴቱን ይገልጻል:: ማንኛውም ዓይነት ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ፣ የችግሩ ምንጮች ሌሎች ሰዎች ናቸው የሚል አሳብ ይኖረዋል:: ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ፣ መራራው ሥር ከልባችን ተነቅሎ ይወጣል፣ የጌታም ደስታ ወደ ሕይወታችን ይመለሳል::

> 36ኛ ጥያቄ፡- አንድ ሰው ይቅር ባለማለቱ ምክንያቱ ሕይወቱ መራራ የሆነበትን ሁኔታ ግለጽ:: ለ) መራርነቱ ግለሰቡ ከጓደኞቹ፣ ከቤተሰቦቹና ከሌሎችም ሰዎች ጋር ባለው ግንኙነት ላይ ተጽዕኖ ያሳደረው እንዴት ነበር? ሐ) ይቅርታ ማድረግ እንዴት ደስታን እንዳመጣለትና መራርነቱን እንዳስወገደ ግለጽ::

ሰ. ይቅርታ በምናደርግበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር መታመናችንንና በእርሱ ላይ ጥገኛ መሆናችንን እናሳያለን:: ብዙውን ጊዜ አንድ ነገር ሲደርስብን በልባችን በእግዚአብሔር ላይ እንቆጣለን:: «ለምን ይህ ነገር እንዲደርስብኝ አደረግክ? ግለሰቡን ለምን አልቀጣኸውም?» ልንል እንችላለን:: ነገር ግን እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን በምንጠይቅበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር ዓለምንና ሁኔታዎችን እንደ ፈለገ የመምራትና የመቆጣጠር መብት እንዳለው እንዘነጋለን:: በሥልጣኑ ላይ እያመፅን ነው ማለት ነው:: መራር በምንሆንበት ጊዜ፣ እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ እንዲፈጸም የፈቀደውን ነገር ለመቀበል እንፈልግም እያልን ነው:: ይቅርታን በምናደርግበት ጊዜ፣ በእግዚአብሔር መታመናችንን እናሳያለን:: እርሱ ነገሮችን በመቆጣጠር ላይ መሆኑንና በእንድ ሁኔታ ውስጥ

የፈለገውን የማድረግ መብት እንዳለው እንረዳለን:: እግዚአብሔር አሁንም ሆነ በዘላለሙ መንግሥት የመቅጣት መብት እንዳለው ይገባናል:: እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቅር በመረዳት እናርፋለን:: መራራ ነገሮችን በመውሰድ ለክብሩ ሊያውላቸው እንደሚችል እንገነዘባለን:: እርሱ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገሮች ሁሉ ለበጎ እንዲደረጉ እቆጣጠራቸዋለሁ አላለምን? (ሮሜ 8:28)::

37ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙ ክርስቲያኖች ኃጢአታቸው እስኪታወቅ ድረስ ይቅርታ የማይጠይቁት ለምን ይመስልሃል? ለ) እንዲህ ዓይነት ሰዎች ስለ ኃጢአትና ከእግዚአብሔር ጋር ስላላቸው ግንኙነት ምን ዓይነት ግንዛቤ ያላቸው ይመስልሃል? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች ከአንድ ሰው አንድ ነገር ከሰ ረቁ በኋላ «ይቅር በለኝ» ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? መ) አንድ አማኝ ወደ በደለው ግለሰብ በመሄድ ያጠፋውን ነገር ማስተካከል በሚያስፈልገው ሰዓት የሚጋፈጠውን ሁኔታ ግለጽ:: ሠ) ብዙ አማኞች የሚያስቡትን ይቅርታ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ጋር አነጻጽር:: ሁለቱ ይቅርታዎች የሚለያዩትና የሚመሳሰሉት እንዴት ነው?

## ራሳችንንም ይቅር ማለት አለብን::

በአብዛኛው ስለ ይቅርታ በምናስብበት ጊዜ፣ ወደ አእምሯችን የሚመጣው በሰው ላይ የምንፈጽመው በደል ወይም ሌላ ሰው በእኛ ላይ የሚፈጽመው በደል ነው:: ስለሆኑ ለፈጸምነው ኃጢአት ራሳችንን ይቅር የማለቱስ ጉዳይ እንዴት ይታያል? ራሳችንን ይቅር ማለት አለብን? አዎን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ይቅርታ ተተኪ የሌላቸውን ጥፋቶችና በደሎች በምንፈጽምበት ጊዜ ሳይቀር፣ ራሳችንን ይቅር ማለት እንዳለብን ያስተምረናል:: በአብዛኛው ከራስ ይልቅ ሌላውን ሰው ይቅር ማለቱ ቀላል ነው:: ስላስከተልነው ችግር በተደጋጋሚ እናሰላስላለን:: ልጆቻቸው ከጌታ የኮበለሉባቸው ክርስቲያን ወላጆች ቀሪ ዘመናቸውን የሚያሳልፉት ራሳቸውን በመውቀስ ነው:: ዝሙት የፈጸመ ሰው ሚስቱ ይቅር ብትለውም፣ ራሱን ይቅር ለማለት ይቸገራል:: ነገር ግን እነዚህን የይቅርታ ትምህርቶች ከራሳችን ሕይወት ጋርም ማዛመድ አለብን:: ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ይቅር እንደሚለን ማመን አለብን:: እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር እንደሚልና



ከእንግዲህም እንደማያስታውስ እየተናገረ (መዝ. 103:12)፣ እኛስ የተስፋ ቃሉን በማመን ራሳችንን ይቅር ማለት አይኖርብንም ይሆን?

38ኛ ጥያቄ:- ሀ) ክርስቲያኖች ራሳቸውን ይቅር ለማለት በመቸገራቸው ለብዙ ጊዜ በበደለኛነት ስሜት የሚሠቃዩባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ:: ለ) ይህ አግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ሁሉ ይቅር እንደሚል የሰጠውን ተስፋ ስለ ማመናቸው ምን ያሳያል?

## ይቅርታ ለማድረግ መከተል የሚገቡን ደረጃዎች:-

ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን መጠን ትችት እንደሚደርስብን ማወቅ አለብን:: ምንም ያህል ታዋቂነት ቢኖረን፣ ወይም ምንም ያህል ጥረት ብናደርግ፣ ሰዎች ስሜታችንን የሚጎዱበትና በደል የሚፈጽሙብን ጊዜ እንደሚመጣ መገንዘብ አለብን:: በመሆኑም፣ ይህንን የይቅርታ «ክህሎት» ማወቅ አለብን:: ምናልባትም በይበልጥ ትክክል የሚሆነው የይቅርታ ልማድ ሊኖረን ይገባል የሚለው ይሆናል:: ምክንያቱም ይቅርታ በብዛት ልናደርገው የሚገባን ነገር ነው:: ሌሎች ሰዎች በሚያደርሱብን በደል ምክንያት ለመራርነት እንዳንጋለጥ መሪዎች የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ይኖርብናል:-

1. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለሰዎች አስተያየት ብዙ ትኩረት መስጠት የለባቸውም:: ሰዎች ለሚሰጡን ጥሩ አስተያየት ብዙ ትኩረት መስጠት የለብንም:: ምክንያቱም ሥራውን ያከናወነው እግዚአብሔር እንጂ ራሳችን አለመሆናችንን እናውቃለን:: እንዲሁም ደግሞ ሰዎች የሚሰነዝሯቸውን ትችቶች፣ ጎጂ አስተያየቶችና ተግባራትም አክብደን ማየት የለብንም:: አንድ ሰው ለብዙ ጊዜ በባዶ እግሩ የሚሄድ ከሆነ፣ ስለሚላመድ እንቅፋት ቢመታው ብዙ አያምመውም:: እኛም ራሳችንን በማስለመድ የሰዎች አስተያየቶች ስሜታችንን እንዳይጎዱ ማድረግ አለብን:: ሰሎሞን እንዳስጠነቀቀን፣ ለሚነገረው ነገር ሁሉ ጆሮ መስጠት የለበንም (መክ. 7:21-22):: አንድ ምሳሌ እንደሚለው፣ «የውሾች ጩኸት ተጓዦቹን ከመንገዳቸው አያስተጓጉልም::» ሰዎች ምንም ያህል ቢጮሁ፣ እግዚአብሔርን እስከ ታዘዝንና እስከ ተከተልን ድረስ ሥራው መቀጠሉ የማይቀር ነው::

2. የሰዎችን እስተያየቶች እልፌህ ልባዊ ፍላጎታቸውን ለማንበብ አትሞክር፡፡ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ለሚናገሯቸውና ለሚያደርጓቸው ነገሮች ሰውር ትርጉሞችን እንፈልጋለን፡፡ ልባዊ ፍላጎታቸው ምን ሊመስል እንደሚችል እንገምታለን፡፡ ይህ ግን በምንም ዓይነት ጠቃሚ አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር በስተቀር ማናችንም የሰውን ልብ ልናይ አንችልም፡፡ አንድ ነገር ግልጽ እስኪሆን ድረስ ስለዚያ ጉዳይ መጨነቁ ተገቢ አይሆንም፡፡ በማቴዎ ስ 7:1-5 ኢየሱስ በሰዎች ላይ እንዳንፈርድ አስጠንቅቆናል፡፡ ይህ ማለት ሰዎች የሚያደርጓቸውን ነገሮች ተመልክተን ከተሳሳተ ልባዊ ፍላጎት የመነጨ ነው እንዳንል ወይም መረጃ ሳይኖረን ሰ ዎችን እንዳንተች የሚያሳስብ ነው፡፡ ጳውሎስ ፍቅር ሁሉን እንደሚያምን አመልክቷል (1ኛ ቆሮ. 13:5-7)፡፡ ፍቅር ከሰዎች ቃላት፣ ልባዊ ፍላጎቶችና ተግባራት እጅግ የተሻለውን ነገር እንጂ፣ እስከፊ የሆነውን አይጠብቅም፡፡ ብዙውን ጊዜ በሰዎች ልብ ውስጥ አለ ብለን የምናስበው ነገር የተሳሳተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ እሉታዊ ነገሮችን በመገመታችን በራሳችን ላይ አላስፈላጊ ሥቃይ ያስከትልብናል፡፡ የሚያሳዝነው፣ ስለ ሰዎች ልባዊ ፍላጎት የራሳችንን ግምት ወስደን ለሌሎች ሰዎች ይህንኑ ግምታችንን በመናገር ሐሜትን እናደርጋለን፡፡ እንዳንድ ጊዜ ውሳኔያችን የሚመሠረተው በእነዚህ የውሸት ግምቶቻችን ላይ ነው፡፡ ሰዎች ሊጎዱን እየፈለጉ ነው ወደሚል ግምት ካልገባን፣ ብዙም ይቅር የምንለው ነገር አይኖርም፡፡

3. እንድ ሰው እኛን የሚጎዳ ተግባር በሚፈጽምበት ጊዜ፣ ይህንኑ ለሰዎች አለመናገር፡፡ በሐሜት ኃጢአት አትሸነፍ፡፡ ለሰዎች በመናገር የግለሰቡን ስም አታጥፋ፡፡ ለእግዚአብሔር ብቻ ተናገር፡፡ ውስጣዊ እፎይታ ታገኝ ዘንድ ለአንድ ሰው መናገር ካለብህ፣ በምንም ዓይነት ጉዳዩን ለሌላ ሰው አሳልፎ የማይሰጥ ሰው ም ረጥ፡፡

4. ሁኔታውንና ሥቃዩን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ስጥ፡፡ በጸሎት ግለሰቡን ይቅር ማለትህን ለእግዚአብሔር ተናገር፡፡ ከየትኛ ውም መራርነትና የበቀል አሳብ ራቅ፡፡



5. ግለሰቡን መጋፈጥ እንዳለብህ ወይም እንደሌለብህ ወስን፡፡ የምትጋፈጠው ከሆነ፣ ለምን ይህንን እንደምታደርግ ጠንቅቀህ እወቅ፡፡ መጋፈጥ ያለብህ ግለሰቡ አንተን እንደ በደለህ የሚያውቅ ከሆነ፣ ወይም ለመንፈሳዊ እድገቱ ችግር የሚፈጥርበት ከሆነ ብቻ መሆን አለበት፡፡ የምትጋፈጠው ግለሰቡ መጥፎ ስሜት እንዲሰማው ወይም በአንተ ላይ ያሳደረው ችግር እንዲወገድ አይደለም፡፡ ስሜትህ ከመቀዝቀዙ በፊት አታናግረው፡፡ በተጋጋለ ስሜት የምታናግረው ከሆነ፣ ወደ ባሰ ችግር ልትገቡ ትችላላችሁ፡፡ እግዚአብሔር ከግለሰቡ ጋር እንድትነጋገር እንደሚፈልግ ካመንክ፣ በቁጣ እየተጋፈጥከው ነው የሚል መልእክት የማያስተላልፍ ምቹ ጊዜ ምረጥ፡፡

6. ተግባርህ ቁጣህን አያሳይ፡፡ ደግ ሰው ሁንለት፡፡ ይህ ሰው ወደ ፊት የቅርብ ጓደኛህ ላይሆን ቢችልም፣ አሉታዊ ስሜቶችህ በሥራዎችህ እንዳይገለጹ አድርግ፡፡ ምንም ዓይነት አንተን የሚጎዳ ነገር እንዳላደረገብህ አድርገህ አስብ፡፡

7. እንድ ሰው ወደ አንተ መጥቶ ስለ ጉዳዩ ለመነጋገር በሚፈልግበት ጊዜ፣ ሁኔታውን አስቸጋሪ ከማድረግ ይልቅ ቀለል ያለ ስሜት እንዲሰማው አድርግ፡፡ አንድ ሰው ኩራቱን ወረድ አድርጎ ኃጢአቱን መናዘዙ በራሱ ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ስለ ሆነም፣ ይቅርታ ለመጠየቅ ሁኔታውን ቀለል ማድረጉ ጠቃሚ ነው፡፡ የዮሴፍ ወንድሞች ለባርነት ስለ ሸጡት የበደለኝነት ስሜት እየተሰማቸው ሳለ፣ እርሱ ግን ይህ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር የነበረ ሁኔታ መሆኑን በመግለጽ የተሻለ ስሜት እንዲሰማቸው አድርጓል፡፡ እኛም ይቅርታ ለመጠየቅ የመጣውን ሰው ስሜት የሚገነባ ጥሩ ነገር መናገር አለብን፡፡ አንተ ይቅር ብለኸዋል፡፡ ነገር ግን እርሱም የይቅርታ ፈውስ ያስፈልገዋል፡፡ በፍቅር ስለ ችግሩ መነጋገር እንዲቀልለው አድርግ፡፡

8. እንድን ሰው ስትጋፍጥ ወይም ራሱ ስለ ጉዳዩ ሲነግርህ፣ ንግግሩ ከሁለታችሁ እንደማይወጣ ግለጽለት፡፡ ምሥጢሩን ለማንም ሰው እንደማታወጣው ግለጽለት፡፡ ብዙ ሰዎች ይቅርታ ከማይጠይቁባቸው ምክንያቶች አንደኛው ምሥጢሩ ወደ ሌሎች ሰ

ዎች እንዳይወጣ መፍራት ነው። ዮሐንስ እንዳለው፣ ሰዎች እንደምትወዳቸው ሲያወቁ አይፈሩም (1ኛ ዮሐ. 4:18)።

9. ሁልጊዜም በተቻለ ፍጥነት ለስሜት መጎዳትና ይቅርታ መፍትሔ ፈልግ። የስሜት መጎዳትና ሥቃይ በልብህ ውስጥ እንዲሰነብት ካደረግክ፣ አንተንም ሆነ ከተቀያየምከው ግለሰብ ጋር ያለህን ግንኙነት እየጎዳ መሄዱ የማይቀር ነው። በዚህ ጊዜ ይቅር ማለቱ አዳጋች ሲሆን ይችላል። ጳውሎስ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ ስለሚል፣ ፈጥነን ይቅርታ ማድረግ አለብን (ኤፌ. 4:26)። በተከሰተው ነገር ላይ ብዙ እንዳይቆይ አእምሮህን መግራት ይኖርብሃል። ይልቁንም፣ ክርስቶስ ኃጢአትህን ይቅር ለማለት የከፈለውን ዕዳ አስታውስ። ያ ሌላውን ሰው ይቅር ማለት እንዲቀልልህ ያደርጋል።

10. ለግለሰቡ ጸልይለት። በማቴዎስ 5:43-48 ኢየሱስ ጠላቶቻችንን እንድንወድና እንድንጸልይላቸው ነግሮናል። ይህ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያሳያል። ለሚበድሉን ሰዎች መጸለይ አለብን። ኢየሱስ ለማለት የፈለገው «ይቅር በለው» ብለን እንድንጸልይ ብቻ አይደለም። በርግጥ ይህንን ማድረግ አለብን። እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው መጸለይ የለብንም። ይህ ሌላው የመበቀል ፍላጎት ነው። ኢየሱስ ጸልዩላቸው ሲል እግዚአብሔር መልካምን ነገር እንዲያደርግላቸው እንድንጠይቅ እየነገረን መሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ለእኛ የሚያደርገው ይህንን አይደለምን? ሰዎች ሁልጊዜም እየበደሉት እርሱ ግን መልካምን ነገር ያደርግላቸዋል። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ እድገታቸው በሚበጅ መንገድ እንዲበርካቸው መጸለይ አለብን። ከኃጢአትና ከበደለኛነት ስሜት እንዲላቀቁ፣ ክርስቶስን ወደ ማወቅ እንዲደርሱ፣ እግዚአብሔር እነርሱንና ቤተሰባቸውን እንዲባርክ፣ ወዘተ. . . መጸለይ አለብን። እግዚአብሔር እንዲረዳቸው በእውነተኛ ልብ መጸለይ መራርነትን ከልባችን ለማራቅ ከሚያስችሉ ምርጥ መላ ዎች አንዱ ነው።



> 39ኛ ጥያቄ፡- አንድ ሰው በጥልቀት እንዴት እንደ ጎዳህ አስታውስ። ከላይ የተገለጹትን የይቅርታ ደረጃዎች ከተመለከትክ በኋላ፣ ያንን ሰው ይቅር ለማለት ምን ማድረግ ይኖርብሃል? አሁኑኑ ጊዜ ወስደህ ግለሰቡን ይቅር በለው። ከተቻለ በፍጥነት ከግለሰቡ ጋር በመነጋገር ለኃጢአትህ ይቅርታ ጠይቀው።

## አንድን ሰው ይቅር በምንልበት ጊዜ ምን ይከሰታል?

1. በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ጣልቃ መግባታችን ይቆማል። መፍረድና መቅጣት የእግዚአብሔር እንጂ የእኛ ሥራ አይደለም (ሮሜ 12:17-19)። በቃላችን ወይም በድርጊታችን ለመበቀል በምንሞክርበት ጊዜ ሁሉ፣ በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ጣልቃ እንገባለን። የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት እየሞከርን ነው ማለት ነው። እኛ እግዚአብሔር ስላልሆንን፣ በእርሱ ሥራ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት መሞከራችንን ማቆም አለብን። በትክክል ሊፈርድ የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

2. ከውስጣችን የመራርነት ስሜት ይወገዳል። ይቅርታ በማናደርግበት ጊዜ የምንጎዳው ራሳችን ነን። የጎዳን ግለሰብ ነገሩን ስለሚረሳው፣ ከመራርነትና ከንዴት ጋር አይታገልም። አንድን ሰው ይቅር በማንልበት ጊዜ፣ መራርነቱ ልክ እንደ አሲድ ልባችንን ይበላዋል። ደስታ አይኖረንም። ግለሰቡ ስለ ፈጸምብን በደልና እኛም ምን ዓይነት የበቀል እርምጃ ልንወስድ እንደምንችል እያሰብን እንቅልፍ እናጣለን። ግለሰቡን ባየን ቁጥር ውስጣችን ይቆጣል። ሳይንቲስቶች እንደሚሉት፣ ይቅር አለማለት ለሆድና ሌሎች ብዙ በሽታዎች ያጋልጣል። መራርነት የሕይወታችንን ክፍሎች ሁሉ ይጎዳል። ከእኛ አልፎም የምንወዳቸውን ሰዎች ይጎዳል። ብዙውን ጊዜ ንዴታችንን በልጆቻችን፣ በባለቤታችን ወይም አብረውን በሚሠሩት ሰዎች ላይ እንገልጻለን። በእግዚአብሔርም ላይ የምንቆጣበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ይቅርታ ባለማድረጋችን ሕይወታችን በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል።

ነገር ግን ይቅርታ ስናደርግ፣ እግዚአብሔር ነገሮችን በራሱ መንገድ እንዲቆጣጠር ስናደርግ፣ እንዲሁም ስለዚህ ጉዳይ ከማሰብ ስንቆጠብ፣ ውስጣዊ ሰላምና ደስታ ይሰማናል።

3. የመንፈስ ቅዱስ ልዩ ኃይል ይለማናል። (ኤፌ. 4:29-32ን አንብብ።) የዚህ ምንባብ ዐውድ እንደሚያሳየው፣ መንፈስ ቅዱስን ከምናሳዝንባቸውና ኃይሉ በሕይወታችን ውስጥ በሚገባ እንዳይገለጽ ከምናደርግባቸው መንገዶች አንዱ ይቅርታ አለማድረግና በቃላት መበቀል ነው። ነገር ግን ይቅርታ ስናደርግና ችግሩን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስንሰጥ፣ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ሕይወታችን ይመለሳል። ምናልባትም የመንፈስ ቅዱስ ኃይል በብዙ መሪዎች ሕይወት ውስጥ ከማይገለጥባቸው ምክንያቶች አንዱ ሰዎችን ይቅር ባለማለታችን ሊሆን ይችላል። በልባችን፣ ቂም እንይዝና መራርነት የሚለማበትን ስፍራ እናመቻቻለን። መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ አይሠራም። መንፈስ ቅዱስ በውስጣችንና በሕይወታችን በኃይል ሊሠራ የሚችለው ይቅር በማለት መራርነትን ስናስወግድ ብቻ ነው።

| |
|---|
| 40ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙውን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሰዎች የሚናደዱባቸውንና የሚማረሩባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) ይህ በመሪዎች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያመጣው እንዴት ነው? ሐ) ይህ ቤተ ክርስቲያንን እንዴት በአሉታዊ መልኩ እንደሚጎዳ ግለጽ። መ) የዚህ ትምህርት እውነታዎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአገልግሎታቸው የተሻሰ ተግባር ሰማከናወን ነጻነት እንዲኖራቸው የሚረዱት እንዴት ነው? ሠ) እነዚህን እውነቶች በቤተ ክርስቲያናችሁ እንዴት ልታስተምር እንደምትችል የሚያሳይ አጭር ዕቅድ አውጣ። |

ለመሪዎች እንድ ተጨማሪ ምክር። እንድ ሰው ትክክል ያልሆነ ወቀሳ በሚሰነዝርብህ ጊዜ፣ ከመናደድ ተቆጠብ። ከዚያ ይልቅ ግለሰቡ የሚናገረውን አሳብ አድምጥ። ግሰሰቡ ወቀሳውን ሊሰነዝርብህ ምን ለማለት እንደ ፈለገ ጠይቀው። የተገለጸውን ችግር እንዴት በሕይወትህ ውስጥ እንደ ተመለከተ ጠይቀው። ንጹሕ ነኝ ብለህ ለመከላከልም ሆነ ማመኻኛዎችን ለማቅረብ አትሞክር። ተናድደህ ግለሰቡን ጥፋተኛ ነህ ማለት የለብህም። የሚቻል ከሆነና ግለሰቡም ለማዳመጥ ፈቃደኛ ከሆነ፣ ስለ ጉዳዩ የራስህን አመለካከትና ምናልባትም ግለሰቡ ያላወቀው ነገር ካለ አብራራለት። መሳሳትህ ግልጽ ከሆነ፣ ስሕተትህን ተቀበል። ነገር ግን ግለሰቡ ለማዳመጥ ካልፈቀደና አንተም ጥፋተኛ እይደለሁም ብለህ የምታምን ከሆነ፣ ራስህን በማዋረድ ወደ እግዚአብሔር ቅረብ። በዚህ ወቀሳ ውስጥ እውነተኛው ነገር ምን እንደ ሆነ እግዚአብሔር እንዲያሳይህ ጠይቀው። በአመዛኙ በብዙ የውሸት ወቀሳዎች ውስጥ ትንሽ እውነት ስለሚኖር፣ ያንን ተመልክቶ የራስን ሕይወት ማስተካከሉ ተገቢ ነው። 90 በመቶው ወቀሳ ውሸት ቢሆን እንኳን፣ እግዚአብሔር ከተቀረችው 10 በመቶ ለእድገትህ የሚበጅ ትምህርት እንዲያስተምርህ ጠይቀው። የተቀረውን ለአንተ ጥቅም እንደሌለው ነገር ቆጥረህ ተወው።



## አምስተኛ ቀን:- ለሳምንታዊ ስብሰባ በመዘጋጀት የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስ።

### ሳምንታዊ ስብሰባ

***የመወያያ ጥያቄዎች:-***

1. በሽማግሌዎች እና በመጋቢው መካከል የተፈጠረን አለመግባባት የሚያሳይ እንድ ድራማ ሥሩ። የሽማግሌዎቹ ሰብሳቢ ሁኔታውን ለመረዳት በሚያስችል መንገድ በማዳመጥ እንዴት ስምምነት ሊፈጥር እንደሚችል በድራማው ውስጥ አሳዩ። ሀ) ችግር ባለባቸው ግንኙነቶች ውስጥ ጥሩ ያልሆነ ተግባቦት የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው? ለ) አምስቱ የማዳመጥ መንገዶች እንዴት በስብሰባ ላይ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ የሚያሳይ ምሳሌ ስጡ። ሐ) ሁኔታውን ለመረዳት በሚያስችል መንገድ ማዳመጥ ችግሩን ሰመፍታት እንዴት ሊያገለግል ይችላል? መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ የምትጋፈጣቸው ሌሎች የግንኙነት ችግሮች ምን ምንድን ናቸው? እግዚአብሔር በማዳመጥ አማካኝነት እንዴት እነዚህን ችግሮች ሊፈታ እንደሚችል ተወያዩ።

2. ሀ) የይፋዊ ተግባቦት ክህሎት ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለምን እንደሚያስፈልግ ግለጽ። ለ) አጠቃላይ የጥሩ ይፋዊ ተግባቦት መርሖዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ እንዴት እንደ ተከናወኑ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ጥቀስ። ሐ) እነዚህ መርሖዎች በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ ይሆኑ ዘንድ ምን ቢደረግ ጥሩ ይሆናል?

3. ሀ) የአምልኮ መሪዎች እንዴት የተሻለ ተግባር ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ግለጽ:: ለ) ማስታወቂያ ተናጋሪዎችስ? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ሰባኪዎች እንዴት የስብከት ችሎታቸውን ሊያሳድጉ እንደሚችሉ ግለጽ:: መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ማስታወቂያ የሚናገሩ ሰዎች የተሻለ ብቃት እንዲኖራቸው ማሠልጠን ያለባት ለምንድን ነው? ሠ) የአምልኮ መሪዎች፣ ማስታወቂያ የሚናገሩ፣ የሚሰብኩና የሚያስተምሩ አገልጋዮች የበለጠ ክህሎት ያለበትን ተ ግባቦት እንዲያካሂዱ ለማስቻል ትምህርት እንዴት ሊሰጣቸው እንደሚገባ የሚያሳይ ዕቅድ አውጣ::

4. ሀ) የቤተ ክርስቲያናችሁ መሪዎች በየጊዜው ከምእመናን ጋር የአሳብ ልውውጥ የሚያካሂዱባቸውን መንገዶች ዘርዝር:: ለ) ይህ የአሳብ ልውውጥ ምን ያህል አጥጋቢ ነው? ሐ) በመሪዎች እና ምእመናን መካከል ግልጽ የአሳብ ልውውጥ በማይኖርበት ጊዜ የሚከሰቱ አሉታዊ ነገሮች ምን ምንድን ናቸው? መ) መሪዎች ከቤተ ክርስቲያን ምእመናን ጋር እንዴት የተሻለ የአሳብ ልውውጥ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ግለጽ::

5. ሀ) ስለ «ይቅርታ» ብዙ አማኞች የሚያስቡትን መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያስተምረው እውነት ጋር አነጻጽር:: ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ስይቅርታ ፈጣኖች መሆናቸው ለምን ያስፈልጋል? ሐ) ይቅር አለማለት ቤተ ክርስቲያንን የጎዳበትን ሁኔታ ግለጽ:: መ) ይቅር አለማለት የቤተ ክርስቲያን መሪውን የግል ሕይወት የጎዳበትን ሁኔታ ግለጽ::



# ትምህርት አሥራ አምስት

## አንደኛ ቀን

ዳዊት የእግዚአብሔር ሕዝብ በአንድነት በሚኖርበት ጊዜ ስለሚገኝ በረከት ጽፎ ነበር (መዝ. 133):: የሚያሳዝነው፣ በታሪክ ሁሉ በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል አንድነት እምብዛም የማይታይ ነገር ሆኖ ቆይቷል:: ቃየል ወንድሙ አቤልን ከገደለበት ጊዜ አንሥቶ፣ ወደ አሳዛኝ ውጤቶች የሚመሩ አለመግባባቶች ሲከሰቱ መኖራቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል:: ስለ ዮሴፍና ወንድሞቹ፣ ዳዊትና ንጉሥ ሳኦል፣ ጳውሎስና በርናባስ፣ ጴጥሮስና ጳውሎስ (ገላ. 2)፣ እንዲሁም የግሪክ አይሁዶችና ከይሁዳ አይሁዶች ጋር አለመስማማታቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ (የሐዋ. 6):: የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በበኩሉ የቤተ ክርስቲያን መሪ ዎችና ምእመናን የተጣሉባቸው፣ የተከፋፈሉባቸውና አዳዲስ ቤተ አምነቶችን የፈጠሩባቸው፣ ወዘተ. . . ሁኔታዎች መኖራቸውን ይነግረናል:: ይህ ዛሬም ሳይቀር የምንመለከተው እውነት ነው:: በደርግ ዘመን በብዙ የቤተ ክርስቲያን ቤተ አምነቶች መካከል ሰላም የነበረ ሲሆን፣ አሁን በነጻነት ጊዜ ግን በመሪዎች፣ በመሪዎችና በምእመናን፣ እንዲሁም በምእመናን የእርስ በርስ ግንኙነት መካከል እምብዛም አንድነት አይታይም::

> 1ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስለተከሰተውና አሉታዊ ውጤቶችን ስላመጣው አንድ አለመግባባት ግለጽ:: ለ) አለመግባባቱ የተ ጀመረው ከመሪዎች ነበር ወይስ ከምእመናን? ሐ) ችግሩ እንዴት ነበር የተፈታው? በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ወይስ በዓለማዊ መንገድ? መልስህን አብራራ::

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን መጠን፣ አለመግባባቶች አይቀሬ ጉዳዮች መሆናቸውን መረዳት አለብን:: ከሰ ዎች ትዕቢት የተነሣ ሁልጊዜም አለመግባባቶች መፈጠራቸው የማይቀር ነገር ነው:: ከዚህም የተነሣ ሰዎች እርስ በርሳቸው ይጣላሉ:: ከቤተሰቦቻችን ጋር አለመግባባት የምንፈጥርባቸው ጊዜ ያት እንደሚኖሩ ሁሉ፣ ከቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ከምእመናንም

ጋር አለመግባባቶችን ልንፈጥር እንችላለን:: ከተለያዩ ጎሳዎች ወይም ቤተ እምነቶች የሚመጡ ውጥረቶችም ሊገጥሙን ይችላሉ:: በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አለመግባባቶችንና ግጭቶችን በክርስቲያናዊ መንገድ እንዴት በፍጥነት ማስተካከል እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው::

2ኛ ጥያቄ:- ማቴ. 5:9፤ ዮሐ. 17:20-23፤ ፊልጵ. 1:27-2:11፤ ያዕ. 4:1-3 አንብብ:: ሀ) ኢየሱስ ብሩክ ነው ያለው ማንን ነው? ለ) ኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ምን እንዲኖራቸው ጸለየ? ሐ) ይህ ለዓለም ያላቸውን ምስክርነት በተመለከተ ምን ዓይነት ውጤት ያስከትላል አለ? መ) ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ምን እንድትመስል አዘዘ? ሠ) ይህ ይሆን ዘንድ ምእመናን ምን ዓይነት ባሕርይ እንዲኖራቸው ተናገረ? ረ) ጳውሎስ አንድነትን ለመጠበቅ በምሳሌነት የጠቀሰው ማንን ነው? ሰ) ኢየሱስ አለመግባባትን የሚፈጥረው ምን ዓይነት ባሕርይ ነው አለ?

## እግዚአብሔር ልጆቹ በአንድነት እንዲኖሩ ይፈልጋል::

እጅግ መራራ ጸቦች የሚፈጠሩት ብዙውን ጊዜ በቤተሰብ ውስጥ ነው:: በአመዛኙ ከቤተሰባችን ውጭ ካሉት ሰዎች ጋር በቀላሉ በሰላም መኖር የሚቻል ይመስለናል:: ነገር ግን በቤተሰብ ውስጥ ጸብ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ በአብዛኛው የመረረና መፍትሔ ለመስጠት የሚያስቸግር ሆኖ ይገኛል:: በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥም ሁኔታው ተመሳሳይ ነው:: እንደ አማኞች፣ ሁላችንም የእግዚአብሔር አባታችን ልጆች ነን:: ከክርስቶስ ጋር ወንድም ነን:: በመሆኑም፣ ሁላችንም አንድ ቤተሰብ ነን:: እዚህ ላይ የመጣንበት ጎሳ፣ ጾታችን፣ የትምህርትና የኢኮኖሚ ደረጃችን ለውጥ ሊያመጣ አይገባም:: አማኞች ሁሉ የአንድ ታላቅ ቤተሰብ አባላት ናቸው:: ይሁን እንጂ፣ ከክርስቲያኖች በላይ ከማያምኑ ሰዎች ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ያለን ይመስላል:: አማኞች በሚጣሉበት ጊዜ፣ በአመዛኙ ክፍፍሉ የከፋ ስለሚሆን፣ እርቅን መፍጠር አስቸጋሪ ይሆናል::

እግዚአብሔር ክርስቲያኖች አስታራቂዎች እንዲሆኑ ቢጠይቅም፣ በአመዛኙ ክፍፍልን የምንፈጥረው እኛው ነን:: በወንጌላት ውስጥ የምናገኘው የክርስቶስ የመጨረሻው ጸሎት አማኞች አንድ እንዲሆኑ የሚጠይቅ ነው:: እንዲያውም ለዓለም



ትልቁ ምስክርነታችን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት በመሆናችን ባለን አንድነት እጅግ ደስ መሰኘታችን ሊሆን ይገባ ነበር:: ጳውሎስ አማኞች አንድ አሳብ፣ አንድ መንፈስና አንድ ዓላማ እንዲኖራቸው አዝዟል:: የክርስቶስን ምሳሌነት በመጠቀም እንዴት በአንድነት ልንኖር እንደምንችል አስተምሯል:: ይህ አንድነት የሚመጣው ግን መብቶቻችንን ስንተውና ለሌላው ሰው ቅድሚያ በመስጠት ስናገለግለው ብቻ ነው:: ያዕቆብ የአንድነት ጠላት ራስ-ወዳድነት እንደ ሆነ ገልጾአል:: ይህም ከሌሎች ፍላጎቶች ይልቅ ለራሳችን ፍላጎት ማሰብ ነው:: በመሆኑም፣ እንደ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ተባብሮ በመኖሩ ላይ ትኩረት ልናደርግ ይገባል:: በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ክፍፍል መፈጠሩ የእርሱ ፈቃድ አይደለም:: እርሱ ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ከዚህ ክፍፍል ውስጥ ጥሩ ነገሮችን ሊፈጥር ይችላል:: ነገር ግን ይህ ከልጆቹ የሚፈልገው ነገር አይደለም::

## የተለያዩ ያለመግባባት ዓይነቶችን መለየት::

ሁሉም አለመግባባቶች ስሕተት ናቸውን? አይደሉም:: ትክክል ብቻ ሳይሆኑ፣ የግድ መደረግ ያለባቸው አለመግባባቶች አሉ:: በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ለመኖር ከፈለግን፣ የተለያዩ ያለመግባባትና የክፍፍል ዓይነቶችን ልንረዳና እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ዓይነት አለመግባባት የሚሰጠውን ምላሽ ልናውቅ ይገባል::

1. ከባሕርይ ወይም ከባህል መጣረስ የሚመጡ አለመግባባቶችና ክፍፍሎች::

ባሕርያቸው ከእኛ በመለየቱ ምክንያት፣ ሳያውቁ፣ ግጭት የሚፈጥሩ ሰዎች አሉ:: ብዙ የሚናገሩና ጭምት በሆኑ ሰዎች ላይ እምብዛም የማያስደስት ስሜት የሚፈጥሩ ሰዎች አሉ:: አንዳንዶች ደግሞ በጣም ድብቅ በመሆናቸው ልናውቃቸው እንቸገራለን:: አንዳንድ ሰዎችን በቀላሉ ልንወዳቸውና ወዳጅነትን ልንመሠርት እንችላለን:: ከሌሎች ጋር ጓደኝነት ስመመሥረትም ሆነ አብረናቸው ለመሆን ልንቸገር እንችላለን::

3ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የባሕርይ ልዩነት በአንተና በሌላ ሰው መካከል ውጥረትን ሲፈጥር የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ይህ ልዩነት ምን ዓይነት ችግሮችን አስከተለ? ሐ) ያህንን ችግር እንዴት አስወገድክ?

እግዚአብሔር የተለያዩ ሰዎችን ፈጥሯል። እኛም በእነርሱ ወይም በባሕርያቸው ከመበሳጨት ይልቅ ልዩነታቸውን ማድነቅ መቻል አለብን። ከእኛ የተለየ ባሕርይ ካላቸው ሰዎች ጋር ለመጣጣም ስንቸገርና እነዚህ ልዩነቶች አንድነታችንን እንዲያናጉ ስናደርግ፣ የተለያዩ ሰዎችን ከፈጠረው አምላክ ጋር እየተጣላን ነው ማለት ነው።

በባሕርዩ ምክንያት ከሰው ጋር በምንጣላበት ጊዜ፣ የሚከተሉትን እውነቶች መረዳት አለብን፦

ሀ. እነርሱም የእግዚአብሔር ቤተሰብ እንደ ሆኑና በክርስቶስ ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን እንደ ሆኑ።

ለ. የተለያዩ ባሕርያት ያሏቸው ሰዎች ለእኛ አስፈላጊዎች መሆናቸውን። እነዚህ ሰዎች ደካማ ጎኖቻችንን ስለሚያሳዩና በመንፈሳዊ ሕይወታችን በየትኞቹ ጉዳዮች ላይ ማደግ እንዳለብን እናውቃለን። ወይም ደግሞ የእኛን ባሕርይ ሚዛናዊ በማድረግ ያለብንን ድክመት የሚያሸንፍ ባሕርይ ይኖራቸዋል።

ሐ. በማስተዋልና በፍቅር እነርሱ የሚያደርጓቸውንና እኛን የሚረብሹንን ነገሮች በመንገር (አብረውን በሚሆኑበት ጊዜ) እነዚህን ነገሮች እንዲያስወግዱ ወይም እንዲቀንሱ ልናበረታታቸው እንችላለን።

መ. ግለሰቡንና ልዩ ባሕርዩን ለመቀበል ራሳችንን ልንገራ እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቅር የግለሰቡን ባሕርይ በማንወድበት ጊዜ እንኳን እንድንቀበለው ያዝዘናል።

በሰዎች መካከል የባሕርይ ልዩነት እንዳለ ሁሉ፣ በባህላዊ ልምምዶችም ልዩነቶች አሉ። ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች አብረው ሲኖሩና ሲሠሩ፣ ልዩነቶቻቸው በአብዛኛው ነገሮችን በተሳሳተ መንገድ መረዳትንና ግጭትን ያመጣሉ። በባህሎች ውስጥ የእሴቶች ልዩነት አለ። አንዳንድ ሰዎች (ኢትዮጵያውያን) ከሰዎች ጋር ጊዜ ማሳለፍ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ (ምዕራባውያን) ልክ በሰዓቱ ከሥራ ቦታ ላይ መድረስ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። አንዳንዶች የቤተሰብ አንድነት አስፈላጊ እንደ ሆነ ሲያስቡ፣ ሌሎች ደግሞ ነጻነትንና ተነሣሽነትን ማክበር አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። አንዳንዶች የሰዎች ስሜት እንዳይጎዳ ለመከላከል እውነትን መደበቅ አስፈላጊ ነው ብለው ሲያስቡ፣ ሌሎች ግን እውነትን መናገር አንድ ሰው በባሕርዩ እንዲያድግ ስለሚያደርግ አስፈላጊ ነው ብለው ያምናሉ። ሌላው ክፍፍልን የሚፈጥረው ነገር ብዙ ባህላዊ ቡድኖች በታሪካቸው የተቀላቀሉባቸው ነገሮች በመራቸው ምክንያት ዛሬ ላይ ጥሩ ግንኙነቶችን ለመመሥረት እስከማይችሉ ድረስ የሚጠራጠሩና የሚጠላሉ መሆናቸው ነው።

የባህል ክፍተቱ በሰፋ ቁጥር፣ በአሳብ የመተሳሰፍ ዕድሉም እየበዛ ይሄዳል። ለምሳሌ፣ በኢትዮጵያውያንና በምዕራባውያን ባህሎች መካከል ሰፊ ክፍተት አለ። ይህም ብዙውን ጊዜ ለሁለቱም ቡድኖች ችግሮችን ይፈጥራል። በኢትዮጵያውያን ባህል ድርጅቶች የሚመሩት በጠንካራ የሥራ መሪዎች ነው። እነዚህ መሪዎች ለሠራተኞቹ ምንም ዓይነት ነጻነት ሳይሰጡ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ያዝዟቸዋል። የምዕራቡ ዓለም ባህል ግን የራስ ተነሣሽነትን ያበረታታል። አንድ የምዕራቡ ዓለም ሰው አሳቡ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ፣ ሥራውን የሚያከናውነው በራሱ ኃላፊነት ነው። በመሆኑም፣ ምዕራባውያን ሚሲዮናውያን ከኢትዮጵያውያን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጋር አብረው በሚሠሩበት ጊዜ፣ በግለሰቦች ሚና ላይ የተለያዩ አቋሞችን ስለሚይዙ ለመግባባት ይቸገራሉ።

4ኛ ጥያቄ፦ የተለያዩ ጎሳዊ ልማዶች በክርስቲያኖች መካከል ግጭት ሲፈጥሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) የተለያዩ ባህላዊ ልማዶች ወይም ባሕርያት ግጭቶችን ሲፈጥሩ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ።

5ኛ ጥያቄ፦ የሐዋ. 15:36-41ን አንብብ። ሀ) ጳውሎስ እና በርናባስ እንዲጋጩ ያደረገው ምንድን ነበር? ለ) ያጠፋው ማን ነበር? ትክክለኛ

ውስ? መልስህን አብራራ። ሐ) እግዚአብሔር ከእነርሱ አለመግባባት ያፈለቀው መልካም ነገር ምን ነበር? መ) 1ኛ ቆሮ. 9:6፣ 2ኛ ጢሞ. 4:11 አንብብ። እነዚህ ጥቅሶች ክርስቲያኖች አለመግባባታቸውን ሊያሸንፉ እንደሚችሉ የሚያሳዩት እንዴት ነው?

2. በተለያዩ የሥራ ማከናወኛ መንገዶች ላይ የሚያተኩሩ አለመግባባቶችና ክፍፍሎች።

አንዳንድ ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ደካማ የሆኑ ሰዎች ብቻ በአንድ አሳብ ከመስማማት ይቆጠባሉ ብለን እናስባለን። እውነቱ ግን የመንፈሳዊነት ደረጃቸው ምንም ያህል ቢሆን፣ ሁሉም አማኞች አንዳንድ ጊዜ የማይስማሙባቸው ነገሮች መኖራቸው ነው። በአማኞች መካከል የሚፈጠር አንድነት የወንጌሉ እምብርትና ክርስቶስ የሚፈልገው ትልቁ ነገር ስለሆነ፣ ሰይጣን በዚህ ላይ በከፍተኛ ደረጃ ማተኮሩ የማይቀር ነው። ሁለተኛውና መንፈሳዊ የሆኑ አማኞች ሳይቀር በአንድ ጉዳይ የማይስማሙበት ምክንያት በአንድ ጉዳይ ላይ የተለየ አሳብ ስላላቸው ነው። ምንም ያህል ብናውቅ፣ ሁላችንም ሰዎች ስለሆንን፣ ሁሉንም ነገር ልናውቅ አንችልም። ምርጥ የሚባሉ ፍርዶቻችን እንከን የማይለያቸው ናቸው። የሌሎች ሰዎችን ልባዊ ፍላጎትና ተግባር ሙሉ በሙሉ በትክክል አንረዳም። የራሳችን ልባዊ ዓላማዎችም ቢሆኑ ሁልጊዜም ንጹሕ ላይሆኑ ይችላሉ። ሁሉንም ነገር ስለማናውቅ፣ የተለዩ ገጠመኞችና ግንዛቤዎች ስላሉን፣ ሁልጊዜም ነገሮችን በተለያዩ መንገዶች እንመለከታለን። የተለያዩ አመለካከቶች፣ የተለያዩ ግቦችና የተለያዩ ተሞክሮዎች ወደ ተለያዩ ማጠቃለያዎች ይመሩናል። ነገሮችን በተለያዩ መንገዶች ስለምንመለከት፣ በአሳብ ልንለያይ እንችላለን። ክርስቲያኖች በአንድ ነገር በአሳብ በሚለያዩበት ጊዜ፣ ሁለቱም ወገኖች ለያዙት አቋም በመረጃነት የሚያቀርቧቸው ጥሩ ጥሩ ምክንያቶች ይኖሯቸዋል። እንደ መሪዎች፣ መንፈሳዊ ብስለት ባላቸው አማኞች መካከል እንኳን የአሠራር ልዩነቶች የአሳብ ልዩነቶችን እንደሚያስከትሉ መረዳት አለብን።

በሐዋርያት ሥራ 15:36-41 ውስጥ፣ ሁለት መንፈሳዊ መሪ ዎች፣ ማለትም በርናባስና ጳውሎስ በአንድ አሳብ ተለያይተው



ነበር። ሁለቱም ለወንጌል መልእክተኛነት አገልግሎት ለመውጣት ፈልገው ነበር። ነገር ግን የቡድኑ አባላት እነማን ይሁኑ? በሚለው ጥያቄ ላይ የተለያየ አመለካከት ነበራቸው። ሰዎችን ማበረታታት የሚወደው በርናባስ (የስሙ ትርጉም «የመጽናናት ልጅ» መሆኑ ይታወሳል) ዮሐንስ ማርቆስን ለመውሰድ ፈለገ። ምንም እንኳን ዮሐንስ ማርቆስ በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ ላይ በርናባስን እና ጳውሎስን በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ጥሎ የተመለሰ ቢሆንም፣ በርናባስ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁለተኛ ዕድል እንደሚሰጣቸው ስለሚያውቅ፣ ለዮሐንስ ማርቆስ ይህንኑ ለማድረግ ፈለገ። ዮሐንስ «የውዳቂነት» ስሜት እንዲሰማው አልፈለገም ነበር። በርናባስ በዘመዱ ላይ ማተኮሩና እርሱን መምረጡ ትክክል ላይሆን ይችላል። ዮሐንስ የአክስቱ ልጅ ነበር። ጳውሎስ ደግሞ ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ፣ አንድ የቡድኑ አባል ትቶ መመለሱ ለቡድኑ ሥነ-ምግባር ምን ዓይነት መልእክት እንደሚያስተላልፍ ያውቅ ነበር። ዮሐንስ ከስደት ነበር የሸሸው። በእንዲህ ዓይነት ወሳኝ ጉዞ ላይ ዮሐንስ ዳግም ጥንካሬውን የሚያሳይበትን ዕድል መስጠቱ ከባድ ነበር። (ለምሳሌ፣ በደርግ መንግሥት ጊዜ እምነቱን የካደን ሰው እንደገና ማመን ምን ያህል እንደሚከብድ አስብ።) በመሆኑም፣ ጳወሎስ ዮሐንስ የቡድኑ አባል እንዲሆን አልፈለገም ነበር። ነገር ግን ጳውሎስ ሰዎች ሊያስቡ ወይም በብስለት ሊያድጉ አይችሉም ከሚል ድምዳሜ መድረሱ ስሕተት ነበር። የሚያሳዝነው፣ የሁለቱ መንፈሳዊ ሰዎች ትዕቢት ተከፋፍለው በተ ለያዩ መንገዶች ለአገልግሎት እንዲወጡ አደረጋቸው። ከዚያ በኋላ አብረው ለመሥራት አልቻሉም።

አንዳንድ ምሁራን በበርናባስ እና ጳውሎስ አለመስማማት ውስጥ ሌላም ነገር እንደ ነበረ ይገምታሉ። ጳውሎስ የመሪነቱን ሚና መጫወት መጀመሩ በርናባስን አስከፍቶት ሊሆን ይችላል ሲሉ ይገምታሉ። በመጀመሪያው የወንጌል ጉዞ ወቅት ቀዳሚው መሪ በርናባስ ነበር። (መጽሐፍ ቅዱስ በርናባስና ሳውል ይላል። [የሐዋ. 13:2፣ 7])። ከዚያ በኋላ ግን በትንሹ እስያ ውስጥ ጳውሎስ መሪነቱን ተረከበ። (መጽሐፍ ቅዱስ ጳውሎስና በርናባስ ይላል

[የሐዋ. 13:42-0]):: ጳውሎስም በርናባስ ከጴጥሮስ ጋር በመሆን በገላትያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአይሁዶችና አሕዛብ መካከል ክፍፍል እንዲፈጠር በማድረጉ ላይቀየም የቀረ አይመስልም (ገላ. 2:13)::

እንዲሁም ምሁራን ሁለቱ ሰዎች በወንጌላዊ ጉዞ ውስጥ የተለያዩ ግቦች እንደ ነበሯቸው ይናገራሉ:: ምናልባትም በርናባስ በአይሁዶችና በአገሩ ቆጵሮስ ላይ ትኩረት ለማድረግ ሳይፈልግ የቀረ አይመስልም:: ጳውሎስ ግን በትንሹ እስያና በአውሮጳ ውስጥ ያሉትን አሕዛብ የማገልገል ፍላጎት ነበረው:: በዚህ ጉዳይ ላይ ትክክል የሆነውና ያልሆነው የአሠራር ስልት የትኛው ነው? ሁለቱም የአሠራር ስልቶች በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሲሆኑ፣ የተለያዩ መንገዶች ናቸው:: በርናባስና ጳውሎስ የተለያዩ ጥሪዎችና ስጦታዎች ነበሯቸው:: ወንጌል ለአይሁዶችም ለአሕዛብም ያስፈልጋል:: የአሠራር ስልቶች በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ከፍተኛ ውጥረቶችን ያስከትላሉ:: ለምሳሌ፣ ሁለት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል ለማካፈልና አማኞችን ለማስተማር ሲፈልጉ ይችላሉ:: ነገር ግን ይህንን ተግባር ለማከናወን የሚጠቀሙባቸው ስልቶች የተለያዩ በመሆናቸውና እነዚህን የተለያዩ ስልቶች ለማዋሃድ ባለመቻላቸው ተጣልተው ይለያያሉ::

ስለዚህ፣ አንድን ተግባር በማከናወኑ ረገድ ሳንስማማ ስንቀርና ወደ አንድ መፍትሔ ለመድረስ በማንችልበት ጊዜ ምን ማድረግ አለብን? ከጳውሎስና በርናባስ ታሪክ የሚከተሉትን ነጥቦች ልንማር እንችላለን:-

ሀ. ሁለቱንም ወገኖች የሚያስማማ ዘለቄታዊ መንገድ በማይኖርበት ጊዜ፣ በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ያለው ጊዜያዊ መፍትሔ መፈለጉ ጠቃሚ ነው:: ጳውሎስና በርናባስ የየራሳቸውን መንገድ መከተላቸው ፍጹም ትክክለኛ የሆነ መፍትሔ አልነበረም:: የአሳብ ልዩነቶቻቸውን አስወግደው አብረው ሲሠሩ ይችሉ ነበር:: በብዙ ሁኔታዎች ሰዎች በማይስማሙበት ጊዜ፣ «ላለመስማማት መስማማታቸው» በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: ሁለቱም ወገኖች



እንደ መረዳታቸው የሚኖሩበትን ጊዜያዊና ያልተሟላ መፍትሔ መፈለጉ ተገቢ ነው:: ጳውሎስና በርናባስ በተለያዩ መንገዶች ለአገልግሎት በመሰማራታቸው ስሜታቸውን ለማቀዝቀዝና የበለጠ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ለማሰብ ጊዜ አግኝተዋል:: ፍጹም ባልሆነች ዓለማችን ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ፍጹም ያልሆኑ መፍትሔዎችን ማግኘቱ ጠቃሚ ነው:: አንድ ሰው ለሌላኛው ሰው ዕቅዶች የግድ መገዛት ሳይኖርበት ሁለት የተለያዩ የአሠራር ስልቶችን ማዘጋጀቱ ጠቃሚ የሚሆንበት ጊዜ አለ::

ለ. ምንም እንኳን የአጭር ጊዜ ዕቅድ አንዳንድ ጊዜ አስፈላጊ ቢሆንም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለተፈጠረው አለመስማማት ዘላቂ የሆነ መፍትሔ ቢፈልጉ መልካም ነው:: ለአጭር ጊዜ የሚበጅ መፍትሔ በመፈለጋቸው ምክንያት የጳውሎስና በርናባስ ጸብ ረግቧል:: ሁለት ቡድኖች ወደ ብዙ ስፍራዎች ለመሄድ በመቻላቸው ወንጌሉን የማሰራጨቱ ሥራ ቀጥሏል:: ነገር ግን ጳውሎስም ሆነ በርናባስ በመለያየታቸው ደስተኞች የነበሩ መሆናቸው አጠራጣሪ ነገር ነው:: በመሆኑም፣ ጊዜ የስሜት መጎዳታቸውን ሲፈውስና ስሜታቸው ሲቀዘቅዝ ሁለቱ ሰዎች አዲስ ግንኙነት ለመፍጠር ችለዋል:: ብዙም ሳይቆይ ጳውሎስ በርናባስን አመስግነው (1ኛ ቆሮ. 9:6):: ዮሐንስ ማርቆስም ከጳውሎስ የቅርብ ጓደኞች አንዱ ለመሆን በቃ:: ጳውሎስ የሚሞትበት ጊዜ ሲቃረብ፣ በመጨረሻዎቹ ጊዜያት ዮሐንስ ማርቆስ አብሮት እንዲሆን ጠይቋል (2ኛ ጢሞ. 4:11)::

በመሆኑም፣ መሪዎችም ሆኑ አብያተ ክርስቲያናት ለጊዜው ለማስታረቅ የሚያስቸግር ጉዳይ ገጥሟቸው ቢለያዩ፣ በዚያው ረክተው ሲቀመጡ አይገባም:: ለክርስቶስ እርቀ ሰላም ከፍተኛ ትርጉም እንደሚሰጠው በመረዳት ወደ ይቅርታና እርቅ የሚመጡበትን መንገድ መፈለግ አለባቸው:: ምናልባትም በጸብ ምክንያት ወደ ሌላ ቤተ እምነት የገባ መሪ መመለስ ላያስፈልገው ይችላል:: ወይም ደግሞ በአሳብ ልዩነት ምክንያት አንድን አካባቢ ለቅቆ የሄደ ወንጌላዊ ወደዚያው ስፍራ መመለስ ላያስፈልገው ይችላል:: ወይም ደግሞ ከሽማግሌዎች ጋር ለመስማማት ባለመቻ

ሉ ምክንያት የራሱን አገልግሎት የጀመረ አገልጋይ ወደ በፊት አገልግሎቱ መመለስ ላያስፈልገው ይችላል፡፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እነዚህ ግለሰቦች ይቅር ለመባባል ሊፈልጉ ይገባል፡፡ ይህም ሰይጣን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማዳከም ቀጣይነት ያለው ክፍፍል እንዳይፈጥር የሚያደርግ መልካም ተግባር ነው፡፡

| |
|---|
| ፩ኛ ጥያቄ፡- ሀ) አንድን ተግባር ማካሄድን በተመለከተ የሚፈጠር የአሠራር ልዩነት በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል ውጥረት ሊፈጥር የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ፡፡ ለ) የአሳብ ልዩነቱ እንዴት እንደ ተፈታ አብራራ፡፡ |

በዚህ ታሪክ ውስጥ ስለ ጳውሎስና በርናባስ ሌላ ጠቃሚ እውነት እንመለከታለን፡፡ ምንም እንኳን አንዳንድ አለመስማማቶች ጎጂ ሊሆኑ ቢችሉም፣ የሥራ ክንውኖችን በተመለከተ የሚነሡትን አብዛኞቹን አለመስማማቶች እግዚአብሔር በመቆጣጠር ወደ መልካም ነገር ሊመልስ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር በጳውሎስና በርናባስ መካከል የተፈጠረውን አለመግባባት መንግሥቱን ለማስፋፋት ተጠቅሞበታል፡፡ በፊት አንድ ብቻ የነበረው የወንጌል መልእክተኞች ቡድን አሁን ወደ ሁለት ክፍ ሊል ቻለ፡፡ እምቅ ኃይላቸውን ለመጠቀም ያልቻሉ እንደ ሲላስና ጢሞቴዎስ ያሉ ሰዎች በአገልግሎት ለመሰማራት ቻሉ፡፡ ሉቃስ በጳውሎስ ላይ ትኩረት ስላደረገ፣ የማርቆስና የበርናባስ አገልግሎት የት እንደ ደረሰ ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ዛሬም እግዚአብሔር መሪዎች ባለመስማማታቸው ምክንያት አዲስ ቤተ ክርስቲያን በሚመሠርቱበት ጊዜ፣ ከአንድ ይልቅ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ይኖሩናል፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 4፡7 ጳውሎስ የወንጌሉ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ወይም በደካማና ኃጢአተኛ የሰው ልጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ ይናገራል፡፡ ይህም ሆኖ አሁንም ወንጌሉ ወደ ፊት እየተጓዘ ቤተ ክርስቲያን ታድጋለች፡፡ ይህ ሁላችንም ራሳችንን ዝቅ እንድናደርግ ያደርገናል፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እድገት በራሱ በእግዚአብሔር ላይ እንጂ በእኛ ላይ አይደገፍምና፡፡

ምንም እንኳ የአሠራር ስልትን የሚመለከቱ የተለያዩ አሳቦች ቢኖሩም፣ ልባችን መራራ እንዳይሆንና የጠላትነትን መንፈስ



እንዳያዳብር መጠንቀቅ አለብን፡፡ ችግሩ ያለው ካለመስማማቱ ላይ ሳይሆን፣ ለተፈጠረው አለመስማማት በምንሰጠው ምላሽ ላይ ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ ወይም ውሳኔ ላይ የአሳብ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ሁልጊዜም ምርጥ የሆነ መፍትሔ ለማግኘት መጣር አለብን፡፡ ነገር ግን ልባችንን ከንዴትና በተፈጠረው ችግር ከመበሳጨት መጠበቅ አለብን፡፡ ልዩነቱን ምክንያት በማድረግ መከፋፈልን ለመፍጠር ወይም ሌሎችንና ቤተ ክርስቲያንን ለማጥፋት መጣር የለብንም፡፡ በቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ ጉዳት የሚያደርሰው ሰዎች የአሳብ ልዩነት ፈጥረው የየራሳቸውን መንገድ በመሄዳቸው ምክንያት አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ችግር የሚፈጠረው መሪዎች እርስ በርሳቸው የመራርነትን ስሜት ሲያዳብሩና አንዱ የሌላውን ሥራ ለማዳከም ሊጥር ወይም ደግሞ አብያተ ክርስቲያናት መጣላታቸውን ሲቀጥሉ ነው፡፡

ዛሬም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ራእይ ወይም ዓላማ ላይ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡ ይህ ልክ ጳውሎስና በርናባስ በሮም ግዛት ላሉት ሰዎች ወንጌልን ለማዳረስ ከተስማሙበት ሁኔታ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ ነገር ግን መሪዎች ይህንኑ ዓላማ እንዴት እናሳካው? በሚለው ጉዳይ ላይ ላይስማሙ ይችላሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ከልባቸው የሚስማሙበትን ዕቅድ አብረው ለማውጣት ካልቻሉ፣ ሥራውን ለማከናወን አንዱ የሌላውን ዕቅድ እንዲከተል ከማስገደድ ይልቅ፣ እያንዳንዳቸው እግዚአብሔር ስልባቸው የሚናገረውን እንዲያደርጉ መፍቀዱ የተሻለ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁልጊዜም አብረው እግዚአብሔርን ሊያገለግሉ የሚችሉባቸውን መንገዶች መፈለጋቸውን መቀጠል አለባቸው፡፡ እንዲሁም ደግሞ አንዱ በሌላው ላይ መጥፎ ስሜት ሊኖረው አይገባም፡፡ ከዚህ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ሁለቱንም የአሠራር መንገዶች በመጠቀም መንግሥቱን እያስፋፋ በመሆኑ የአመስጋኝነት ስሜት ሊሰማቸው ይገባል፡፡

| |
|---|
| ፯ኛ ጥያቄ፡- 1ኛ ቆሮ. 5፡1-5ን አንብብ፡፡ ሀ) በዚህ ጊዜ አለመግባባቱ እንዲፈጠር ያደረገው መንሥኤ ምን ነበር? ለ) የዚህ ዓይነቱ አለመግባባት ትክክል ይመስልሃል ወይስ ስሕተት? ሐ) በቤተ ክርስቲያናችሁ የዚህ ዓይነቱን አለመግባባት የተመለከትክበትን ሁኔታ በምሳሌነት ጥቀስ፡፡ ውጤቱ ምን ነበር? ማቴ. 18፡15-20ን አንብብ፡፡ ከኃጢአት የሚመጡትን ችግሮች እንዴት እንደምንፈታ የሚገልጸውን አሳብ በአስተዋጽኦ መልክ አስፍር፡፡ |

3. በኃጢአት ምክንያት በሰዎች ሕይወት ውስጥ የሚፈጠሩ አለመስማማቶችና ክፍፍል።

ኃጢአት አለመግባባትን የሚፈጥርባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ቤተ ክርስቲያንን መመልከት አስገራሚ ነገር ነው። በባሕርይ ልዩነቶች ወይም በአሠራር መንገድና የአስተሳሰብ ልዩነቶች ላይ በጣም ስለምንጣላ፣ በኃጢአት ምክንያት የሚፈጠሩትን ልዩነቶች ንቀን እናልፋለን። ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በመካከላችን ያለውን ኃጢአት ቸል እንላለን። ኃጢአትን አናጋልጥም፣ ንስሐ አንገባም፣ ይቅርታም አናደርግም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኃጢአትን ከምሽጋችን ተግተን እንድናርቅ ያስጠነቅቀናል። ሳሙኤል ሳኦልን (1ኛ ሳሙ. 13:1-14)፣ ናታን ዳዊትን (1ኛ ሳሙ. 12)፣ እንዲሁም ኤልያስ አክአብን (1ኛ ነገሥ. 18) ተጋፍጠዋል። በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5፣ ጳውሎስ ኃጢአትን በመጋፈጡ ምክንያት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር አለመግባባትን ፈጥሯል። የቆሮንቶስ ሰዎች ኃጢአትን አላንሰው በመመልከት በታጋሽነታቸው ሲኩራሩ፣ ጳውሎስ ግን ፊት ለፊት ተቃውሟቸዋል። ኃጢአትን በማጋለጥ ኃጢአተኛውን በቅጣት መልክ ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት አስወጥቷል። ነገር ግን በ2ኛ ቆሮንቶስ 2:1-11 ኃጢአተኛው ንስሐ በሚገባበት ጊዜ፣ ሙሉ በሙሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት እንዲመልሱት ነግሯቸዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞች በሚኖሩበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች «ሰላምን» እናደፈርሳለን ብለው መፍራት የለባቸውም። ትንሹ እርሾ ሊጡን ሁሉ እንደሚያቦካ ሁሉ ንስሐ ያልተገባበትና ያልተቀጣ ኃጢአት ብዙም ሳይቆይ ጠቅላላይቱን ቤተ ክርስቲያን መበከሉ የማይቀር ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞች በሚኖሩበት ጊዜ እንድናጋፍጣቸው እግዚአብሔር «ያዝዘናል» እንላለን። ያ ኃጢአት በምእመናን ወይም በመሪዎች ሕይወት ውስጥ የሚታይ ሊሆን ይችላል። ይህ ለእግዚአብሔር ልዩነት አይፈጥርም። ዋናው ቁም ነገር ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት መቀጣት አለበት። ይሁንና፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኃጢአት



የሚቀጣው ለመጉዳት ሳይሆን፣ ለመጥቀም በማሰብ ነው። (ዕብ. 12:5-11ን አንብብ።) የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ንስሐ ያልገቡ ኃጢአተኞች በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጽሙት በደል ከባድ መሆኑን በመረዳት ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲፈጥሩ የሚያደርግ ነው።

8ኛ ጥያቄ፡- ሐር. 23:9-32፤ 28:1-17፤ ገላ. 2:11-14፤ 2ኛ ጢሞ. 4:1-8ን አንብብ። ሀ) በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የተጠቀሱት ምን ዓይነት ግጭቶች ናቸው? ለ) እነዚህ አስፈላጊ ግጭቶች የሚሆኑት ለምንድን ነው? ሐ) በቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት ግጭቶችን ስለ ተመለከትክበት ሁኔታ ግለጽ። መ) ቤተ ክርስቲያናችሁ ችግሩን የፈታቸው እንዴት ነበር?

4. በአስተምህሮዊ ጉዳዮች የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና የአሳብ ክፍፍል፡-

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በመረዳቱ ላይ የተለያዩ አመለካከቶች በሚፈጠሩበት ጊዜም ልዩነቱን እንዴት እንደሚያስተናግዱ ለማወቅ ይቸገራሉ። አብዛኞቹ ቤተ አምነቶች የሚከፋፈሉት አንድም ጠንካራ ሽብእና ያለው መሪ ስለሚጫናቸው፣ አሊያም ጠቃሚ ባልሆኑ አስተምህሮዎች ምክንያት ነው።

በአስተምህሮዎች ምክንያት የሚከሰቱ አለመግባባቶች ሁለት ዓይነት ደረጃዎች ይኖራቸዋል። በመጀመሪያ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ያልተብራሩ አስተምህሮዎች አሉ። በዚህ ጊዜ የትኛው ወገን የሚያቀርበው አሳብ ትክክል እንደሚሆን መወሰኑ አስቸጋሪ ነው። (ለምሳሌ፣ ስለ መጨረሻው ዘመን የሚነሡ አመለካከቶች፣ የሕጻናት ጥምቀት፣ ውኃ በመርጨት ማጥመቅ፣ በልሳን መናገር የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምልክት ስለ መሆኑ፣ ወዘተ . . .) መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የራሳችንን ትርጉም መስጠት ቢኖርብንና ተመሳሳይ አሳብ ያላቸው አማኞች በአንድነት ኅብረት መፍጠራቸው ተቀባይነት ያለው ነገር ቢሆንም፣ በትናንሽ ጉዳዮች ላይ የሚኖሩን አስተምህሮዊ ልዩነቶች በክርስቲያኖች መሐል ክፍተኛ ክፍፍል እንዲፈጥሩ ማድረግ የለብንም።

<u>ሁለተኛ</u>፣ የወንጌሉ እምብርት የሆኑ አንዳንድ አስተምህሮዎች አሉ:: በእነዚህ አስኳል አስተምህሮዎች ላይ የአሳብ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ ግን፣ አማኞች የሐሰት ትምህርቱን በግልጽ መገዳደር አለባቸው:: በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከእውነተኞቹ አስተማሪዎች ጎን ለጎን ውሸትን የሚያስተምሩ ሰዎች እንደ ነበሩ እንመለከታለን:: መንፈሳዊ ሰዎች ዝም ብለው በመመልከት ሐሰተኛ አስተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዲያስፋፉ ሊፈቅዱላቸው ይገባል የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የለም:: እንዲያውም ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በመጋፈጥ እውነትን ጠብቀው እንዲያቆዩ ታዝዘዋል:: (የሐዋ. 20:27-31ን አንብብ::)

የሚየሳዝነው፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ተመሥርተው ሐሰተኛ አስተማሪዎችን በግልጽ ሲጋፈጡ እንመለከትም:: አብዛኞቻችን ለእውነት ከመታገል ይልቅ በሰላም ለመኖር እንፈልጋለን:: ይህንን በማድረጋችን ደግሞ፣ የሐሰት ትምህርት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲስፋፋ እንፈቅዳለን:: የጳውሎስን አገልግሎት በምንመለከትበት ጊዜ፣ ጴጥሮስ በአስተምህሮውና በባሕርዩ ስሕተት በፈጠረ ጊዜ በሕዝብ ፊት ተጋፍጦታል:: የጴጥሮስ ተግባራት ወደ ተሳሳተ የደኅንነት ግንዛቤ በማምራት የክርስቶስን አካል አንድነት ሊያናጋ ይችል ነበር:: ጳውሎስ መዳን በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም ለሚለው የወንጌሉ እምብርት ነበር የተከራከረው:: ይህ በጳውሎስና ጴጥሮስ መካከል የተከሰተ የግል አለመግባባት ሳይሆን፣ የቤተ ክርስቲያንን የወደፊት ሕይወትና የሕዝቡን መዳን የሚመለከት ነው:: እነዚህ ሁለት ታላላቅ አገልጋዮች መጣላታቸው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ውዝግብ ሊፈጥር ይችል ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር ለጴጥሮስ ስሕተቱን በማሳየቱ፣ ጴጥሮስ ሰዎች የጳውሎስን መልእክቶች ከብሉይ ኪዳን እኩል እንዲቀበሉ ነግሮአቸዋል (2ኛ ጴጥ. 3:15-16)::

9ኛ ጥያቄ:- ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአነስተኛ አስተምህሮዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ክርክር ሲያደርጉ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ይህ በቤተ ክርስቲያን ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት ምን ነበር? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በቤተ ክርስቲያን ዐበይት አስተምህሮዎች ላይ



ጥቃት የሚሰነዝሩ ትምህርቶችን የሚያስፋፉትን ሐሰተኛ አስተማሪዎች ሲታገሡ የተመለከትክበትን ሁኔታ ግለጽ:: ይህ በብዙ ምእመናን ላይ ያስከተለው አሉታዊ ውጤት ምንድን ነበር?

## አብዛኞቹ አለመግባባቶች ገንቢ የማይሆኑት ለምንድን ነው?

አለመግባባት በራሱ መጥፎ ነገር አይደለም:: የተለያዩ አመለካከቶችና ውይይቶች መካሄዳቸው ጥሩ ውሳኔ ለመስጠት ወሳኝ ስለሆነ፣ በነገሮች ላይ የተለያዩ አመለካከቶችን መያዝ ጤናማ ነው:: ኃጢአትንና ሐሰተኛ ትምህርትን በግልጽ መጋፈጥም ትክክል ነው:: ነገር ግን አለመግባባትን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ በማናስተናግድበት ጊዜ፣ ወደ መጥፎ አዝማሚያ ሊመራን ይችላል::

10ኛ ጥያቄ:- ያዕ. 4:1-3ን አንብብ:: ሀ) ያዕቆብ ብዙውን ጊዜ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጣሉት ለምንድን ነው ይላል? ለ) ይህ እውነት መሆኑን የተመለከትክበትን ሁኔታ ተናገር::

ከኃጢአት ተፈጥሮ የሚመጣውን ራስ ወዳድነት መቆጣጠር ብንችል፣ ብዙ አለመግባባቶች ወደ መራራ ጸብ አይለወጡም ነበር:: በፍጥነት ነገሮችን በመመልከት ፍትሐዊና ትክክለኛ ፍርድ ልንሰጥ እንችል ነበር:: መከራር ሳያስፈልገን የሌሎች ሰዎች አመለካከት ትክክል መሆኑን አምነን ልንቀበል እንችል ነበር:: ነገር ግን ሁላችንም የኃጢአት ተፈጥሮ አለን:: ይህ የኃጢአት ተፈጥሮ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ የምንወስዳቸውን እርምጃዎች ይቆጣጠርብናል:: በገላትያ 5:20 ጳውሎስ የኃጢአት ተፈጥሯችን *«ጥላቻን፣ ጠብን፣ ቅንአትን፣ ቁጣን፣ ራስ ወዳድነትን፣ መለያየትን፣ አድመኝነትንና ምቀኝነትን»* እንደሚፈጥር ገልጾአል:: እግዚአብሔር ምርጥ ዳኛ የሚሆንበት ምክንያት ከእኛ ጉዳይ ለራሱ ጥቅም የሚፈልገው ነገር ባለመኖሩ ነው:: እርሱ ሁልጊዜም ትክክለኛና ፍትሐዊ አምላክ ነው:: እኛም እንደ እግዚአብሔር የማናዳላና በተወሰነች ሰብአዊ ግንዛቤያችን ምርጥ ውሳኔዎችን ለመስጠት ከፈለግን፣ የኃጢአት ተፈጥሮአችንን በመቆጣጠር አከራካሪ ነገሮችን እርስ በርሳችን ፍልሚያ የምናካሂድበት የጦር

ሜዳ ከማድረግ ልንቆጠብ ይገባል:: ለመሆኑ ጎጂ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ለምንድን ነው?

1. በትዕቢት ስሜት ከሁሉም የሚሻለውን እናውቃለን ብለን እናስባለን:: ይህ ሁሉም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከሚጋፈጧቸው አደጋዎች አንዱ ነው:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ በልቡ ውስጥ ትዕቢት በሚያድርበት ጊዜ፣ ከእኔ ሌላ ለአሳር የሚል አመለካከት ስለሚኖረው፣ የሌሎች ሰዎችን አሳብ የመቀበል ፍላጎት አይኖረውም:: አስቀድሞ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥና የማንንም አሳብ ላለመስማት ይወስናል:: የሌሎችን መሳሳት ለማሳየት ሥልጣኑንና ትምህርቱን በመከታነት ይጠቀማል:: ይህ በተለይ ብዙ ትምህርትና የሥነ-መለኮት እውቀት ባላቸው መሪዎች ላይ የሚታይ ችግር ነው:: እኛ ከሁሉም የተሻለ እውቀት አለን ብለን ስለምናስብ፣ የሌሎች ሰዎችን አሳብ ለመቀበል እንቸገራለን::

2. ሰዎች አሳባችንን በማይቀበሉበት ጊዜ ስሜታችን ይጎዳል፣ እንናደዳለን:: ብዙውን ጊዜ አሳባችን የራሳችን ክፍል ነው ብለን እናስባለን:: ከዚህም የተነሣ፣ በአሳባችን ላይ የሚሰነዘሩትን ተቃውሞዎች በእኛ ላይ እንደ ተሰነዘሩ ጥቃቶች እንቆጥራለን:: በመሆኑም ክፍፍል ከሚከሰትባቸው ምክንያቶች አንዱ የአሳብ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ ሰዎች ጥቃት እንደ ተቃጣባቸው በመገመት «የመልስ ምት» ለመሰንዘር (አጸፋውን ለመመለስ) ስለሚፈልጉ ነው:: በእንጻሩ ትሑት የሆነ ሰው የራሱን ዝናና ክብር ለመጠበቅ አይሞክርም:: እርሱን የሚያሳስበው እውነትና ነገሮች ለእግዚአብሔር ክብር መከናወናቸው ነው:: ስለሆነም፣ ሰዎች አሳቡን በማይቀበሉ ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ከሁሉም በተሻለ መንገድ የሚያስፋፋ ውሳኔ እንዲሰጥ ከመፈለግ ያለፈ ፍላጎት አይኖረውም:: ትሑት ሰው ሰዎች አሳቡን በማይቀበሉበት ጊዜ ሊያጠቁኝ ፈልገው ነው የሚል ግምት አይኖረውም::

3. የሌሎች ሰዎችን ድብቅ ልባዊ ፍላጎት እናያለን ብለን እናስባለን:: በአመዛኙ መሪዎች እርስ በርሳቸው በሚነጋገሩበት ጊዜ፣ ከሰው ቃላት በስተጀርባ ያለውን ልባዊ ፍላጎት ለመገመት ይሞክራሉ:: ይህም የሚሆነው እርስ በርሳቸው ስለማይተማመኑ ነው:: የሰዎችን ድብቅ ልባዊ ፍላጎት የመፍረዱ ኃጢአት ሰዎች የሚናገሩትን ቃላት አምነን እንዳንቀበል ያደርገናል (ማቴ. 7:1-5):: ሁልጊዜም ድብቅ የሆነውን ነገር እንፈልጋለን:: ፈልገን ሳናገኝ ስንቀር ደግሞ፣ መጥፎ ነገር መሆን አለበት ብለን እንገምታለን:: ሰዎች የሆነ መጥፎ ልባዊ ፍላጎት በመፈለጋቸው ምክንያት ፊት ለፊት የሚነገራቸውን አሳብ ስለማይቀበሉ፣ ብዙ አለመግባባቶች ይፈጠራሉ::

4. በራስ ወዳድነታችን ምክንያት ከሚሰጠው ውሳኔ ጥቅም ለማግኘት እንፈልጋለን:: ብዙውን ጊዜ በስብሰባ ላይ በምንሆንበት ጊዜ፣ «ከዚህ ውሳኔ ለራሴ፣ ለቤተሰቤ ወይም ለቤተ ክርስቲያኔ ምን ዓይነት ጥቅም ላገኝ እችላለሁ?» ብለን እናስባለን:: ይህ የራስ ወዳድነት ፍላጎት በምንወያይባቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ጥላውን ስለሚያሳርፍ፣ ቤተ ክርስቲያናችንን አይጠቅምም ብለን የምናስበውን ነገር ሁሉ እንቃወማለን:: እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሳይሆን፣ የራሳችንን መንግሥት እንደምንፈልግ የሚያሳይ ነው:: ጥሩ ውሳኔ ልንሰጥ የምንችለው ስለሌሎች ሰዎችና ለችግሮቻቸው ስናስብ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለውን ስናስብ ነው::

ይህ የራስ ወዳድነት አስተሳሰብ ሰዎች ውሳኔዎች እነርሱን በሚጠቅም መንገድ እንዲወሰኑ በመፈለጋቸው ምክንያት የሚከሰት ነው:: ወይም ደግሞ ይህ የቡድኖች (ማለትም የጎሳዎች፣ የቤተ ክርስቲያናት፣ የቀጣና ቤተ ክርስቲያን) ጥቅም ጉዳይ ሊሆን ይችላል:: በእንግሊዝኛ «ለመጣላት ሁለት ሰው መሆን ያስፈልጋል» የሚል አባባል አለ:: በአመዛኙ ጠንካራ አለመግባባት ካለ፣ በሁለቱም ወገን ችግሮች አሉ ማለት ነው:: የትኛውም ወገን ለመስማት ፈቃደኛ አይሆንም:: የራሳችንን አመለካከት ለማብራራትና መልስ ለመስጠት ብቻ ስለምንፈልግ፣ ሌላኛው ቡድን የራሱን አሳብ በሚያብራራበት ጊዜ ለመስማት እንሻም:: ለአንድ «ትክክለኛ» ለሆነ ነገር እየተጣላን ነው ብለን በምናስብበት ጊዜ ሳይቀር፣ የራስ ወዳድነትን ባሕርይ እናካትታለን:: በሰዎች መካከል ከንጹሕ ልብ የፈለቁ ብዙ አለመግባባቶች **እምብዛም**

አይከሰቱም። በአመዛኙ እነዚህ አለመግባባቶች የራስ ወዳድነት ውጤቶች ናቸው።

11ኛ ጥያቄ፡- ከሰው ጋር አለመግባባት ውስጥ የገባህበትን ሁኔታ አስታውስ። አለመግባባቱ የተፈጠረው ከላይ ከተዘረዘሩት አራት ምክንያቶች በየትኛው መንሥኤነት ነበር?

## ከአለመግባባት አሉታዊ ውጤቶች አንዳንዶቹ፡-

1. በቡድኖቹ ልብ ውስጥ የሚፈጠረው መራርነት ክፍፍሉ እንዲቀጥል ያደርገዋል (ዕብ. 12፡14-15ን አንብብ)።

ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ አለመግባባቶች ከሚያስከትሏቸው ነገሮች አንዱ አለመግባባቶቹ ውስጥ በገቡት ሰዎች ልብ ውስጥ መራርነት እንዲፈጠር ማድረግ ነው። አለመግባባቱ ሳይፈታ በቆየ መጠን፣ መራርነቱ ይበልጥ ሥር እየሰደደ ይሄዳል። ማደግ በሚጀምርበት ጊዜ ደግሞ፣ ልክ እንደ ባህር ዛፍ ሥሩን አጥልቆ ወደ ውስጥ ስለሚሰድ፣ ለመላቀቅ አዳጋች ይሆናል። በሌላ ሰው ወይም ቡድን ላይ ልባችን መራራ በሚሆንበት ጊዜ፣ ተጎጂው ማን ነው? በቀዳሚነት የሚጎዳው ሌላው ሰው ወይም ቡድን ሳይሆን፣ ራሳችን ነን። ልባችን በንዴት ይሞላና ደስታ ይርቀናል። ለሥቃይ ስላጋለጠን ሁኔታ እያሰብን እንቅልፍ-አልባ ሌሊቶች እናሳልፋለን። በሚፈጠረው ምስቅልቅል ሁኔታ ሳቢያ ከምንወዳቸው ሰዎች (ከሚስታችን፣ ከልጆቻችንና ከጓደኞቻችን) ጋር ጥሩ ግንኙነት ሳይኖረን ይቀራል። ስለሆነም፣ ሌላኛው ቡድን በደንቦቹና በተግባሮቹ ብቻ አይደለም የሚጎዳን፣ መራርነታችን ራሱ በጠለቀ መንገድ ይጎዳናል። በሕይወታችን በአንድ ጉዳይ ላይ ደስታና መራርነት ሊኖረን አይችልም።

2. በሥራችን ውጤታማ እንሆንም (መክ. 4፡9-12ን አንብብ)።

ሰሎሞን ክፍፍል በሚፈጠርበት ጊዜ የሚፈጠረውን ሁኔታ ለመግለጽ መኝታን በምሳሌነት ይጠቀማል። አንድ ሰው ብቻውን ቢተኛ ይበርደዋል፣ ሁለቱ አብረው ቢተኙ ግን ይሞቃቸዋል። በአንድ የተገመደ ገመድ በቀላሉ ይበጠሳል፣ በሁለት ወይም በሦስት



ሰበዞች የተገመደ ገመድ ግን በቀላሉ አይበጠስም። ውጤታማ አገልግሎት ለማካሄድ የእግዚአብሔር ሕዝብ አብረው መሥራት አለባቸው። ክፍፍል እንዲፈጠር በምናደርግበት ጊዜ፣ ውጤታማነታችን የሚቀንስባቸው ቢያንስ ሦስት መንገዶች አሉ፡-

ሀ. አብረን ስለማናቅድና አብረን ስለማንሠራ፣ የእግዚአብሔር ሥራ የሚገባውን ያህል ውጤታማ ሳይሆን ይቀራል። የሚገርመው ነገር ሰዎች አብረው በሚሠሩበት ጊዜ፣ ለብቻቸው ከሚያከናውኑት የበለጠ ውጤታማ ተግባር ይፈጽማሉ። ስለሆነም፣ ሰዎች በአንድነት እንዳይሠሩ የሚያደርግ ክፍፍል በሚኖርበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔርን ሥራ እንደሚገባው ውጤታማ አድርገን ልናከናውን አንችልም።

ለ. የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን ልንጠቀምበት የምንችለውን ጊዜ እናባክናለን። ሥራ የሚበዛባቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የተጣሉትን ሰዎች ለማስታረቅ በመጣር ውድ ጊዜያቸውን ያባክናሉ። በስብሰባዎች ላይም እንዴት እግዚአብሔርን ማገልገል እንደሚቻል ማሰብ ሲገባን፣ እርቅን ለማምጣት ስንጥር እንቆያለን። እንዲሁም ደግሞ አለመግባባት በሚኖርበት ጊዜ፣ የተለያዩ ቡድኖች የራሳቸውን የራስ ወዳድነት መንገድ ስለሚከተሉ፣ ከስምምነት ላይ መድረስ አይቻልም። በአብያተ ክርስቲያኖቻችን ለእግዚአብሔር መንግሥት ከመሥራት ይልቅ የተጣሉ ወገኖችን ለማስታረቅ ብዙ ጊዜ በመውሰድ ላይ ነን። ግጭቶችን እንዴት እንደምንፈታ በመወያየት የምናጠፋው ጊዜ ወንጌልን እንዴት ላልዳኑ ሰዎች እንደምናዳርስ በመወያየት ከምናሳልፈው የበዛ ነው። ሰይጣን ጊዜያችንንና ሌሎች ሀብቶችን በመጠቀም ወንጌሉን ከማስፋፋት ይልቅ አንድነትን ለማምጣት ስንጥር እንድንኖር አድርጎናል።

ሐ. የእግዚአብሔርን ሀብት እናባክናለን። ያለንን ሀብት በማስተባበር አብረን መሥራት ስንችል፣ አንድን ተግባር ለማከናወን በየፊናችን ገንዘብ ለማውጣት እንገደዳለን። ለምሳሌ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን የሚያሠለጥን አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መክፈት ሲቻል፣ እያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን

አካባቢ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ለማሠልጠን የየራሱን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመክፈት ይገደዳል:: የዚህም ውጤቱ እግዚአብሔርን የሚያስከብር አንድ ጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከመክፈት ይልቅ ብዙ ደካማ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶችን መክፈት ይሆናል:: ወይም ደግሞ የተ ጣሉትን ቡድኖች ለማስታረቅ ያለችንን አነስተኛ ገንዘብ እናባክናለን:: መሪዎች አብረው ለመሥራት ባለመስማማታቸውና ለየብቻቸው ለመሥራት በመምረጣቸው፣ በየዓመቱ በሺዎች የሚቆጠር ብር በድግግሞሽ ሥራዎች ምክንያት ይባክናል::

3. የክርስቶስን እና የቤተ ክርስቲያናችንን ስም እናሰድባለን (ሮሜ 2:24ን አንብብ)::

በዚህ ምንባብ ጳውሎስ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በማይኖሩ አይሁዶች ባሕርይና ተግባር ምክንያት *«የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል እንደሚሰደብ»* ገልጾአል:: ግልጽና መራራ ክፍፍል በመካከላችን በሚኖርበት ጊዜ፣ የምንጎዳው ራሳችንን ብቻ አይደለም:: የክርስቶስንም ስም እናሰድባለን:: ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት እንፈልጋለን እንላለን:: በየእሑዱ ሰዎች በክርስቶስ እንዲያምኑ እንመሰክራለን:: በእርሱ ካመኑ እርሱ ችግሮቻቸውን ሁሉ እንደሚፈታላቸው እንነግራቸዋለን:: ይህንን እየተናገርን ሳለ በጸብ ውስጥ ስንሆን፣ ተግባራችን የሚያስተላልፈው መልእክት ክርስቶስ ክፍፍልን እንጂ ሰላምን እንደማያመጣ ነው:: የዚህ ዓይነቱ ተግባር ቤተ ክርስቲያናችንንም ያሰድባል:: ሰዎች፣ «ያች ቤተ ክርስቲያን እንደዚያ ዓይነት ከሆነች፣ ወደዚያ ድርሽ አልልም:: ከእኛ የከፉ አይደሉም እንዴ?» ማለታቸው የማይቀር ነው:: አንድ ጊዜ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ከአንድ የመንግሥት ባለ ሥልጣን ጋር ይነጋገር ነበር:: እርሱም፣ «እኛ የመንግሥት መሪዎች እናንተ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የወደፊት ተስፋዎች ናችሁ ብለን እናምናለን:: ቀጥተኛ ሰዎች በመሆናችሁ እንዴት በታማኝነት መኖር እንዳለብን ልታሳዩን ትችላላችሁ፣:: ሰላም ወዳዶች በመሆናችሁም ጎሳዎቻችን እንዴት አብረው እንደሚሠሩ ልታሳዩአቸው ትችላላችሁ» ብሎ ነበር:: ከብዙ ወራት በኋላ



ደራሲው ወደዚሁ ባለ ሥልጣን እንደገና ሄደ:: በዚህ ጊዜ የባለ ሥልጣኑ አመለካከት ከበፊቱ የተለየ ነበር:: «እናንተ ወንጌላውያን ከእኛ የከፋችሁ ናችሁ:: ክርስቶስ በተለያዩ ጎሳዎች መካከል ሰላምን ያመጣል ትላላችሁ:: ነገር ግን በየእሑዱ ጸብ ስለምትፈጥሩ፣ የተ ለያዩ ጎሳዎች እርስ በርሳቸው እንዳይጨፋጨፉ በማሰብ ፖሊስ ለመመደብ ተገድደናል:: በፍርድ ቤቶቻችንም የቤተ ክርስቲያናት ክስ እየበዛ መጥቷል:: እናንተ ለአገራችን የማትጠቅሙ ናችሁ፣» አለ:: ወንድሞቼና እኅቶቼ ሆይ፣ የእኛ ስም ቢጠፋ ምንም አይደለም:: የቤተ ክርስቲያናችንም ስም ቢጠፋ ምንም አይደለም:: ነገር ግን በምንም ዓይነት የክርስቶስ ስም መሰደብ የለበትም! ይህ በአሕዛብ መካከል ሊከበር የሚገባው ስም ነው:: (ሚልክ. 1:14ን አንብቡ::)

12ኛ ጥያቄ፡- ከተመለከትካቸው አለመግባባቶች እነዚህ ሦስቱም ዓይነት አለመግባባቶች እንዴት በቤተ ክርስቲያናችሁ ላይ ጉዳት እንዳደረሱ ግለጽ::

## ሁለተኛ ቀን

### በአሳብ ልዩነት ወይም በአሠራር ልዩነት ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ለመቆጣጠር የሚያግዙ አጠቃላይ መርሖዎች:-

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሚጋፈጧቸው አብዛኞቹ አለመግባባቶች መጋፈጥ ያለብንን ኃጢአት ወይም የሐሰት ትምህርት የሚመለከቱ አይደሉም:: ነገር ግን፣ እነዚህ የባህልና የባሕርይ ወይም የአሠራር ስልትና የአመለካከት ልዩነቶች የፈጠሯቸው አለመግባባቶች ናቸው:: የክርስቶስ ተከታዮች እንደ መሆናችን፣ ግጭቶችን ማስተናገድ እንድንችል የሚያግዙን መርሖ ዎች ምንድን ናቸው?

1. ሁሉም የአሳብ ልዩነቶች መጥፎ አለመሆናቸውን መረዳት:: በማንኛውም ጉዳይ ላይ ጥሩ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው፣ የተለያዩ አሳቦች ቀርበው ሲስተናገዱ ነው:: የተለያዩ ሰዎች አንድን ጉዳይ የሚረዱት በአንድ መንገድ ብቻ ከሆነ፣ ምናልባትም በጥልቀት አላሰቡበትም ይሆናል:: ከጅማ ወደ አዲስ አበባ ለመድረስ በተለያዩ

መንገዶች መምጣት እንደሚቻል ሁሉ፣ ለአንድ ጉዳይም መፍትሔ ለመስጠት በአብዛኛው የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ይቻላል:: ምርጥ ውሳኔ መስጠት የሚቻለው፣ ሰዎች የተለያዩ አሳቦችን ሲሰነዝሩ ነው:: ንጉሥ ሰሎሞን እንደ ተናገረውና ብረት ብረትን እንደሚስል ሁሉ፣ አንደኛው ሰው ሌላኛውን መሳል አለበት (ምሳሌ 27:17):: ምርጥ መፍትሔ የሚመጣው በተሰያዩ አሳቦች ላይ በመወያየት ነው::

ነገር ግን የማንም ሰው ስሜት በማይጎዳበት መንገድ ሰዎች ያለመስማማት ነጻነት እንዲኖራቸው፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አሳባቸውን ለሰዎች አስመለሎ ከማቅረብ መነጠል አለባቸው:: ሰው ምን ይለኛል በሚል ስሜት የልባችንን ገልጠን ለመናገር የምንቸገር ፈሪዎች ከሆንን፣ ብዙውን ጊዜ አሳባችንን ከማንነታችን ጋር እንቀላቅለዋለን:: በመሆኑም፣ ሰዎች ከአሳባችን ጋር በማይስማሙበት ጊዜ፣ አይወዱንም ማለት ነው ብለን እናስባለን:: ይህ ግን እውነት አይደለም:: ሰዎች ከአሳባችን ጋር ባይስማሙም፣ ሊያከብሩንና እንደ ሰው ሊያደንቁን ይችላሉ:: ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ ሰዎች አሳባቸውን በማይቀበሉበት ጊዜ መከፋት የለባቸውም:: እንዲያውም፣ የተለያዩ አሳቦች ቀርበው ከተ ከራከርን በኋላ ጥሩ ውሳኔ መስጠት እንደሚቻል ስለምናውቅ፣ ሰ ዎች ከእኛ የተለየ አሳብ እንዲያቀርቡ ማበረታታት ይኖርብናል:: ነገር ግን በአሳብ አለመስማማቱ ወይም እውነትን መናገሩ ከፍቅር መንፈስ ያልታለየ መሆን እንዳለበት እርግጠኞች ልንሆን ይገባል:: (ኤፌ. 4:15ን አንብብ::) ሰዎች አሳባቸውን በማንቀበልበት ጊዜ እንኳን እንደምንወዳቸውና እንደምናከብራቸው ማወቅ አለባቸው::

13ኛ ጥያቄ:- ዘኍል. 32፣ ኢያሱ 22:11-34ን አንብብ:: ሀ) በእነዚህ ሁኔታ ዎች ውስጥ አለመግባባቱን የፈጠረው ምንድን ነበር? ለ) ይህ ተመሳሳይ የግጭት ምክንያት በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ መቼ እንደሚታይ የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ስጥ:: ሐ) ክርስቶስ በማቴ. 7:1-2 ምን ትእዛዝ ሰጠ? ይህ ትእዛዝ ግጭቶችን እንዴት የሚለውጥ ይመስልሃል?

2. በክርስቲያኖች መካከል ብዙ አለመግባባቶች የሚፈጠሩት ሰ ዎች የሰውን ባሕርይ፣ ልባዊ ፍላጎት፣ ወይም ተግባር በተመለከተ



ግምታዊ አሳብ ስለሚሰነዝሩ ነው:: ይህ በተለይ መተማመን በማይኖርበት ጊዜ የሚፈጠር ችግር ነው:: አንድን ሰው ወይም ቡድን በማናምንበት ጊዜ፣ ከንግግራቸው ውስጥ የሆነ አሉታዊ ነገር እናገኛለን:: እውነት የሆነውን ነገር በርግጠኝነት ከማወቃችን በፊት ፍርድ እንሰጣለን:: ኢየሱስ በሰው ላይ አትፍረዱ ሲለን (ማቴ. 7:1-5)፣ ከግለሰቡ በላይ እናውቃለን እንዳንል ወይም አንድን ነገር ያደረገው በመጥፎ ልባዊ ፍላጎት ነው ብለን እንዳናስብ ማስጠንቀቁ ነበር:: አንድ ሰው አንድን ነገር የሚናገረው ከመጥፎ ልባዊ ፍላጎት ተነሥቶ ነው ብለን በምናስብበት ጊዜ፣ ብዙውን ጊዜ ግምታችን የተሳሳተ ይሆናል:: እርሱም ደግሞ እኛ በምንናገርበት ጊዜ ስለ ልባዊ አስተሳሰባችን ግምታዊ ግንዛቤ መያዝ ይጀምራል:: እንዲያውም፣ የግለሰቡን ልብ ሳናውቅ ልባዊ ፍላጎቱን በምንገምትበት ጊዜ፣ ከምንጠራጠረው ግለሰብ የበለጠ ኃጢአት እየሠራን ልንሆን እንችላለን:: በኢያሱ 22:11-34 መሪዎች ስለ አንድ ቡድን ተግባራት ግምታዊ አሳብ በመሰንዘራቸው እስራኤ ላውያን የእርስ በርስ ጦርነት ለመጀመር ተቃርበው ነበር:: አንዱ ቡድኑ የሌላውን ልባዊ ፍላጎት ወይም ተግባር በመጠራጠሩ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእርስ በርስ ጦርነት የምንፈጥርባቸው ጊዜያት ምንኛ ብዙ ናቸው?

14ኛ ጥያቄ:- ሀ) አንድ ሰው ልባዊ ፍላጎትህን ወይም ተግባርህን በተሳሳተ መንገድ የተረዳበት ጊዜ አጋጥሞህ ያውቃል? ከሆነ፣ ሁኔታው ምን ይመስል እንደ ነበረ ግለጽ:: ለ) ሰዎች አሳብህን ወይም ተግባርህን በተ ሳሳተ መንገድ መረዳታቸው በራስህ፣ በቤተሰብህና በቤተ ክርስቲያናችሁ ላይ ያስከተለው አደገኛ ሁኔታ ምን ነበር? ሐ) ያንን የተሳሳተ ግንዛቤ እንዴት ልታቃና ቻልክ?

የሰይጣን መሣሪያ በመሆን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክፍፍል መፍጠር ካልፈለግን፣ አምስት ነገሮችን ማስታወስ አለብን:-

ሀ. አንድ ጥፋት መፈጸሙን የሚያሳይ የተረጋገጠ ማስረጃ እስከሌለህ ድረስ በምንም ዓይነት የአንድን ሰው ልባዊ ፍላጎቶች ወይም ተግባራት አትጠራጠር:: ጳውሎስ እንዳለው፣ ማስረጃው ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች የሚገኙበት ጠንካራ መሆን አለበት::

(1ኛ ጢሞ. 5:19-20 አንብብ።) እርግጠኛ ለመሆን በማትችልበት ጊዜ፣ ግለሰቡ ንጹሕ ልባዊ ፍላጎት እንዳለው ወይም ትክክል ነው ብሎ በሚያምነው መሠረት ተግባሩን እያከናወነ ነው ብለህ አስብ።

ለ. ሌሎች ሰዎች ወይም ሽማግሌዎች በአንድ ነገር እርግጠኛ ስለሆኑ ብቻ የእነርሱን አሳብ ተቀብለህ ማስተጋባት የለብህም። አብዛኞቹ ሰዎች ውሳኔዎችን የሚሰጡት በቂ መረጃ ሳይይዙ ነው። የሆነ ወሬ እንደ ሰሙ፣ ግለሰቡን ማውገዝ ይጀምራሉ። አንተ ግን የዚህ ዓይነቱ ኃጢአት ተካፋይ መሆን የለብህም።

ሐ. ንግግርህን ተቆጣጠር። ስለ አንድ ሰው በሚቀርብ ሐሜት ላይ ተሳታፊ አትሁን። ይልቁንም፣ ሰዎች ቆም ብለው እንዲያስቡና የተጣራ መረጃ ለማግኘት እንዲሞክሩ ንገራቸው።

መ. ምንም ዓይነት እርምጃ ከመውሰድህ በፊት ክሱን በጥንቃቄ መርምር። በፍጥነት ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ ግጭቶች ብዙ አይደሉም። ኢያሱ ለምን አንዳንድ አይሁዶች መሠዊያ እንደ ሠሩ ለማጣራት ሰዎችን እንደ ላከ ሁሉ፣ አንተም ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት ጊዜ ውሰድ። በጉዳዩ ላይ አንድ አቋም ከመያዝህ በፊት፣ ኢየሱስ በማቴዎስ 5:23-24 እና በማቴዎስ 18:15-17 የሰጠውን ትምህርት ተከተል።

ሠ. ግለሰቡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባልሆነ መንገድ ወይም ምክንያት አንድ ጥፋት እንደ ፈጸመ እርግጠኛ በምትሆንበት ጊዜ፣ በገርነት ተጋፈጠው። ሰሎሞን ለስላሳ ቃላት ቁጣን ያቀዘቅዛል ብሏል (ምሳሌ 15:1)። ግለሰቡ ላይ ወቀሳ በሚሰነዘርበት ጊዜ፣ አይሆንም ብሎ መከላከሉ የማይቀር ነው። እውነት መሆኑን ልቡ ቢያውቀውም። ነገር ግን ስለ ጉዳዩ በገርነት ብታወያየውና ባትከራከረው፣ ወይም ስሜታዊ ባትሆን፣ ችግሩ በቀላሉ ሊወገድ ይችላል።

| |
|---|
| **15ኛ** ጥያቄ፦ ዘፍጥ. 13ን አንብብ። ሀ) በዚህ ስፍራ የተፈጠረውን ግጭት ግለጽ። ለ) ግጭቶችን ስለ መፍታት ከአብርሃም ምሳሌ ምን እንማራለን? |

**3.** አንድ ግጭት መመለሻ የሌለው ችግር ከማስከተሉ በፊት፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተቻለ ፍጥነት ችግሩን ለመፍታት



መጣር አለባቸው። ብዙውን ጊዜ ዝም ብለን የምንጠብቅ ወይም ችግሩን ቸል የምንል ከሆነ፣ እየከፋ ይሄዳል። ግጭቶች በራሳቸው ጊዜ የሚረግቡት እምብዛም ነው። ከላይ በተመለከተው የዘፍጥረት ታሪክ ውስጥ አብርሃምና የወንድሙ ልጅ ሎጥ በግንኙነታቸው ላይ ከፍተኛ ጠባሳ ሊጥል የሚችል ግጭት ፈጥረው ነበር። ከዚህ ታሪ ክ ግጭቶችን ስለ መፍታት የሚከተሉትን ነገሮች ልንማር እንችላለን፦

ሀ. ግጭቶችን ወዲያውኑ እንደ ተከሰቱ መፍታት። ችግሩ በራሱ ጊዜ ይፈታል ብለህ አትጠብቅ። አብርሃም ስለ ችግሩ በሰማ ጊዜ፣ ለግጭቱ መፍትሔ ፈልጓል። ችግሩን ሳይፈታ ቢቆይ ኖሮ፣ ምናልባትም ግጭቱ በአብርሃምና በሎጥ መካከል ሲካረርና በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ሊያዳግታቸው ይችል ነበር።

ለ. በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አማራጭ አለ ብለህ እመን። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ሁኔታ ውስጥ አንድ ሰው አንድ ጥሩ ነገር በሚያገኝበት ጊዜ፣ ለእኛ የሚደርሰን መጥፎው ነው ብለን እናስባለን። የጥሩ ነገሮች ቁጥር ውስን ስለሆነ፣ ሌላው ግለሰብ ወይም ቡድን ጥሩውን ነገር እንዲወስድ ከፈቀድንለት፣ ለእኛ የሚተርፈን ጥሩ ነገር አይኖርም ብለን እናስባለን። ነገር ግን እግዚአብሔር እኛ ከምናስበው በላይ ነገሮችን መባረክ የሚችል አምላክ ነው። እግዚአብሔር የሚያደርጋቸው መልካም ነገሮች መጨረሻ የላቸውም። እኛ ወይም ቤተ ክርስቲያናችን የሚያስፈልገንን አንድ መልካም ነገር ልናጣ ከመሰለን፣ ይህንኑ መልካም የመሰለንን ነገር የሙጥኝ ብለን ስንጣላ ከምንኖር፣ እግዚአብሔር ለእኛ ከዚያ የላቀ ነገር እንዳለው በማመን ጥለናው ልንሄድ ይገባል። አብርሃም እግዚአብሔር እንደሚባርከው ያውቅ ነበር። ለዚህም ነው ሎጥ እጅግ ለም የሆነውን ቦታ እንዲመርጥ የፈቀደለት። እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት አይቶ ባረከው። ጠቅላላውን የከነዓን መሬት ርስቱ አድርጎ ሰጠው። የፈለግነውን ነገር ካላገኘን፣ ምንም አናገኝም ብለን መጨነቅ የለብንም። እግዚአብሔር ለእኛ የሚበጅ መፍትሔ እንደሚሰጥ ስለምናምን፣ ማጣትን መፍራት የለብንም።

ሐ. አለመግባባት ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ፣ ለእኛ ወገን ብቻ ሳይሆን፣ ለሁሉም የሚበጅና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው መፍትሔ መፈለግ አለብን:: በሰዎች መካከል የአሳብ ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ችግሩን ማስተካከል የሚቻልባቸው ስድስት መንገዶች አሉ::

1) <u>እኔ አሸንፋለሁ</u>:- «እኔ አሸንፋለሁ:: ስለ አንተ አያገባኝም::» ይህ የአለመግባባት መንገድ ለራሳችን ብቻ እንደምናስብ የሚያሳይ ነው:: «የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቱ ወደ እኛ ቀጣና እንዲመጣ እፈልጋለሁ:: ሌሎች የፈለጉትን ቢሉም፣ ይህ መሆን አለበት::» ውሳኔው ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አካባቢዎችን በአሉታዊ መንገድ ይነካ እንደ ሆነ አንጨነቅም። ይህ አመለካከት ችግሮችን የሚመለከተው ከራስ ጥቅም አንጻር ብቻ ነው:: ለሌሎች የግድ የለሽነት ስሜት ይኖረዋል:: ይህ ሁልጊዜም የራስ ወዳድነት አቋም ነው::

2) <u>እኔ አሸንፋለሁ፣ አንተ ትሸነፋለህ</u>:- «እኔ አለቃ ነኝ:: ስለዚህ የእኔ አመለካከት እንዲያሸንፍና የአንተ እንዲሸነፍ አድርጌ እወስናለሁ::» ሌላው ግለሰብ ወይም ቡድን ቢጎዳም እንኳን፣ እንዲህ ዓይነት አመለካከት ያላቸው ሰዎች ለራሳቸው የሚበጅ ውሳኔ ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም:: በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ይህ ተፈጥሯዊ አሠራር እንደ ሆነ ስንማር ኖረናል:: እኔ ካሸነፍኩ፣ የሆነ ሰው ይሸነፋል ብለን እናስባለን:: ቮሊቦል በምንጫወት ጊዜ፣ አንደኛው ቡድን ያሸንፋል፣ ሌላኛው ደግሞ ይሸነፋል:: በትምህርት ቤትም፣ አንዱ ጥሩ ውጤት ያገኛል፣ ሌላው ደግሞ መጥፎ ውጤት ያገኛል:: ጥሩ ውጤት ያመጣው ተማሪ ሲሸለም፣ ጥሩ ውጤት ያላመጣው ግን አይሸለምም:: የዚህ ዓይነቱ የግጭት ግንዛቤ ፉክክርን እንጂ አንድነትን አያመጣም:: ለጥሩ መፍትሔ አብረው የሚሠሩትን ሰዎች እንደ መሸለም፣ ሰዎች በፉክክር ላይ የተመሠረተ ሥራ እንዲሠሩ ያደርጋል:: የዚህ ዓይነቱ አሠራር አንደኛው ቡድን እንዲያሸንፍና ሌላኛው እንዲሸነፍ የሚያደርግ ነው:: በሰዎች ወይም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ፉክክር ሲኖር፣ ግንኙነቶች እየሻከሩ ይሄዳሉ::



ሥልጣናችንን ተጠቅመን ስናሸንፍ ወይም አሳባችን የሌላውን ሰው አሳብ ሲያሸንፍ ክርክሩ ሊቆም ቢችልም፣ ግንኙነቱ ከአደጋ ላይ ይወድቃል:: አንድ ሰው በክርክር «በሚሸነፍበት» ጊዜ፣ በልቡ ቅር ስለሚለኝ ውደፊት የተባባሪነት መንፈሱ ይቀንሳል:: በኋላም ችግሩ እንደገና በሌላ መንገድ ይከሰታል:: ከቡድኖቹ አንደኛው ተሸንፌአለሁ የሚል ስሜት በልቡ እስካነገበ ድረስ፣ ዘለቄታዊ መፍትሔ ማምጣት የሚቻልበት መንገድ አይኖርም::

3) «እኔ <u>ልሸነፍ</u>፣ <u>አንተ</u> አሸንፍ»:- «እኔ ራሴን ዝቅ በማድረግ አንተ እንድታሸንፍ አደርጋለሁ::» ብዙ የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ለሕይወት ያላቸው ግንዛቤ እንዲህ ዓይነት ነው:: «እኔ አልተ ማርኩም:: አንተ የተማርክ ስለ ሆንክ፣ የምትነግረኝን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ» ይላሉ:: «እኔ ቅጥር ሠራተኛ ስሆን፣ አንተ አለቃ ነህ::» «ወጣቶች ስሜታዊነት በበዛበት ስብሰባቸው ላይ የሚያደርጉትን ነገር አልወደውም:: ግን ምን ላደርግ እችላለሁ? በሰላም ለመኖር ስል፣ ያሻቸውን እንዲያደርጉ ዝም ማለት አለብኝ::» «እኔ ሴት ነኝ፣ አንተ ወንድ ነህ። ስለዚህ አንተ የምትፈልገውን ነገር ሁሉ አደርጋለሁ::» የዚህ ዓይነቱ አመለካከት በሁለት መንገዶች ሊታይ ይችላል::

በመጀመሪያ፣ አመራር ላይ ስላይደሉ፣ ሁልጊዜም ውሳኔው እነርሱን እንደሚጎዳ የሚያስቡ ሰዎች አሉ:: እንዲህ ዓይነት አስተ ሳሰብ ያላቸው ሰዎች አሳብ የመስጠት ወይም የግል ራእይ የመያዝ መብት እንደሌላቸው ያስባሉ:: በየትኛውም ክርክር ላይ በቀላሉ እጅ ይሰጣሉ:: የዚህ ዓይነቱ ግንኙነት ወይም የግጭት አፈታት ዘዴ በፍጹም ጤናማ አይደለም:: ሰሎሞን እንዳለው፣ ጤናማው ግንኙነት ብረት ብረትን የሚስልበት ዓይነት ነው:: ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ አንድ ሰው አሳቡን በግልጽ መናገር ሲችል ነው:: በሰዎች መካከል ጥሩ ግንኙነት ሊኖር የሚችለው ሁለቱም አመለካከታቸውን፣ አሳባቸውን፣ ፍላጎታቸውንና ሕልማቸውን ለመግለጽ ሲችሉ ነው:: አንድ ቡድን ራሱን ድምጽ-አልባ አድርጎ ማቅረቡ ጤናማ አይደለም:: ምንም እንኳን ሰዎች ለሌላው ግለሰብ ፈቃድ ራሳቸውን ቢያስገዙም፣ በልባቸው ውስጥ ንዴት ማደጉን

ሊቀጥል ይችላል:: ይህም ንዴት ሲያድግ ቆይቶ በድንገት እንደ እሳተ ገሞራ ሊፈነዳ ይችላል:: ባሏ ከሚገባው በላይ ስለ ጨቆናት ለሚያዛት ነገር ሁሉ እሺ ስትል የቆየች ሚስቱ፣ በድንገት ተበሳጭታ ለውዬውን የገደለችበት ጊዜ አለ::

ሁለተኛ፣ ብዙውን ጊዜ ራሳቸውን በእኩል ደረጃ ላይ እንደሚገኙ አድርገው የሚመለከቱ ሰዎች በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ አመለካከት ይኖራቸዋል:: ከብዙ ውይይት በኋላ በድምጽ ብልጫ አንደኛው ቡድን በመጨረሻው ለሌላኛው ቡድን አመለካከት ይገዛል:: ምንም እንኳን ሰላምን ለማምጣት ሲባል አንደኛው ቡድን ለሌላኛው ቡድን ቢገዛም፣ የተሸነፉት ሰዎች ብዙውን ጊዜ ከስብሰባው ቦታ የሚወጡት ተናድደው ነው:: ይህ ደግሞ በኋላ በሌሎች ውሳኔዎች ላይ እምብዛም ተሳታፊዎች እንዳይሆኑ ያደርጋቸዋል::

4. <u>ሁለታችንም</u> <u>እንሸነፋለን</u>:- «በዚህ ጉዳይ እርሱ እንዲያሸንፍ አልፈልግም፤ ትክክል ይሁን ስሕተት የሚያገባኝ ነገር የለም:: እኔ ለማሸነፍ ካልቻልኩ፣ ሁለታችንም እንሸነፋለን::» ሰዎች እጅግ በመናደዳቸው ምክንያት ሊያስማማ የሚችለውን አሳብ ለመቀበል የማይፈልጉበት ጊዜ አለ:: ባላንጣቸውም ምንም የማያገኝ ከሆነ፣ ሲፈልጉ የነበረውን ነገር ማጣታቸው ምንም መስሎ አይታያቸውም:: ብዙውን ጊዜ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ጥላቻና ንዴት ስለሚያይል፣ ማናቸውም ስለ ጥሩ መፍትሔ አያስቡም:: ሁሉም ሰው የሚያስበው ባላንጣውን ለማሳጣት ብቻ ይሆናል::

5. <u>ሁለታችንም እናሸንፋለን፤ ሁለታችንም እንሸነፋለን</u>:- «እኔ የምፈልገውን ሁሉ አላገኝ:: እርሱም የሚፈልገውን ሁሉ አያገኝ:: ነገሩን ወደ መሐል ቤት እናምጣውና ሁለታችንም ከምንፈልገው የተወሰነውን ነገር እናገኝ:: ይህ ከሁሉም የተሻለ መፍትሔ ላይሆን ቢችልም፣ ሁለታችንም ከምንፈልገው የተወሰነውን ነገር ልናገኝ ስለምንችል፣ ስምምነት ይኖረናል::» ብዙውን ጊዜ፣ የአሳብ ልዩነት በሚከሰትበት ጊዜ፣ በኮሚቴ ወይም በቦርድ የሚሰጡት ውሳኔዎች በዚህ መንገድ የሚከናወኑ ናቸው:: መሐል ቤት ምርጥ አማራጭ



ባይሆንም፣ ለመፍትሔ አስፈላጊ የሚሆንባቸው ጊዜያት አሉ:: መሐል ቤት አማራጭ ማለት ሰላምን ለመጠበቅ ሲባል ከምንፈልገው ያነሰ ነገር ማግኘት ማለት ነው:: የመሐል ቤት አማራጭ «ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለው ነገር ምንድን ነው?» ከማለት ይልቅ፣ «ሰዎች እንዴት አብረው እንዲሠሩ ማድረግ እንችላለን?» የሚል ጥያቄ ያነሣል::

6) <u>ሁለታችንም ልናሸንፍ የምንችልበትን መንገድ እንፈልግ</u>:- «እግዚአብሔር ለሁለታችንም ጥሩ የሆነ መፍትሔ እንደሚሰጠን አውቃለሁ:: ስለዚህ የምትናገረውን ለመስማት ዝግጁ ነኝ:: የራሴንም አሳብ አካፍልሃለሁ:: እግዚአብሔር ሁለታችንንም ምርጥ ነው ወደምንለው መፍትሔ እስኪያደርሰን ድረስ በትዕግሥት እጠብቃለሁ::» የዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ እግዚአብሔር በሁኔታው ውስጥ ሊሠራ እንደሚችልና ለሁሉም፣ በተለይም ለእግዚአብሔር መንግሥት ምርጥ የሆነውን መፍትሔ እንደሚሰጥ ያምናል:: ሁለቱም ወገኖች ምርጥ መፍትሔ ተገኝቷል ብለው እስኪያምኑ ድረስ መፍትሔ ፍለጋው ይቀጥላል:: የሚቻል ሲሆን፣ ይህ ግሩም የግጭት አፈታት ስልት ነው:: ነገር ግን ይህ ብዙውን ጊዜ ተግባራዊ የሚሆነው ሰዎች እርስ በርሳቸው ለመደማመጥ ሲፈቅዱና እግዚአብሔር ለሁሉም ሰው የሚመች የተሻለ መንገድ እንዳለው ሲያምኑ ነው::

መ. እንግዲህ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ የትኛውን ዓይነት የመፍትሔ አማራጭ ልንከተል ይገባል? ይህ እንደ ሁኔታው የሚለዋወጥ ነው::

1) አጣዳፊ ነገር ካለና ውሳኔ መስጠት ካስፈለገ፣ መሪው አንዳንድ ጊዜ ለማሸነፍ መወሰን አለበት:: ውሳኔ ይሰጥና ሌሎች ተግባራዊ እንዲያደርጉት ይነግራቸዋል:: ይህ የሚሆነው ጉዳዩ አጣዳፊ ከሆነና ከሌሎች ጋር በጥልቀት ለመወያየት የሚያስችል ጊዜ ከሌለን ብቻ ነው:: መወያየት የሚቻልበት ዕድል እያለ እንዲህ ዓይነት እርምጃ መውሰዱ ግን፣ ወደ ብስጭትና ክፍፍል እንደሚመራ ግልጽ ነው::

2) አብሮ መሥራቱ አስፈላጊ ካልሆነ፣ አንዳንድ ጊዜ መፎካከሩ ጥሩ ሊሆን ይችላል:: «ሃያ አምስቱንም የመቅህማ መጻሕፍት አጥንተው የሚጨርሱ የመጀመሪያዎቹ ሀያ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ይሰጣቸዋል» ብንል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ለማግኘት ሲሉ ብዙ ሰዎች የመቅህማን ጥናት ሊያካሂዱ ይችላሉ:: ይህ ግን ብዙውን ጊዜ ራሱን የሚጎዳ አሠራሪ ነው:: የመጀመሪያዎቹ ሀያ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ሽልማት ካገኙ በኋላ፣ ጥናቱን የሚያካሂዱ ሰዎች አይኖሩም:: መጽሐፍ ቅዱስ ሳይሸለሙ የቀሩ ሰዎች ደግሞ ተስፋ ይቆርጣሉ:: ከፊሉ የሚያሸንፍበትና ከፊሉ የሚሸነፍበት ፉክክር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አምብዛም ውጤታማ አይሆንም::

3) አንዳንድ ግጭቶች አስከፊ በመሆናቸው ምክንያት ሰላም ለማምጣት ሲባል አንደኛው ቡድን ሰመሸነፍ የሚወስንበትና ሌሳኛው የሚያሸንፍበት ሁኔታ ይኖራል:: በቆሮንቶስ ምእመናን እርስ በርሳቸው በመጣላትና አንዱ ሌላውን ወደ ፍርድ ቤት በመጎተት ላይ በነበሩበት ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ ያቀረበው የመፍትሔ አሳብ ይሄ ነበር (1ኛ ቆሮ. 6:1-8):: የክርስቶስንና የቤተ ክርስቲያን ስም ላለመሰደብ ሲባል፣ ክርስቲያኖች «ቢሸነፉ» መልካም ነው የሚል መልእክት ነበር ያስተላለፈው:: መንፈሳዊ የሆኑ ክርስቲያኖች ለክርስቶስ ብለው የሚሸነፉባቸው ጊዜያት አሉ:: ነገር ግን ይህ መሸነፍ በግለሰቡ ፈቃደኝነት ሳይሆን በሌላ ሰው አስገዳጅነት የሚከናወን ከሆነ፣ በአመዛኙ ችግሩ እየተባባሰ ይሄዳል:: በአብዛኞቹ ውሳኔዎች ውስጥ ደግሞ አንዱ ተሸንፎ ሌላው ማሸነፉ ጥሩ ነገር አይሆንም:: አንድ ሰው ሁልጊዜም የሚሸነፍ ከሆነ፣ ውሳኔው ምርጥ ውሳኔ ነው ሊባል አይችልም:: ብዙም ሳይቆይ የተሸነፈው ግለሰብ ወይም ቡድን በንዴት ይነሣሣና የበለጠ ችግር ሊከተል ይችላል::

4) ሰዎች አብረው ለመሥራት በሚፈልጉበት ጊዜ፣ ሁለቱንም የሚያስማማ መፍትሔ ከልባቸው መፈለግ ይኖርባቸዋል:: ሰዎች ቀደም ብለው ልዩነቶቻቸውን ከሚከተሉት ሁለት መንገዶች በአንዱ ለመፍታት ካለቡ፣ ቀጣዩ ግንኙነታቸው የበለጠ ጤናማ ይሆናል::



አንደኛ፣ መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ቡድኖች ደስተኛ ወደሚሆኑበት ውሳኔ እስካልመራቸው ድረስ፣ ምንም ነገር እንደማያደርጉ ይስማማሉ:: ግንኙነታቸውን የሚጎዳ ውሳኔ ከመስጠት ይልቅ፣ ግንኙነታቸው የበለጠ አስፈላጊ መሆኑን ይቀበላሉ:

ሁለተኛ፣ ወደ ጋራ ስምምነት ሊደርሱ ካልቻሉ፣ እያንዳንዱ ቡድን በራሱ መንገድ እንደሚሄድና አብረው ለመሥራት እንደማይሞክሩ ይስማማሉ:: ለረዥም ጊዜ የቆየ ግንኙነት ያላቸው ሰዎች አንዱ ተጠቃሚ ሌላው ተጎጂ የሚሆንበት ሁኔታ ውስጥ ከሚገቡ፣ በፍቅር ላለመስማማት ቢስማሙ መልካም ነው:: ይህንን በምናደርግበት ጊዜ የምንለው ይህንን ነው፣ «ለማሸነፍ አፈልጋሰሁ:: አንተም እንድታሸንፍ አፈልጋለሁ:: ይህ የማይቻል ከሆነ ግን፣ ግንኙነታችን እንዳይበላሽ ስለምፈልግ፣ ማናችንም የማንሸነፍበትን መንገድ መፈለግ አለብን:: ሽንፈቱ ግንኙነታችንን ከማበላሸት የተሻለ ሚና አይኖረውም:: ስለዚህ፣ ሌላ አማራጭ መፈለግ ወይም በየራሳችን መንገድ መሄድ ይኖርብናል:: አንተም አገልግሎትህን በራስህ መንገድ ታካሂደዋለህ፣ እኔም አገልግሎቴን በራሴ መንገድ አካሂደዋለሁ:: ወይም ደግሞ ጭራሽ አገልግሎት የሚባሰውን ነገር መተው አለብን::» ሰዎች በእኩል ደረጃ ተያይትው በሚሠሩበት ጊዜ፣ ወደ ጤናማና ፍቅር ወዳለበት ግንኙነት የሚመራቸው እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ብቻ ነው::

16ኛ ጥያቄ:- በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ስለ ነበረ አንድ ግጭት አስታውስ:: ሀ) ከላይ የተገለጹትን ስድስት መንገዶች በመጠቀም ቢካሄድ ኖሮ፣ መፍትሔው ምን ይመስል እንደ ነበረ ግለጽ:: ለ) ለዚህ ሁኔታ የትኛው አማራጭ የሚሻል ይመስልሃል? ለምን? ሐ) ሰዎች ሰሌ ሎች ሰዎች ውሳኔዎች እጅ ሲሰጡና በኋላ ግን መሸነፋቸው የበለጠ ችግር ሲፈጥር የተመለከትከበትን ሁኔታ ግለጽ::

**4. ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች የተለያዩ አሳቦችን በመያዛቸው ምክንያት መፍትሔ ማምጣቱ አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ፣ በግጭት**

ውስጥ ያልተሳተፈና ሁለቱም ቡድኖች (ወይም ግለሰቦች) የሚያከብሩትን ሰው በማስገባት ችግሩን ለመፍታት መሞከር ጠቃሚ ነው።

ይህ ሦስተኛ ሰው ወይም ቡድን የሚመጣው እገሌ ጥፋተኛ ነው እገሌ ትክክል ነው የሚል ፍርድ ለመስጠት አይደለም። ነገር ግን፣ ሁለቱም ሰዎች ወይም ቡድኖች የልዩነቶቻቸውን ምክንያቶች እንዲያውቁና በጋራ የሚያስማሟቸውን ነጥቦች እንዲፈልጉ ለማገዝ ነው። ሦስተኛው ሰው በችግሩ ውስጥ ስሜታዊ ተሳትፎ ስለሌለው (ማለትም እንደ እነርሱ ስሜታዊ ስለማይሆን)፣ ሁለቱ ወገኖች ጉዳዩን በግልጽ ተመልክተው ሊያስማሙ የሚችሉትን እርምጃዎች እንዲወስዱ የማገዝ ብቃት ይኖረዋል። (ማስታወሻ፡- ይህ ሽምጋይ እንዴት ተግባሩን እንደሚያከናውን ወደ በኋላ በዚሁ ክፍል ውስጥ ማብራሪያ ቀርቧል።)

5. የአሳብ ልዩነቶችን ለማስታረቅ ጥረት በሚደረግበት ጊዜ፣ በተቻለ መጠን ብዙ አማራጮች እንዲቀርቡ ማድረጉ ተገቢ ነው። ብዙ አማራጮች በሚኖሩበት ጊዜ፣ የትኛው ጥሩ መፍትሔ እንደሚሆን መወሰኑ ይቀላል። አለመስማማትን ለማስቆም ከሁሉም የሚሻለው መንገድ ሁለቱንም ቡድኖች የሚያስማማ መፍትሔ ማግኘት ነው።

6. አንዱ የሌላውን ጥፋት መዘርዘር የለበትም። ይህ እምብዛም ጠቃሚ ስለማይሆን፣ በመፍትሔው ላይ ትኩረት ማድረጉ ጠቃሚ ነው። አብርሃም ሎጥን አጥፍተሃል ብሎ አልወቀሰውም። ምንም እንኳን ታላቅ እንደ መሆኑ መጠን፣ ከብቶቹን ውኃ የማጠጣት መብት ቢኖረውም፣ መብቱን ለማስከበር አልሞከረም።

7. በረዥም ጊዜ ግብ ላይ ትኩረት አድርግ። በወደፊቱ ጠቃሚ ግብ ላይ ትኩረት ለማድረግ ሲባል አነስተኛዎቹን ጉዳዮች ማለፉ ተገቢ ነው። አብርሃም ለምርጥ ግቡ (ከወንድሙ ልጅ ጋር በሰላም ለመኖር ሲል) ምርጡን መሬት (ለእርሱ ብዙም አስፈላጊ ያልነበረውን) ትቷል። ሰዎች ትክክል ነው ብለው የሚያስቡትን ነገር ለማሳካት የሚታገሉ ከሆነ፣ የተሻለ መፍትሔ ለማምጣት



አይሞክሩም። አንዳንድ ጊዜ የጸቡን ዑደት ለማቆምና ዘለቄታዊ መፍትሔ ማምጣት የሚቻልበትን መንገድ ለመክፈት አማራጩ ከተከራካሪ ወገኖች አንደኛው ፍትሐዊ ባይሆንም እንኳን፣ ተፎካካሪው የሚፈልውን እንዲያገኝ መፍቀድ ሊሆን ይችላል። ደግ በመሆን የምታጣው ነገር የለም። እግዚአብሔር ደግነታችንን በማክበር የተሻለ ነገር ይሰጠናል። አብርሃም በወቅቱ ምርጥ የሆነውን መሬት ቢያጣም፣ እግዚአብሔር በኋላ አገሩን በሙሉ ሰጥቶታል። ብዙውን ጊዜ በደግነት ለመሸነፍ ፈቃደኛነታችንን በምናሳይበት ጊዜ፣ ሌሎች ይበልጥ ጠቃሚ በሆኑ ጉዳዮች እንድናሸንፍ ሊያደርጉን ይችላሉ። ይህ ሰዎች ቀደም ሲል የፈለጉትን ነገር በማጣታቸው፣ ሌሎችም የፈለጉትን እንዳያገኙ የሚተናኮሉበትን ዑደት ለማስቀረት ጠቃሚ እርምጃ ሊሆን ይችላል።

8. አንድን ነገር ከተውከው በኋላ፣ ንዴት ወደ ልብህ እንዲገባና ግንኙነቱን እንዲያበላሽ አትፍቀድ። ያለፈውን እርሳውና ከግለሰቡ ጋር ጤናማ ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት አድርግ። አብርሃም ሎጥ የተሻለውን ነገር እንዲመርጥ ያደረገው በምሬት የተሞላ ልብ ይዞ አልነበረም። በኋላ፣ ሎጥ ችግር በገጠመው ጊዜ፣ አብርሃም ሕይወቱን ለአደጋ በማጋለጥ ሊታደገው እንመለከታለን። አንተ ስትሸነፍ ባሸነፉት ሰዎች ላይ የበቀል አሳብ በመያዝ ወደፊት የእጃቸውን እንዲያገኙ አደርጋለሁ የሚል የበቀል ስሜት በልብህ ውስጥ ማስተናገድ እንደሌለብህ አስታውስ። በሽንፈትህ ተቆጭተህ የወደፊት ውሳኔዎችን በመጠቀም ሌሎችን ልትጎዳ ካሰብክ፣ እንዲህ ዓይነቱ ሥራ በአንተም ሆነ በእግዚአብሔር መንግሥት ላይ ችግር የሚፈጥር መሆኑን መገንዘብ ይኖርብሃል።

9. አንድን ተግባር ለማከናወን ከስምምነት ላይ መድረስ ካልቻላችሁ፣ እያንዳንዱ ሰው እግዚአብሔር በመራው መንገድ እንዲሠራው ነጻነት ስጡት። አንድ ሰው ወይም ቡድን ትክክለኛ የአሠራር መንገድ አይደለም የሚለውን መስመር ተከትሎ እንዲሠራ በሌሎች ግዳጅ እንዲጣልበት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። ሁለት ሰዎች ወይም ቡድኖች አብረው ለመሥራት እየፈለጉ ሥራውን በሚያከናውኑበት መንገድ ላይ ለመስማማት

ካልቻሉ፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ቡድን ያለምንም ጸብ የራሱን ዕቅድ ተከትሎ እንዲሠራ ነጻነት መስጠቱ መልካም ነው:: በዚህ በኩል ነው መሥራት ያለበት ብሎ ሰዎችን ከማስገደድ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በመቆጣጠር ለራሱ ክብር እንደሚያውል ማመኑ የተሻለ ነው::

10. የምናደርገው ማንኛውም ነገር የክርስቶስን ስም እንዳያሰድብ ተጠንቀቅ:: የክርስቶስ ስም ከሚሰደብ ይልቅ፣ ሰዎች መጠቀሚያ ቢያደርጉን ወይም ቢጎዱን የተሻለ ነው (1ኛ ቆሮ. 6:7):: *«እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት (ትክክል ብትሆኑም እንኳን) ነው:: ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን?»*

11. ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የተሻለው ነገር ምንድን ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ማተኮሩን አረጋግጡ:: (ማቴ. 6:33 አንብብ::) ስለ ችግሮችና የአሠራር ስልቶች በምናስብበት ጊዜ፣ ነገሮችን መመልከት ያለብን ከራሳችን እይታ አንጻር ወይም ለእኛ ምርጥ ከሆነው ነገር አንጻር መሆን የለበትም:: ሁሉም ሰው ለእግዚአብሔርና ለመንግሥቱ የሚሻለውን ነገር ማሰብ አለበት:: ለእግዚአብሔር መንግሥት ምርጥ ያልሆነውን ነገር ማድረግ የለብንም:: አንድ ነገር ለእግዚአብሔር መንግሥት ምርጥ ከሆነ፣ ለእኛ ምርጥ ባይሆን ወይም ባይመቸንም፣ ለማከናወን መጨከን አለብን:: ትልቁ ጥያቄ «ለቤተ ክርስቲያን እድገትና ለእግዚአብሔር መንግሥት ከሁሉም የሚሻለው ምንድን ነው?» የሚለው ነው:: ዋናው ጉዳይ ይሄ ነው:: ውሳኔዎችን የምንሰጠው ለአካባቢያችን ክብርን በሚያመጣው ነገር ላይ በመመሥረት ከሆነ፣ የራሳችንን መንግሥት እየገነባን ነው ማለት ነው:: ይህ መንግሥት መውደቁ የማይቀር ነው:: ነገር ግን ውሳኔዎችን የምንሰጠው ለእግዚአብሔር መንግሥት በሚበጅ ጉዳይ ላይ በማተኮር ከሆነ፣ እግዚአብሔር ውሳኔያችንን በመባረክ መንግሥቱን ለማስፋፋት ይጠቀምበታል::

12. በፍቅር ላይ በማተኮር ከራሳችን በላይ በሌላው ሰው ፍላጎቶች ላይ አጽንኦት መስጠት (ፊልጵ. 2:3-4):: አብዛኞቹ



ክፍፍሎች የሚከሰቱት በራስ ወዳድነት «ለእኛ የሚጠቅመው የትኛው ነው?» የሚል ጥያቄ ስለምናነሣ ነው (ያዕ. 4:1-2):: የሰላም፣ የፍቅርና የመልካም ግንኙነቶች መሠረቱ ለሌላው የሚበጀው ነገር ምንድን ነው? በሚል ጥያቄ ላይ ትኩረት ማድረግ ነው:: ራስህን በሌላው ግለሰብ ስፍራ በማድረግ፣ «የሌላኛው ቤተ ክርስቲያን መሪ ብሆን ምን እፈልግ ነበር? አስፈላጊው ነገር ምን ይሆን ነበር?» ብለህ መጠየቅ አለብህ::

17ኛ ጥያቄ:- የክፍለ ማኅበረት ኅብረት መሪ ነህ እንበል:: ሁለት የቀጣና አብያተ ክርስቲያናት ለቦርድ ስብሰባ መጥተዋል:: ሁለቱም በየአካባቢያቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለመክፈት ፈልገዋል:: ያለው ገንዘብ ግን አንድ ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ከመክፈት ያለፈ አለመሆኑን ታውቃለህ:: ከአብርሃም ሕይወት የተማርናቸውን እውነቶች ከልስ:: ሀ) ሁለቱ ቀጣናዎች ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ ለማገዝ ውይይቱን እንዴት አድርገህ ትመራለህ? ለ) ከስድስቱ የውሳኔ መንገዶች የትኛው ለዚህ ሁኔታ በመፍትሔነት ሊያገለግል እንደሚችል አብራራ:: ሐ) ሽማግሌዎች በሁለቱም ቡድኖች ተቀባይነት ያለው መፍትሔ ለማግኘት ወይም ይህ መንፈስ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የሚሠራበት ጊዜ መሆኑን የሚያሳይ ነው የሚል አቋም ለመያዝ ቢፈልጉ፣ ይህ በውይይቱና በውሳኔው ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደሚያሳድር ግለጽ:: መ) በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሁለቱንም ቡድኖች የሚያስማማ መፍትሔ መፈለግ የረዥም ጊዜ ግንኙነታቸውን የሚጠብቀው እንዴት ነው? ሠ) አንደኛው ቡድን ብቻ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት እንዲገነባ ማድረግ ሁለቱ ወገኖች ወደፊት አብረው እንዳይሠሩ የሚያደርገው እንዴት ነው?

## በሁለት ጎሳዎች ወይም ቡድኖች መካከል ግጭቶች በሚከሰቱበት ጊዜ፣ እንዴት ሰላምን ማምጣት እንደሚቻል:-

18ኛ ጥያቄ:- የሐዋ. 6:1-7ን አንብብ:: ሀ) ግጭቱ የተፈጠረበት ዋንኛው ምክንያት ምን ነበር? ለ) ግጭቱ እንዲጎለብት ያደረጉት ሌሎች ምክንያቶች ምን ምን ይመስሉሃል? ሐ) ሐዋርያት ግጭቱን ለማስቆም ምን አደረጉ? መ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ተመሳሳይ ግጭት የተከሰተበትን ሁኔታ ግለጽ:: ሠ) ግጭቱን በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ለማስቆም ሽማግሌዎች ምን አደረጉ? ረ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ ቡድኖች መካከል እንዴት ክፍፍል ሊፈጠር እንደ ተመለከትክ አብራራ:: የእነዚህ ክፍፍሎች ውጤት ምን ነበር?

በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመግባባት መኖሩን የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ይነግረናል:: እንዲህ ዓይነት አለመግባባት በሚኖርበት ጊዜ፣ ሰይጣን በሥራ ላይ መሆኑን መረዳት ይቻላል:: በተጨማሪም፣ መፍትሔ የሚያሻቸው መሠረታዊ ችግሮች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መኖራቸውን የሚያሳይ ምልክት ጭምር ነው:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚኖርበት ጊዜ፣ መጸለይና እግዚአብሔር ችግሩን እንዲያስወግድ መጠየቁ ብቻ በቂ አይደለም:: ነገር ግን መሠረታዊ ችግሮች ምን ምን እንደ ሆኑ በጸሎት ፈልገን ማግኘት አለብን:: ለችግሩም መፍትሔ መስጠት ይኖርብናል:: በዚህ ታሪክ ውስጥ ክርስቲያኖችን ለግጭት የዳረጉ ሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች ነበሩ::

አንደኛ፣ የጎሳ ችግር ነበር:: በዚያን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ዓይነት ጎሳዎች ነበሩ:: በፍልስጥኤም የተወለዱና የአረማይክ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዶች ነበሩ:: ከፍልስጥኤም ውጭ የተለወዱና የግሪክ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዶችም ነበሩ:: ሁለቱም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነበሩ:: የተለያዩ ቡድኖች በቤተ ክርስቲያን ውለጥ በሚገኙበት ጊዜ፣ ነገሮችን በጥሩ ሁኔታ ካልተቆጣጠርን፣ ክፍፍል ሊፈጠር ይችላል:: ነገሮች ሰዎች ሚዛናዊ ነው ብለው በሚያምኑት መንገድ የማይያዙ ከሆነ፣ ሁልጊዜም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ችግሮች መከሰታቸው የማይቀር ነው:: ሐዋርያት በቡድኖቹ መካከል ለማዳላት እየፈለጉ አልነበሩም:: ይህ ለክፍፍሉ መፈጠር ቡድኖቹ ያቀረቡት ማመካኛ ነው::

ሁለተኛ፣ የምእመናን ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማደጉ ለአመራር ችግር ፈጥሮ ነበር:: በአንድ ቀን 3000 አባላት በቤተ ክርስቲያናችሁ ላይ መጨመራቸው ምን ያህል ለውጥ እንደሚያስከትል አስብ! (የሐዋ. 2:41):: ወዲያውኑ 12ቱ ሐዋርያት በብዙ ሥራዎች መጠመድ ጀመሩ:: የአማኞችን ፍላጎቶች የሚያሟላ ጥሩ አለተዳደራዊ መዋቅር ስላልነበረ፣ ውጥረቶች መከሰት ጀመሩ:: ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ውጥረቶች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ችግሩ የሚፈጠረው መሪዎች ሥራ ስሚበዛባቸውና ለምእመናን



የሚያስፈልጉትን መንፈሳዊና አካላዊ ነገሮች በጊዜው ለማቅረብ ስለሚቸገሩ ነው::

በተለያዩ ቡድኖች መካከል ግጭቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ (በተለይም በታሪክ የታወቀ ችግር የሚደርስበት አናሳ ቡድን ሲኖር)፣ መከፋፈል የሚፈጠረው ፍትሐዊ አሠራር ባለመኖሩ ምክንያት ሳይሆን፣ ፍትሐዊነት አይኖርም የሚል ግንዛቤ በሰዎች አእምሮ ውስጥ በመስረጹ ምክንያት ነው:: ሰይጣን ልዩነቶችን አጉልቶ በማሳየት፣ አንደኛው ቡድን መድልዎ ደርሶብኛል ብሎ የሚያስብበትን ሁኔታ ያመቻቻል:: በአመዛኙ መሪዎች ፍትሐዊ ለመሆን የሚችሉትን ጥረት ያደርጋሉ:: ሆኖም፣ ወቀሳው አሁንም እዚያው ይኖራል:: በመሆኑም፣ ለዚህ ዓይነቱ ችግር መፍትሔ በሚፈለግበት ጊዜ ማድረግ ያለብን ተጨባጭ የሆነውን ኢ-ፍትሐዊነት ማስወገድ ብቻ አይደለም:: ነገር ግን ነገሮች በፍትሐዊነት እየተከናወኑ አይደሉም የሚለውን አለተሳሰብም ለማጥፋት መጣር አለብን::

19ኛ ጥያቄ:- ሀ) ሁለት ወይም ሦስት የጎሳ ቡድኖች በአንድ ቤተ ክርስቲያን ውለጥ መኖራቸው እንዴት ግጭትን እንደ ፈጠረ ያጋጠመህን ምሳሌ በመጥቀስ አስረዳ:: ለ) ነገሮች በፍትሐዊ መንገድ እየተከናወኑ ሳለ ፍትሐዊ አይደሉም የሚል ግንዛቤ በመፈጠሩ ምክንያት ግጭት ሊነሣ የቻለበትን ሁኔታ አብራራ:: ሐ) ለምእመናን መንፈሳዊ ችግሮች መፍትሔ የሚሰጡ ብቁ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች አለመኖራቸው ግጭቶች እልባት ሳያገኙ እንዲኖሩ ያደረገበትን ሁኔታ ግለጽ::

ከዚህ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 6 ታሪክ በቤተ ክርሰቲያን ውለጥ ባሉት የተለያዩ ቡድኖች መካከል አንድነትን ለመፍጠር የሚያስችሉ አንዳንድ መርሖዎች ልንመለከት አንችላለን:-

1. የጎሳ ወይም የቡድን አለመግባባቶች መኖራቸውን የሚያሳይ ምልክት እንደ ታየ፣ በፍጥነት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል:: የዚህ ዓይነቱ አለመግባባት በራሱ ጊዜ ሊጠፋ እንደማይችል መገንዘቡ ጠቃሚ ነው:: ሐዋርያት መፍትሔ መፈለግ የጀመሩት ልክ ችግሩ እንደ ተከሰተ ነበር:: ችግሩ በራሱ መንገድ እንዲወገድ ለማድረግ አልሞከሩም::

2. ሥራውን በብቃት ለማከናወን የሚችሉ መሪዎች ከሌሉ፣ ተገቢውን አስተዳደራዊ ተግባር ለማከናወን ወይም ለምእመናን በቂ እንክብካቤ ለማድረግ እንዲቻል ሌሎች ሰዎችን መጠቀም ወይም አስተዳደራዊ መዋቅሩን ለችግሮቹ እልባት እንዲሰጥ አድርጎ ማስተካከል ተገቢ ይሆናል:: ምእመናን እየጨመሩ ሲመጡ፣ ሐዋርያት ሁሉንም ሥራ ለማስተዳደር አልቻሉም ነበር:: በመሆኑም፣ ችግሮች መከሰት ጀመሩ:: ሐዋርያት እህሉ በፍትሐዊነት እየታደለ ነው ወይ? የሚለውን ጥያቄ ከመመለስ ይልቅ፣ የችግሩን ሥር ለመዳሰስ ነበር የፈለጉት:: በመሆኑም፣ ለዚህ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ ለአጠቃላይ የቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደራዊ ጉዳዮች መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል አዲስ መዋቅር አዘጋጁ:: በዲያቆናት ደረጃ የሚሰጥ አመራር መጀመራቸው፣ ሐዋርያት በሌሎች ሥራዎች ሳይጠመዱ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መንፈሳዊ አመራር አጠናክረው እንዲቀጥሉ አስችሏቸዋል:: ከዚህም በላይ፣ በጊዜው የተፈጠረው ችግርና የወደፊት ወሳኝ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በዲያቆናት ሊከናወኑ ይችሉ ነበር::

ሐዋርያት ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ በመሻት ሌላ ችግር ላለመፍጠር ጥንቃቄ አድርገዋል:: የእህል አከፋፈሉን ሁኔታ ከመለወጣቸው በተጨማሪ፣ ፍትሐዊነቱን ለማረጋገጥ ራሳቸው እህል ለማደል አልሞከሩም:: ይህ ችግሩን ሊፈታ ቢችልም፣ በሐዋርያት ላይ የሥራ ጫና በመፍጠር ሌላ ችግር ይፈጥር ነበር:: ይህ ደግሞ ሐዋርያት እህል በማከፋፈሉ ሥራ ተጠምደው፣ ቀዳሚውን የመንፈሳዊ አመራር ሥራቸውን እንዳያከናውኑ ያደርጋቸው ነበር::

ግጭቶች በሚነሡበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መፍትሔ መስጠት ያለብን ለችግሩ መገለጫዎች ብቻ ሳይሆን፣ ለምንጩም ጭምር መሆን አለበት:: ይህንንም ማድረግ ያለብን ሌሎች ችግሮችን በማያስከትል መንገድ ነው:: መሪዎች የግንኙነት ችግሮች በመሳሰሉት ነገሮች ራሳቸውን ማጨናነቅ የለባቸውም:: የአምልኮ፣ የወንጌል ስርጭትና የማስተማር አገልግሎቶች በተጠናከ



ረ መንገድ እንዲቀጥሉ ለማድረግ፣ ጥንቃቄ መውሰድ አለብን:: እነዚህ ነገሮች ከተዳከሙ፣ ሰይጣን የአሸናፊነትን አክሊል ደፍቷል ማለት ነው:: ከዚህ ይልቅ፣ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሳይደናቀፍ ችግሮች የሚፈቱበትን መንገድ መፈለግ አለብን::

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዘላቂ ሰላም ሊኖር የሚችለው እያንዳንዱ አባል በቂ እንክብካቤ ካገኘና ችግሮች በፍጥነት እልባት ከተሰጣቸው ነው:: ለአባላት የእግዚአብሔርን ቃል በብቃት ማስተ ማሩም አስፈላጊ ነው:: እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን ለእነዚህ ሁለት አገልግሎቶች መሟላት ትኩረት መስጠት አለባት:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሁሉም ሰው መንፈሳዊ እንክብካቤ የሚያደርገው ማን ነው? መጋቢው ነው? ሽማግሌዎች? ሐዋርያት በቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ ጉዳዮች ተጠምደው መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ለማዳከም እንዳልፈለጉ ሁሉ፣ ሽማግሌዎችም የእግዚአብሔርን መንጋ በመንፈሳዊ መና የመመገብ ኃላፊነት አለባቸው:: አማኞች እግዚአብሔርን በመምሰል ሲያድጉና ችግር መፍጠራቸውን ሊቀንሱ የሚችሉት ደግሞ ቀጣይነት ያለው የትምህርትና የጸሎት አገልግሎት ሲሰጥ ነው::

ነገር ግን አስተዳደራዊ ሥራዎችንስ የሚሠራው ማን ነው? በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን እንደተከሰተው፣ ጥሩ አስተዳደር ከሌለ፣ ችግሮች መፈጠራቸው ስለማይቀር፣ አስተዳደራዊ ጉዳዮችም አስፈላጊዎች ናቸው:: የማስተዳደሩን ሥራ መሥራት ያለባቸው መሪዎች ናቸው? ከሆነ፣ ይህ ኃላፊነት መንፈሳዊ አገልግሎትን ከመስጠት ያደናቅፋቸው ይሆን? ወይስ እንዲህ ዓይነቱን ኃላፊነት ለዲያቆናት መስጠት ይቻል ይሆን? በጥሩ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያን የማትተዳደር ከሆነ፣ ሰይጣን በቀላሉ የግንኙነት ችግሮችን ሊፈጥር ይችላል::

20ኛ ጥያቄ:- ሀ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ መንፈሳዊ እንክብካቤ የሚያደርገው ማን ነው? ለ) ይህ ጠቃሚ መንፈሳዊ አገልግሎት ምን ቢደረግ በተሻለ ሁኔታ የሚካሄድ ይመስልሃል? ሐ) ለቤተ ክርስቲያናችሁ አስተዳደራዊ አገልግሎት የሚሰጠው ማን ነው? መ) በቤተ ክርስቲያን ጥሩ አስተዳደር የሚያስፈልገው ለምንድን ነው? ሠ) ይህ አገልግሎት ምን ቢደረግ በተሻለ ሁኔታ ሊካሄድ የሚችል ይመስልሃል?

3. ሁሉም ውሳኔዎችና መፍትሔዎች ለሁሉም በግልጽ መታወቅ አለባቸው። ሐዋርያት በድብቅ ተሰባስበው አልነበረም ውሳኔ የሰጡት። ከዚህ ይልቅ፣ አማኞች ሁሉ ባሉበት ስፍራ ነበር በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተፈጠረውን ውዝግብ የፈቱት። በተ መሳሳይ ሁኔታ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ፣ አያንዳንዱን ቡድን የሚመለከቱ ውሳኔዎች ሁሉ በግልጽ መታወቅ አለባቸው። ውሳኔዎች ድብቅ በሚሆኑበት ጊዜ፣ መተማመን ሊኖር አይችልም። ውሳኔዎች ለሁሉም በሚብራሩበት ጊዜ፣ ግልጽነት ይኖራል። ይህ ደግሞ ስለ ኢ-ፍትሐዊነት የሚነሣው ወቀሳ እንዲወገድ ያስችላል።

4. መፍትሔ እንዲሰጡ የሚመረጡ ሰዎች መመረጥ ያለባቸው በመንፈሳዊ ብቃታቸው ሊሆን ይገባል። ምንም እንኳን ሥራው እህል ማከፋፈል ቢሆንም፣ ሐዋርያት ለዚህ ሥራ የሚመረጡ ዲያቆናት መንፈስ ቅዱስ የሞላባቸውና በመልካም ባሕርያቸው የተ መሰከረላቸው መሆን እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን ሥራ ለማከናወን ምርጥ ሰዎችን መፈለግ አለብን። ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ተቋም ስለ ሆነች፣ ምርጥ ሰ ዎች ምን ጊዜም መንፈሳዊ ሰዎች ናቸው። ዘለቄታዊ ውጤት ሊገኝ የሚችለው የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በሚፈቅደው መንገድ ሊሠራ ነው። ሰዎች መፍትሔ አምጭዎቹ ላይ እምነት ከሌ ላቸው፣ መሪዎች የሚያደርጉት ማንኛውም ነገር በቅሬታ አቅራቢ ዎቹ ዘንድ ተአማኒነት አይኖረውም።

5. የችግሩ ተካፋዮች የሆኑ ወገኖች የመፍትሔው አካል መሆን አለባቸው። ሐዋርያት እነርሱ ብቻ የሚታመኑባቸውን ሰዎች አልመረጡም። ሰዎች እንዲመርጧቸው ነበር ያደረጉት። ይህ ደግሞ ሐዋርያት ኢ-ፍትሐዊ ናቸው የሚለውን ወቀሳ የሚያረግብ ነበር። ቅሬታ አቅራቢዎቹ የግሪክ ቋንቋ የሚናገሩ አይሁዶች ስለ ነበሩ፣ መፍትሔ አምጭዎች የተመረጡት ከእነርሱ ነበር። ሰባቱም ሰዎች የተመረጡት የግሪክ ተናጋሪዎች ከሆኑት አናሳ ቡድኖች ነበር። ከዚህ በኋላ የፍትሐዊነት ችግር ተፈጠረ የሚባልበት መንገድ አይኖርም ነበር። የጎሳ ችግሮችን መፍታት ከሚቻልባቸው መንገዶች አንዱ ቅሬታ አቅራቢዎቹ ራሳቸው መፍትሔ እንዲያመጡ ማድረግ ነው። የሌላ ጎሳ ሰዎች መፍትሔ የሚሰጡ ከሆነ፣ አናሳው ቡድን የሆነ ችግር ቢኖር ነው የሚል አመለካከት ይኖራቸውና አለመግባባቱ በመርገብ ፈንታ ይቀጥላል።

6. ኢ-ፍትሐዊነት እየደረሰብን ነው የሚሉ ወይም እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ይህ እውነት አለመሆኑን እንዲያምኑ መደረግ አለበት። ይህ ምናልባትም ከሌሎች የበለጠ ጥቅም እንዲያገኙ የሚያደርግ ሊሆን ቢችልም። ትልቁ ቡድን ከፍልስጥኤም የሆኑ አይሁዶች የሚገኙበት ነበር። በዴሞክራሲያዊ መንገድ በድምጽ ብልጫ እንወስን ቢባል ኖሮ፣ አብዛኞቹ ሰዎች ከዚሁ ቡድን ነበር የሚመረጡት። ይህ ግን አለመግባባቱን አይቀርፈውም ነበር። አለመግባባቱ እንዲረግብ ለማድረግ አብዛኞቹ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን ግሪክ ተናጋሪ አይሁዶች አብዛኞቹን ዲያቆናት እንዲመርጥ ዕድል መስጠት ነበረባቸው። ነገር ግን ሐዋርያት ይህንን በመፍትሔነት ጠቁመው ቢሆን ኖሮ፣ የፍልስጥኤም አይሁዶች መድልዎ ተደርጎብናል ብለው ሊያስቡ ይችሉ ነበር። ስለዚህ፣ ውሳኔው የሕዝብ መሆን ነበረበት። ከፍቅራቸው የተነሣ፣ የፍልስጥኤም አይሁዶች ከአናሳ የአይሁዶች ቡድን ሰባቱንም ዲያቆናት መሪዎች መረጡ።

ሌሎች ሆን ብለው ባይበድሏቸው እንኳን፣ ብዙውን ጊዜ አናሳ ቡድኖች (ለምሳሌ፣ አናሳ ጎሳዎች፣ ሴቶች፣ ድሆች፣ ያልተማሩ) መድልዎ ተደርጎብናል የሚል ስሜት ይሰማቸዋል። በተለምዶ ሁሉም ተግባር በትልቁ ቡድን ላይ ስለሚያተኩር፣ ሁልጊዜም ከሁኔታዎች ጋር የመመሳሰል ግዴታ የተጣለበትን አናሳ ቡድን ሥቃይ የሚረዳ ሰው አይኖርም። የምርጫ ሂደትም ሳይቀር ዴሞክራሲያዊ የድምጽ ብልጫን ስለሚጠቀም፣ ነገሮች ውሳኔ የሚያገኙት አብዛኞቹ አባላት የሚገኙበትን ቡድን በሚጠቅም መንገድ ነው። በመሆኑም፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድነትና ስምምነት እንዲኖር ከተፈለገ፣ አመራሩ በአናሳ ቡድን ፍላጎቶች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። ይህ በእኩልነት ተቀባይነት የተ ለጣቸውና ዋጋ ያላቸው ሰዎች መሆናቸውን እንዲገነዘቡ

ያስችላቸዋል። አንዳንድ ጊዜ አናሳዎቹ በአመራር ላይ ከሚገባቸው በላይ በብዙ መሪዎች ሊወከሉ ወይም የበለጠ ገንዘብ እንዲያገኙ ቢደረግ መልካም ነው። ይህም ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ቡድኖች በእኩልነት ለመመልከት የምትችለውን ጥረት እያደረገች መሆኗን ለመረዳት ያስችላቸዋል።

| |
|---|
| 21ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ያሉትን አናሳ ቡድኖች ዘርዝር። ለ) እነዚህ ወገኖች በእኩል ደረጃ እየታዩ ይመስልሃል? የዚህን ጥያቄ መልስ ካላወቅክ፣ የጉዳዩን ባለቤቶች ጠይቅ። ሐ) ሁሉም አናሳ ቡድኖች ከተቀሩት አባላት ጋር የእኩልነት ስሜት እንዲሰማቸው ለማድረግ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? መ) ከላይ የቀረቡት ስድስት ነጥቦች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰላም ለማምጣት እንዴት እንደሚያግዙ አብራራ። |

## በኃጢአት ምክንያት የሚከሰቱትን አለመግባባቶች እንዴት መፍታት እንደሚቻል።

1. በኃጢአት ምክንያት የሚከሰቱትን አለመግባባቶች ለመፍታት ሁለት መንገዶችን ልንጠቀም እንችላለን።

<u>*ዓለማዊው መንገድ*</u> ኃጢአቱን ወይም አለመግባባቱን በመሸፈን እንዳልተከሰተ አስመስሎ ማቅረብ ነው። ዓለም ምንም ዓይነት ኀፍረት እንዲፈጠር አትፈልግም። ሁለት መሪዎች በሚጣሉበት ጊዜ፣ ሌሎች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሌሎች ሰዎች ስለዚህ ችግር እንዳያውቁ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ። ወይም ደግሞ አንድ መሪ በኃጢአት በሚወድቅበት ጊዜ፣ እንዲህ ዓይነት ታላላቅ ሰዎችን ላለማሳፈር ይጠነቀቃሉ። በመሆኑም፣ ቤተ ክርስቲያን አትቀጣቸውም። ችግርን መሸፈን፣ በቁስል ላይ ጨርቅ እንደ ማስቀመጥ ነው። ቁስሉ ስለማይታይ፣ ድኗል ብለን ልናስብ እንችላለን። ነገር ግን አይድንም። ብዙም ሳይቆይ በሽታው ወደ ሌሎች የሰውነታችን ክፍሎች ይዛመታል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሎች አማኞችን ይበክላል።



<u>*መጽሐፍ ቅዱሳዊው መንገድ*</u> ኃጢአት በአማኞች ሕይወት ውስጥ መኖሩን አምኖ መቀበል ነው። ይህ በኑዛዜ አማካኝነት ኃጢአት መሥራታችንን አምነን የምንቀበልበት ነው። እግዚአብሔር ንስሐ እንድንገባ ይጠይቃል። ይህም ጥፋት መሥራታችንን አምኖ መቀበልና ለእግዚአብሔር ለመኖር መሰወጥን የሚያሳይ ነው። በተጨማሪም፣ ካሳ መክፈልን ይጠይቃል። ካሳ መክፈል አማኙ በተቻለ መጠን ኃጢአቱ ያስከተለውን ችግር ለማስተካከል ጥረት የሚያደርግበት ነው። በኃጢአቱ የተጎዱ ሰዎች የበቀል አሳባቸውን በሚተዉበት ጊዜ ይቅርታ መደረግ አለበት። በመጨረሻም፣ እርቀ ሰላም መውረድ አሰበት። ይህም በኃጢአት ምክንያት የተበላሸው ግንኙነት የሚፈወስበት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ለፈጸመው ኃጢአት ንስሐ ለመግባት የማይፈልግ ከሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ኃጢአቱን አምኖ በመቀበል ንስሐ እስከሚገባበት ጊዜ ድረስ ይፋዊ ቅጣት ትጥልበታለች።

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተለያዩ መንገዶች ሊይዟቸው የሚገቡ ሁለት ዓይነት ኃጢአቶች።

አማኞች ሁሉ ኃጢአተኞች ናቸው። ሁላችንም ኃጢአትን እንሠራለን። ነገር ግን ለኃጢአታችን የምንሰጠው ምላሽ በከፍተኛ ደረጃ ሊለያይ ይችላል። ኃጢአት መሥራትህ ታውቆህ ንስሐ ትገባለህ ወይስ ሌሎች እንዳያውቁብህ በማሰብ ትደብቀዋለህ? መሪዎች እነዚህን ሁለት ዓይነት ለኃጢአት የሚሰጡ ምላሾች ማወቅ አለባቸው። አማኞች ኃጢአትን ከሠሩ በኋላ ተጸጽተው በፍጥነት ንስሐ በሚገቡበት ጊዜ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሊራሩላቸውና ይቅርታ ሊያደርጉላቸው ይገባል። በ1ኛ ዮሐንስ 1፡9 እንደተገለጸው፣ የክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። አማኙ ንስሐ ከገባ በኋላ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጸጋና በምሕረት ችግሩን ማስተካከል ይገባቸዋል። ይህ ማለት በአብዛኛው ንስሐ የገባው አማኝ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ሊጣልበት አይገባም ማለት ነው። ነገር ግን አንድ ሰው ኃጢአት ከፈጸመ በኋላ የመጸጸትና ንስሐ የመግባት አዝማሚያ ካላሳየ፣ የእግዚአብሔር ቃል ቤተ ክርስቲያን የቅጣት እርምጃ እንድትወስድ ያዝዛል።

3. ንስሐ የማይገቡትን ኃጢአተኞች ስምን እንደምንቀጣ በግልጽ መረዳት አስብን።

የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ዓላማ መንግሥት ወንጀለኞችን ወኅኒ ቤት የሚልክበት ዓይነት አይደለም። የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ዓላማ ማስተማር ነው። ይህ ንስሐ በማይገባ መንፈስ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን የሚፈጽሙ ሰዎች የሚከፍሉት ዋጋ እንዳላቸው ስሌሎች አማኞች በማሳየት ከኃጢአት እንዲቆጠቡ በማበረታታት ላይ ያተኮረ ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ይህ ቅጣት ኃጢአተኛው ራሱ ከክርስቶስ አካል በመለየቱ ምክንያት የመነጠል ስሜት ተሰምቶት በንስሐ ተመልሶ በክርስቶስ የተሰጠውን ይቅርታ እንዲያገኝ የሚያደርግ ነው (ገላ. 6:1-2ን አንብብ)። ጳውሎስ ይህንን መደበኛ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት «ስሰይጣን አሳልፎ መስጠት» ሊል ይገልጸዋል። (1ኛ ቆሮ. 5:5፤ 1ኛ ጢሞ. 1:20ን አንብብ።) ይህ ግለሰቡ ፍቅርና የመንፈስ ቅዱስ ጥበቃ ካለበት የአማኞች ኅብረት በመለየቱ ለሰይጣን ጥቃት ሊጋለጥ በሚችልበት ስፍራ መሆኑን የሚገነዘብበት ነው። ነገር ግን ጳውሎስ እንዳለው፣ ይህ እርምጃ የሚወሰደው በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዳይሠሩ ለማበረታታት ነው።

22ኛ ጥያቄ:- ሀ) በቤተ ክርስቲያናችሁ በአማኞች ላይ ቅጣት ሲሰጥ አይተህ ታውቃለህ? የተፈጸመው ኃጢአት ምን ነበር? ሽማግሌዎች ምን ዓይነት ቅጣት ጣሉ? ለ) የቅጣቱ ዓላማ ግለሰቡ ንስሐ እንዲገባ ለማበረታታት ነበር ወይስ ለመቅጣት? ሐ) ሌሎች ሰዎችን በመፍራት ቅጣት ሳይጣል የቀረበት ጊዜ ነበር? ይህ የሽማግሌዎች ውሳኔ አስተዋይነት የታከለበት ይመስልሃል? መልስህን አብራራ።

4. መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቷል የሚል ጥርጣሬ በሚኖረን ጊዜ ምን ማድረግ እንዳለብን ግልጽ ነጥቦችን ያስቀምጣል። አንድ ወንድም ወይም እኅት በዐመፀኝነት ኃጢአት መሥራቱን ሲቀጥልና ንስሐ አልገባም ሲል መደረግ ካለባቸው ነገሮች ጥቂቶቹ ከዚህ በታች የቀረቡ ናቸው።

ሀ. እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አማኞች በግልጽ ኃጢአት በሚሠሩበት ጊዜ እንድናጋፍጣቸው ያዘዘን መሆኑን ማስታወስ አለብን። የእግዚአብሔር ቃል ኃጢአትን እያየን ዝም እንድንል ወይም እንድንሸፋፍን አይፈቅድልንም። ይልቁንም፣ ወደ



ኃጢአተኛው በመሄድ ንስሐ እንዲገባና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ማበረታታት አለብን። (ገላ. 6:1-2ን አንብብ።) ኃጢአትን መሸፋፈን ማለት ትንሹ እርሾ ጠቅላላውን ሊጥ እንደሚያቦካ ሁሉ፣ ችግሩ ወደ ሌሎች አማኞች እንዲዳረስ ማበረታታት ማለት ነው (1ኛ ቆሮ. 5:6-8)። ኃጢአትን የማናጋፍጥ ከሆነ፣ ይህ ፍቅር እንደሌለን የሚያሳይ ነው። አንድን ሰው የማናጋፍጥ ከሆነ፣ ግለሰቡ በያዘው የዐመፀኝነት መንገድ በመሄድ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዲቀበል እናደርጋለን።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ በትላልቅና ትናንሽ ኃጢአቶች መካከል እምብዛም ልዩነት አያደርግም። መጽሐፍ ቅዱስ ቅጣት ሊጣልባቸው የሚገባ ትላልቅ ኃጢአቶች (ለምሳሌ፣ ዝሙት፣ የአልኮል መጠጥ) እና በቸልታ መታለፍ ያለባቸው ትናንሽ ኃጢአቶች (ለምሳሌ፣ ቁጣ፣ ትዕቢት፣ ኅሰኝነት) እንዳሉ አያሳይም። አማኞች ንስሐ በማይገባ መንፈስ የሚፈጽሙት ማንኛውም ኃጢአት ቅጣት ሊጣልበት ይገባል። እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን መጥፎ ናቸው ብላ በምታስባቸው አንዳንድ ኃጢአቶች ብቻ ሳይሆን፣ በሁሉም የሕይወታችን ክፍሎች ቅዱሳን እንድንሆን ይፈልጋል።

23ኛ ጥያቄ:- ሀ) ብዙውን ጊዜ አማኞች ቅጣትን ማስከተል ያለባቸው ትልልቅ ኃጢአቶች ናቸው የሚሏቸውን ነገሮች ዘርዝር። ለ) አማኞች አነስተኛ ኃጢአቶች ናቸው በማለት ብዙም ትኩረት የማያደርጉባቸው ኃጢአቶች የትኞቹ ናቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ንስሐ ባልተገባባቸው ኃጢአቶች ሁሉ ላይ ቅጣት የሚጥሉ ቢሆን፣ ይህ የቤተ ክርስቲያንን የቅጣት አሰጣጥ እንዴት እንደሚቀይር ግለጽ።

ሐ. እንደ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ በቂ ምርመራ ተደርጎ እውነትነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ፣ አንድ ሰው በኃጢአት እየኖረ ነው የሚባለውን ወሬ መቀበል የለብንም። አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቷል የሚል ወሬ በመስማታቸው ብቻ መሪዎች ቅጣት የሚጥሉባቸው ጊዜያት አሉ። (ማስታወሻ:- እውነትነቱን ለማጣራት ሳይሞክሩና ንስሐ የሚገባበትን መንገድ ሳያመቻቹ አንድ ሰው ኃጢአት ሠርቷል የሚል ወሬ ሰምቶ ብቻ ቅጣት

መጣሉ የሐሜተኛነት ኃጢአት ተካፋይ መሆን ነው፡፡) መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ወይም ቢቻል ሦስት ምስክሮች ሳይመሰክሩ፣ በማንም ሰው በተለይም በቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ቅጣት መጣል እንደማይገባ ይነግረናል፡፡ አንድ ምስክር ብቀላ የፈለገ ሰው ሊሆን ስለሚችል፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጉዳዩን በጥልቀት በመመርመር እውነቱን ማግኘት አለባቸው፡፡ መሪዎች ግለሰቡ ጥፋተኛ ለመሆኑ መቶ በመቶ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ሁሉንም ነገር የሚያውቀው አምላክ ይፈርድበት ዘንድ ነገሩን አሳልፈው ሊሰጡ ይገባል፡፡

መ. የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጉዳዩ ውስጥ ከመሳተፋቸው በፊት፣ በግለሰቡ ላይ ቅጣት ለመጣል እንዲፈልጉ የሚያደርግ ትክክል ያልሆነ ልባዊ ፍላጎት እንዳላቸው ራሳቸውን መመርመር አለባቸው፡፡ ኃጢአተኛውን በምናጋፍጥበት ጊዜ ትክክለኛ ያልሆነ ልባዊ ፍላጎት ካለን፣ ራሳችን በኃጢአት እንወድቃለን (ገላ. 6:1)፡፡ ከእርሱ የተሻልኩ ነኝ የሚል አሳብ ካለን፣ ስላልታዘዘን ተናደን ከሆነ፣ ከቀናንበት፣ ከተናደድንበት፣ ወይም የሌላ ጎሳ አባል በመሆኑ ልንቀጣው ብንፈልግ፣ ግለሰቡን የመጋፈጥ መብት የለንም፡፡ መጀመሪያ በራሳችን ሕይወት ውስጥ ያለውን ኃጢአት መሳ ማለት አለብን፡፡ ግለሰቡን መጋፈጥ ያለበት ሌላ ሰው ሊሆን ይገባል፡ እንደ ፈራጅ ሳይሆን፣ በእውነተኛ ፍቅር ለግለሰቡ በማሰብ መጋፈጥህን አረጋግጥ፡፡ ኃጢአተኛን በማጋፈጡ ተግባር ውስጥ መሳተፍ ያለብን ብቸኛው ምክንያት ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ ምክንያት የተዘጋጀለትን በረከት እያጣ ነው የሚል ግንዛቤ ካለን ብቻ ሊሆን ይገባል፡፡

ሠ. አንድ ሰው እንደ በደለን ወይም ኃጢአት ሠርቶ እንዳልተናዘዘ በምናውቅበት ጊዜ፣ መጀመሪያ ሌላ ሰው ሳንጨምር ራሳችን ችግሩን ለመፍታት መጣር አለብን፡፡ መጀመሪያ አንድ ሰው በግል ሳይጋፈጠው በፊት ጉዳዩ ለቅጣት ወደ ሽማግሌዎች መሄድ የለበትም፡፡ ስለ ኃጢአቱ ለሌላ ሰው የመናገር መብት የለንም፡፡ መጀመሪያ ወደ ግለሰቡ በመሄድ ስለ ጉዳዩ ፊት ለፊት ሳንወያይ ለሽማግሌዎች መናገር የለብንም፡፡ (ማቴ. 18:15ን አንብብ፡፡) ለሌላ



ሰው መናገር ማለት ቀደም ሲል በተፈጸመው ኃጢአት ላይ የሐሜትን ኃጢአት መጨመር ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ እኛንም ኃጢአተኞች ያደርገናል፡፡

በአንድ ሰው ሕይወት ውስጥ ኃጢአትን ከተመለከትን፣ እግዚአብሔር እንድንሳተፍበት ይፈልግ እንደ ሆነ መጠየቅ አለብን፡፡ ለግለሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ኃላፊነት ያለን መሪ ከሆንን፣ የግድ መሳተፍ አለብን፡፡ መሪዎች ካልሆንንና ግለሰቡንም በደንብ የማናውቀው ከሆነ፣ ከመጸለይ አልፈን ባንሳተፍ የተሻለ ነው፡፡ ከእኛ ጋር ግንኙነት የሌለውን ሰው መጋፈጡ እምብዛም ውጤታማ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ለእርሱ ካለን ፍቅር የመጣ ሳይሆን፣ ክስ ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ግለሰቡን እንድትጋፈጠው እንደሚፈልግና መቼ እንድትጋፈጠው እንደሚፈልግ ማረጋገጥ አለብህ፡፡ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁሉንም ሰው ኃጢአት ሠርተሃል እያልን እንድንወቅስ መብት አይሰጠንም፡፡ ይህ ጉዳዩን የከፋ እንጂ የተሻለ አያደርገውም፡፡

24ኛ ጥያቄ፡- ሀ) የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች እነዚህን በፈቃደኝነት ኃጢአት የሚሠራን ሰው ለመጋፈጥ የሚያግዙትን አምስት ነጥቦች እንዴት ቸል እንደሚሉ ምሳሌዎችን በመስጠት አብራራ፡፡ ለ) አማኞች ለኃጢአታቸው ንስሐ እንዲገቡ ለማድረግ በምንሞክርበት ጊዜ፣ እነዚህን አምስት መርሖዎች ሳንጠቀም ስንቀር ምን እንደሚከሰት ግለጽ፡፡

ረ. አንድ ሰው ኃጢአት ከሠራ በኋላ ንስሐ ለመግባት እንደማይፈልግ ተጨባጭ መረጃ በሚኖርበት ጊዜ፣ መወሰድ ስላለባቸው ደረጃዎች ክርስቶስ በግልጽ አስተምሯል፡፡ እነዚህን ደረጃዎች መከተል ያለብን እንደ ስካር ወይም ዝሙት ላሉ ኃጢአቶች ብቻ ነው የሚል አሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም፡፡ ይልቁንም፣ ንስሐ መግባትን በማይፈልግ መንፈስ የተደረገ ማንኛውም ኃጢአት በዚህ መንገድ መስተናገድ አለበት፡፡ ኃጢአቱ ሐሜት፣ ውሸት፣ ቁጣ፣ ሚስትንና ልጆችን መደብደብ፣ መስረቅ፣ ወዘተ. . . ሊሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአትን ከባድና ቀላል ብሎ በመከፋፈል የትኞቹን መቅጣትና የትኞቹን

አለመቅጣት እንዳለብን አይናገርም:: ዋናው የልብ ጉዳይ ነው:: ክርስቲያኖች በሁሉም የሕይወት ክፍላቸው በቅድስና ሰመኖር ከፈለጉ፣ ስለ ፈጸሙት ኃጢአት በፍጥነት ንስሐ ይገባሉ:: ዐመፀኞች ከሆኑ ግን፣ ኃጢአቱ ምንም ሆነ ምን፣ ቤተ ክርስቲያን እርምጃ መውሰድ አለባት::

*(ማስታወሻ፡- ምንም እንኳን በባህላችን አንድን ሰው በቀጥታ ለኃጢአቱ ከመጋፈጥ ይልቅ ሽማግሌዎችን የምንልክ ብንሆንም እንኳን፣ የእግዚአብሔር ቃል ንስሐ ያልተገባበት ኃጢአት ችግር በሚፈጥርበት ጊዜ ግለሰቡን በመጋፈጥ መፍትሔ ማምጣት እንዳለብን ይናገራል:: ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚጣሉ ከሆነ፣ እርቅ መፈጠር አለበት::)*

ለ. ቀጥሰው ያሉትን ደረጃዎች ሳትክተል ቤተ ክርስቲያን የቅጣት እርምጃ መውሰድ የለባትም፡-

1) ኃጢአቱን የሚያውቅና ስለ ጉዳዩ የመነጋገር ኃላፊነት ያለው ሰው (እንደ ጓደኛ ወይም እንደ ሽማግሌ) በግል ደረጃ ከግለሰቡ ጋር መነጋገር አለበት:: ስለዚህ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ማንም ሰው ማወቅ የለበትም:: የኃጢአትን መኖር ያረጋገጠው ግለሰብ ወደ ኃጢአተኛው በመሄድ ማነጋገር አለበት:: ኃጢአተኛው ንስሐ ከገባ፣ ችግሩ የትም ሳይሄድ እዚያው ያከትማል:: ኃጢአቱ የአማኞችን ጠቅላላ ማኅበረሰብ የጎዳና ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ካልሆነ በቀር ወደ ሽማግሌዎችም እንኳን መሄድ የለበትም::

አንድን አማኝ በምንጋፈጥበት ጊዜ፣ ወደ ቤቱ ከመሄዳችን በፊት ስለ ሕይወቱና ስለ ሁኔታው ግንዛቤ ማግኘቱ አስፈላጊ ነው:: በኃጢአቱ ላይ ብቻ ማተኮር አያገባም:: ወደ ኃጢአቱ የመራው አንተ የማታውቀው ነገር ነበር? ለምሳሌ ያህል፣ ባል ሚስቱን ሲደበድባት በመኖሩ ምክንያት ከሌላ ሰው ጋር የፍቅር ግንኙነት ከጀመረች፣ መታየት ያለበት የእርሷ አመንዝራነት ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱ ደብዳቢነትም ጭምር ነው:: መሪው ግለሰቡ ለክርስቶስ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ማወቁም ጠቃሚ ነው:: ለክርስቶስ ስለሚያከናውነው ጥሩ ተግባር በማመስገን መጀመሩ ተገቢ ነው::



ለኃጢአቱ አስተዋጽኦ አድርጎ ይሆናል ብለህ ስለምታስበው ነገር አናግረው:: ከዚያም በፈቃደኝነት ወደተፈጸመው ኃጢአት እምራ:: በራእይ ምዕራፍ 2-3 ክርስቶስ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን ስለ ኃጢአታቸው በወቀሰ ጊዜ ንግግሩን የጀመረው ስለ ጥፋታቸው በመናገር ሳይሆን፣ ስለ ጥሩ ሥራቸው በማመስገን ነበር:: ኃጢአታቸውን ባይደብቀውም፣ ይህንኑ ችግር የተመለከተው በሕይወታቸው ዐውድ ውስጥ ነበር::

ግልጽ አሳብ ባለመናገርህ ምክንያት ሰዎች ለማለት የፈለግከውን በተሳሳተ መንገድ እንዳይረዱ ተጠንቀቅ:: በአመዛኙ ወቀሳውን በግልጽ ቃላት አናወጣውም:: ይህ ጥሩ ነገር ሊመስል ቢችልም፣ ሁለት ችግሮችን ያስከትላል:: በመጀመሪያ፣ ግለሰቡ ምን አጥፍተሃል ተብሎ እንደ ተወቀሰ ለማወቅ ይቸገራል:: ምን ዓይነት ወቀሳ እንደ ተሰነዘረበት ሳያውቅ እየተነገረ ያለውን ነገር እንዴት ሊገመግም ይችላል? <u>ሁለተኛ</u>፣ ግልጽ ያልሆኑ ቃላት የግለሰቡን ተግባር ክፉነት ይደብቃሉ:: ኃጢአት ብዙውን ጊዜ ጥሩ ነገር ሊመስል ይችላል:: ዳዊት ኃጢአቱን አውቆ ንስሐ እንዲገባ ናታን የመመኘትን ክፋት የሚያስረዳ ታሪክ እንደ ተናገረ ሁሉ (2ኛ ሳሙ. 12)፣ እኛም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ምን ያህል ክፉ ነገር እንደ ሆነ ማሳየት አለብን:: በዚህ መንገድ መንፈስ ቅዱስ ለግለሰቡ ኃጢአተኛነቱን በማሳየት ወደ ንስሐ ይመራዋል::

2) ግለሰቡ ኃጢአት ሠርቶ ንስሐ አለመግባቱ ከተረጋገጠ፣ ጉዳዩ በትክክል መመርመሩንና የኃጢአቱን አስከፊነት ለማሳየት ቀጣዩ እርምጃ አንድ ወይም ሁለት ምስክሮችን ማምጣት ነው:: ብዙውን ጊዜ እነዚህ ምስክሮች የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይሆናሉ:: አሁንም ኃጢአቱን በማሳየትና ንስሐ እንዲገባ በማበረታታት በገርነት ግለሰቡን መጋፈጥ ያስፈልጋል:: ግለሰቡ ንስሐ ከገባ፣ እና አስፈላጊ ከሆነና ካሳም ከከፈለ፣ ጉዳዩ በይቅርታ ማክተም አለበት::

3) አሁንም ግለሰቡ ንስሐ ለመግባት ካልፈለገ፣ ወደ ሽማግሌዎችና ከዚያም ወደ ጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ምእመናን መድረስ አለበት:: ሽማግሌዎች ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳይገቡ

የማቴዎስ ምዕራፍ 18ን ደረጃዎች እንደ ተከተሉና ግለሰቡን ወደ ንስሐ ለማምጣት ጥረት እንዳደረጉ ለምእመናን በሙሉ መግለጽ አለባቸው፡ ነገር ግን ግለሰቡ ንስሐ ለመግባት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት እንዲወጣና «ክርስቲያን እንዳልሆነ ሰው» እንዲታይ ይናገራሉ:: ይህ ማለት ላልዳኑት ሰ ዎች ፍቅርን እንደምናሳይ ሁሉ ለእርሱም ፍቅርን እንነፍገውም:: ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥቶ የአምልኮ ፕሮግራሞችን መካፈል ይችላል:: ምክንያቱም ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎችም የአምልኮ ፕሮግራማችን ላይ የመገኘት መብት አላቸውና:: ነገር ግን እንደ ቤተ ክርስቲያን ቤተሰብ የኅብረቱ አካል አይሆንም:: (ማስታወሻ:- የቤተ ክርስቲያን ቅጣት እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ እንዲካሄድ ቤተ ክርስቲያን እንደሚዋደዱ ቤተሰቦች ሆና መኖር አለባት:: በሚወደው አባቱ መቀጣቱ አንድን ልጅ እንደሚጎዳው ሁሉ፣ የቤተ ክርስቲያን ቅጣትም ውጤታማ የሚሆነው አፍቃሪ የሆነችው የክርስቶስ አካል እርምጃውን ስትወስድ ነው:: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙም ፍቅር ከሌለ፣ ግለሰቡ እግዚአብሔር በቅጣቱ ውስጥ እንዲማር የሚፈልገውን ነገር ሳይማር በቀጥታ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ሊሄድ ይችላል:: ይሁንና፣ ግለሰቡ ወደ ሌ ላ የወንጌል አማኝ ቤተ ክርስቲያን ከሄደ፣ ቅጣት የጣሉት ሽማግሌ ዎች ስለ ሁኔታው ለሄደባት ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማሳወቅ አለባቸው::)

ጳውሎስ ይህንን ሂደት «ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት» ይለዋል:: ይህን ሲል ግለሰቡን መንፈስ ቅዱስ መሪና ጠባቂ ከሆነበት የአማኞች ኅብረት በማስወጣት፣ ሰይጣን በግለሰቡ ላይ ፍርድ (ምናልባትም በሽታ) እንዲያመጣ መፍቀዳቸውን መግለጹ ነበር:: በዚህ ጊዜ ግለሰቡ በንስሐ ሊመለስ ይችላል:: ሰይጣን እግዚአብሔር ግለሰቡን ወደ ንስሐ ለማምጣት የሚጠቀምበት መሣሪያ ይሆናል ማለት ነው:: ክርስቲያኖች ከዐመፀኛ ኃጢአተኛ ጋር አብረው እንዳይመገቡ (የቅርብ ግንኙነት እንዳይኖራቸው) ታዝዘዋል (1ኛ ቆሮ. 5:9-13)::



25ኛ ጥያቄ:- አንተ ሽማግሌ ነህ እንበል:: በቤተ ክርስቲያናችሁ አንድ ሰው ሐሜትን በማስፋፋት የቤተ ክርስቲያንን አንድነት በማናጋት ላይ ነው:: እነዚህን የመጋፈጥ ደረጃዎች በመጠቀም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ የዚህን ግለሰብ ኃጢአት እንዴት ወደ ንስሐ ለማምጣት እንደምትሞክር ግለጽ:: ለ) ፍትሐዊ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የማይከተሏቸው ደረጃዎች ምን ምንድን ናቸው? ሐ) የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ቸል ሲባል ወይም በፍትሐዊ መንገድ ሳይሰጥ ሲቀር ምን ይከሰታል?

5. መደበኛ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት በሽማግሌዎች ስብሰባ ውስጥ ከሚደበቅ ይልቅ፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በግልጽ መሰጠት አለበት:: ይህ የሚሆነው ለሁለት ምክንያቶች ነው:: <u>አንደኛ</u>፣ ኃጢአትን በግልጽ የማናርም ከሆነ፣ በስፋት በመሰራጨት አማኞች እግዚአብሔርን ወይም ኃጢአትን የማይፈሩበት ሁኔታ ይፈጠራል:: <u>ሁለተኛ</u>፣ ችግሩ በድብቅ የሚስተናገድ ከሆነ፣ መ ረጃውን ያላገኙ ሰዎች ማማት፣ ወገንተኛ አቋም መያዝ፣ ሽማግሌ ዎችን መውቀስና ቤተ ክርስቲያን እንድትከፋፈል ሊያደርጉ ይችላሉ::

6. የቤተ ክርስቲያን መሪም ኃጢአት በሚፈጽምበት ጊዜ፣ በጥንቃቄ ቅጣት ሊጣልበት ይገባል:: ጳውሎስ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች እስካልተረጋገጠ ድረስ በአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ላይ ወቀሳ መሰንዘር እንደሌለበት ያስረዳል:: ኃጢአት መሥራቱ ከተረጋገጠ በኋላ፣ ቅጣቱ መሰጠት ያለበት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው (1ኛ ጢሞ. 5:19-20):: የቤተ ክርስቲያን መሪውን ስም ለመጠበቅ ሲባል በምሥጢር እንዲቀጣ መደረግ የለበትም:: ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ዓይነት ጥበቃ እንደሚደረግላቸው በሚያውቁበት ሰዓት፣ ክፍፍል ሊፈጠር ይችላል:: የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ንስሐ ያልገባውን ሽማግሌ የማይቀጡ ከሆነ፣ ሌሎችን ለመቅጣት መብት የላቸውም:: አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ ገንዘብ ሰርቆ ወይም ሌላ ኃጢአት ፈጽሞ ሳይቀጣ ሊቀር እንደሚችል ካወቀ፣ ሌሎች አማኞችም ልክ እንደ እርሱው ኃጢአት ለመሥራት ሊደፋፈሩ ይችላሉ:: እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ከሌሎች አማኞች በላቀ ኃላፊነት

ይጠይቃቸዋል፡፡ በመሆኑም፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ቅጣት ሊጣልባቸው ይገባል፡፡ ቅጣቱም መሪ ባልሆነ አማኝ ላይ ከሚጣለው ከፍ ያለ መሆን አለበት፡፡

7. የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለመወያየት ከሚገደዱባቸው ከባባድ ጉዳዮች አንዱ የኃጢአት ኑዛዜ መቼ በግል መቼ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን ምእመናን ፊት መፈጸም እንዳለበት ነው፡፡ ሁሉም ክርስቲያኖች ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መናዘዝ አለባቸው? ይህን ብናደርግ፣ ኃጢአታችንን ይቅር የሚለውን መሐሪ አምላክ ለማምለክ የሚተርፍ ጊዜ አይኖረንም፡፡ መሪዎች መከተል ያለባቸው መርሕ «ኃጢአቱ በሕዝብ ፊት የሚታወቅ ከሆነ፣ ንስሐውም በሕዝብ ፊት መደረግ አለበት፣» የሚል ሊሆን ይገባል፡፡ አንድ ሰው በወሲብ ኃጢአት መውደቁን የሚያውቅ ሰው ከሌለ፣ ግለሰቡ በግሉ ለእግዚአብሔር ኃጢአቱን ተናዝዞ ይቅርታ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሽማግሌዎች ብቻ ስለ ኃጢአቱ የሚያውቁ ከሆነ፣ ኑዛዜው በሽማግሌዎች ፊት መደረግ አለበት፡፡ ወይም ደግሞ የቤተ ክርስቲያን አባላት በሙሉ ስለተፈጸመው ኃጢአት የሚያውቁ ከሆነ፣ ወይም የኃጢአቱ ውጤ ት የሚገለጽ ከሆነ (ለምሳሌ፣ ዝሙት ከተፈጸመ በኋላ ልጅቱ አርግዛ ልትወልድ ትችላለች)፣ ኑዛዜው ይፋዊ መሆን አለበት፡፡ ወይም ደግሞ «ኃጢአቱ» የተፈጸመው በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ምእመናን ላይ ከሆነ፣ ኑዛዜው በሁሉም ምእመናን ፊት መፈጸም አለበት፡፡ ለምሳሌ፣ አንድ ሽማግሌ ከምጽዋቱ ገንዘብ ከሰ ረቀ፣ ከጠቅላላው ቤተ ክርስቲያን ገንዘብ ስለሆነ የሰረቀው፣ ኃጢአቱን በቤተ ክርስቲያን ፊት መናዘዝ አለበት፡፡

8. አማኞች ለቤተ ክርስቲያን ቅጣት መጠቀም ያለባቸው መሣሪያ ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት የሚፈጸመው ንስሐ ለመግባት ካልፈለገው አማኝ ጋር የነበረውን ግንኙነት በማቋረጥ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ግለሰቡ ልጃችን፣ ዘመዳችን ወይም የጎሳችን አባል ቢሆን ለውጥ የለውም፡፡ አማኙ በእግዚአብሔር ላይ የሚያምፅ ከሆነ፣ ከእርሱ ጋር የቅርብ ግንኙ ነት ከመፈጸም መቆጠብ አለብን፡፡ ንስሐ ካልገባው ሰው ጋር ግንኙ



ነት ማድረግ የኃጢአቱ ተካፋይ መሆን ነው፡፡ ይህ ከአማኞች ጋር ኅብረት እንዳያደርግ በመከላከል መንፈስ ቅዱስ በሕይወቱ ውስጥ እንዳይሠራ ያደርጋል፡፡ ምንም እንኳን የቁጣ ምልክት ማሳየት ባይኖርብንም፣ ግለሰቡ ከክርስቶስ አካል ጋር ኅብረት እንደሌለው በግልጽ ማሳየት አለብን፡፡

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ሁለት «የተለመዱ» መሣሪያዎች እንድንጠቀም አያዝዘንም፡፡

በመጀመሪያ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግለሰቡ በቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ እንዳይገባ አይከለክለውም፡፡ የማያምኑ ሰዎች ፕሮግራሞቻችንን እንዲካፈሉ እንፈቅዳለን፡፡ ግለሰቡም የአምልኮ ፕሮግራሞችን እንዲካፈል መፍቀድ አለብን፡፡ ምናልባትም መንፈስ ቅዱስ ስብከቱን በመጠቀም ወደ ንስሐ ሊመራው ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ በእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ላሉት ሰዎች የምንሰጠውን የተሟሟቀ ፍቅር አንሰጠውም፡፡

ሁለተኛ፣ ቤተ ክርስቲያን የጌታ እራት አለመብላትን የቅጣት መሣሪያ ማድረግ እንዳለበት የሚያመለክት አሳብ ፈጽሞ አናገኝም፡፡ በርግጥ፣ አማኞች ሁሉ በሕይወታቸው ውስጥ ያለውን ኃጢአት ሁሉ ሳይናዘዙ የጌታን እራት መውሰድ የለባቸውም፡፡ የጌታን እራት ለመውሰድ በፍጥነት ለኃጢአታቸው ይቅርታ መጠየቅና ንስሐ መግባት (አኗኗራቸውን መቀየር) አለባቸው፡፡ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ውስጥ ማን የጌታን እራት መውሰድ እንዳለበትና ማን መውሰድ እንደሌለበት ሐዋርያት በዳኝነት መወሰናቸውን የሚያሳይ መረጃ አናገኝም፡፡ እንዲሁ ደግሞ፣ አንድ ሰው የቅጣት ጊዜውን እስኪጨርስ ድረስ የጌታን እራት እንዳይወስድ የተ ከለከለበትን ስፍራ አናገኝም፡፡ ሰዎች ለኃጢአታቸው ንስሐ እስክ ገቡበት ጊዜ ድረስ፣ ሁሉም አማኞች የጌታን እራት ሊወስዱ ይችላሉ፡፡

9. ኃጢአታችንን ተናዘዝን ማለት አሉታዊ የኃጢአት መዘዞች አይደርሱብንም ማለት አይደለም፡፡ በርግጥ፣ የቤተ ክርስቲያን ቅጣት ዓላማ ማስተማር እንጂ መጉዳት አይደለም፡፡

እግዚአብሔር ይቅር ስላላቸው፣ ቤተ ክርስቲያንም ኃጢአተኞችን ይቅር ማለት አለባት:: ይሁን እንጂ፣ አሉታዊ ውጤት የሚያስከትሉ አንዳንድ ኃጢአቶች አሉ:: የዝሙት ኃጢአትን መናዘዝ ወሲብ የፈጸመች ሴት ያረገዘችውን ልጅ እንዳትወልድ እንደማያደርግ ሁሉ፣ የራሳቸውን አሉታዊ መዘዝ የሚያስከትሉ ኃጢአቶች አሉ:: ኃጢአታቸውን ያለመናዘዝ ታሪክ ያለባቸውን ሰ ዎች ኃጢአታቸውን እስኪናዘዙና ንስሐቸውን በተግባር እስኪያሳዩ ድረስ በቤተ ክርስቲያን ቅጣት ሥር ማኖሩ ተገቢ ሊሆን ይችላል:: መለወጡ ከተረጋገጠ በኋላ ከቅጣት ወጥቶ ወደ ኅብረት እንዲገቡ መደረግ አለበት:: ቤተ ክርስቲያን ፈራጅ ሳትሆን ደግና ይቅር ባይ ማኅበረሰብ ልትሆን ይገባል:: ቤተ ክርስቲያን ቅድስናን ከአፍቃሪነት ጋር ሚዛናዊ ማድረግ አለባት:: ቅድስና ኃጢአትን የምትጸየፍ ማኅበረሰብ እንድትሆን ሲያስችላት፣ አፍቃሪነት ደግሞ ንስሐ የገቡ ኃጢአተኞች ኃጢአትን የሚጠላውንና ዳሩ ግን ኃጢአተኞችን ይቅር የሚለውን አምላካቸውን ለማምለክ የሚሰባሰቡ ማኅበረሰቦች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል::

ቀጣይነት ያለው የኃጢአት መዘዘዝ የሚታወቀው በተለይ በመሪ ዎች ኃጢአት ነው:: ለምሳሌ፣ አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ የወሲብ ኃጢአት ወይም ስርቆት ከፈጸመ በኋላ ንስሐ ቢገባ፣ ይቅርታ ሊደረግለት ይገባል:: ከይቅርታው መካከል የወሰደውን ገንዘብ መመለስ አንዱ ይሆናል:: ከዚህም በላይ፣ የመሪነት ቦታውን ያጣል:: የመሪነት ቦታውን የሚያጣው ቤተ ክርስቲያን ልትቀጣው ስለምትፈልግ ሳይሆን፣ «ነቀፋ የሌለው» ባለመሆኑ ምክንያት ነው:: ይህ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር ቅድመ-ሁኔታዎች አንዱ ነው (1ኛ ጢሞ. 3:2)::

**10.** አንድ ሰው በቅጣት መቆየት ያለበት ለምን ያህል ጊዜ ነው? መጽሐፍ ቅዱስ አንድን ሰው ይህን ያህል ጊዜ እንድንቀጣው አይነግረንም:: ወሲባዊ ኃጢአት የፈጸመ ሰው ቅዱስ ቁርባን እንዳይወስድ በመከልከል ለስድስት ወራት እንድንቀጣው አልታዘዝንም:: እንዲሁም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብ የሰረቀ መሪ ለስድስት ወራት ከመሪነቱ መታገድ አለበት አይልም::



መጽሐፍ ቅዱስ የቅጣቱ ጊዜ በሁለት ነገሮች ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል::

በመጀመሪያ፣ ኃጢአት የፈጸሙት ሰዎች ንስሐ መግባታቸውን በተለወጠ ባሕርይ አሳይተዋል ወይ? በ1ኛ ቆሮንቶስ 5፣ ጳውሎስ በዝሙት ውስጥ የሚኖር አማኝ መቀጣት እንዳለበት ገልጾአል:: ነገር ግን ግለሰቡ ንስሐ መግባቱን ከሰማ በኋላ፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 2:1-11ን ሲጽፍ፣ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኅብረት እንድትመልሰው አዝዟል:: ስለዚህ፣ ግለሰቡ የተቀጣው በተለወጠ ሕይወት ንስሐ መግባቱን እስኪያሳይ ድረስ ነው ማለት ነው:: ይህም አንድ ሰው ንስሐ ካልገባ፣ ቅጣቱ እስከ ሁለት ዓመታት ሊቆይ እንደሚችልና ንስሐ ገብቶ መለወጡን ካሳየ ደግሞ፣ የአንድ ሳምንት ጊዜ ሊሆን እንደሚችል ያመለክታል::

ሁለተኛ፣ አንድ መሪ ኃጢአት በሚሠራበት ጊዜ፣ «ነቀፋ የሌ ለው» የሚለውን መመዘኛ ስለማያሟላ (1ኛ ጢሞ. 3:2) የመሪነት መብቱን «አጥቷል»:: መሪው መንፈሳዊ ዝናውን ካላገኘና በቤተ ክርስቲያንና በዓለም ዳግም «ነቀፋ የሌለው» ሆኖ ካልተገኘ፣ በመሪነት ሊያገለግል አይችልም:: ይህ እንግዲህ ከቅጣት ይልቅ እርሱ የመሪነት መመዘኛ ያለማሟላቱ ጉዳይ ነው:: «ነቀፋውን» ከመሪዎች ሊያነሣ የሚችለው ጊዜና ቀጣይነት ያለው መንፈሳዊ ባሕርይ ብቻ ነው:: ሰዎች እንደገና ምሳሌያዊ መሪ አድርገው የሚያከብሩት ከብዙ ዓመታት ወይም ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ሊሆን ይችላል:: ዳግም ለመሪነት ሊበቃ የሚችለው የመንፈሳዊነት ዝናውን መልሶ ካገኘ በኋላ ብቻ ነው::

ነገር ግን አማኞች ያለፈውን ታሪክ ሁልጊዜም ማስታወስ የለባቸውም:: አንዳንድ ጊዜ አማኞች «ከሃያ ዓመታት በፊት የወሲብ ኃጢአት ስለ ፈጸመ መሪ ሊሆን አይችልም፣» የሚሉበት አጋጣሚ አለ:: እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ይቅር ባይ ማኅበረሰብ አለመሆናችንን ያሳያል:: ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር በማለት እንደገና እንድናገለግለው ዕድል እንደሚሰጠን እንደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለንም ማለት ነው:: አንድ ሰው ቀደም ሲል ኃጢአት

ቢሠራም፣ ቀጣይነት ያለው ክርስቲያናዊ እድገትና መንፈሳዊነት ካሳየ፣ እንደገና ልናምነው ይገባል።

26ኛ ጥያቄ:- በማኅበረ ምእመንና ውስጥ ኃጢአትን ለማረም የተሰጡትን መርሖዎች ተመልሰህ ከልሳቸው፡ ሀ) ቤተ ክርስቲያን ከእነዚህ መርሖዎች መካከል በሚገባ ተግባራዊ የምታደርገው የትኞቹን ነው? ለ) ቤተ ክርስቲያናችሁ በሚገባ ተግባራዊ የማታደርገው የትኞቹን መርሖዎች ነው?

## ሦስተኛ ቀን

## ከአስተምህሯዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙትን ግጭቶች መፍታት።

የሚያሳዝነው፣ በታሪክ ሁሉ በአማኞች መካከል ከታዩት መራራ አለመግባባቶች አብዛኞቹ በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተ ምህሮዎች ግንዛቤ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ይህ ለመረዳት የሚቸግር ነገር አይደለም። በብሉይ ኪዳንና በቀድሞይቱ ቤተ ክርስቲያን ሳይቀር የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ነበሩ። እነዚህንም አስተማሪዎች መከላከል የግድ ነበር። ጳውሎስ ከጻፋቸው ጠንካራ ቃላት አብዛኞቹ በሐሰተኛ አስተማሪዎች ላይ የተሰነዘሩ ነበሩ። እንዲያውም፣ ለገላትያ አማኞች አንድ ሰው እውነተኛ የሆነውን ወንጌል ካላስተማረ፣ ወደ ሲኦል እንዲወርድ ተናግሯል (ገላ. 1:6-9)። ጳውሎስ ለኤፌሶን አማኞች ከአማኞች እንዲያውም ከሽማግሌዎች መካከል ሐሰተኛ ትምህርቶችን የሚያስተምሩ ሰዎች እንደሚነሡ ነግሯቸዋል። እንደ ሽማግሌዎች የራሳቸውን እምነትና የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ ያስፈልጋቸው ነበር (የሐዋ. 20:28-31)። ሁልጊዜም ሐሰተ ኛ ትምህርት ወይም ሚዛናዊ ያልሆነ እውነት የሚያስተምሩ ሰዎች መኖራቸው ስለማይቀር፣ ሁልጊዜም አስተምህሯዊ አለመግባባቶች እንደሚኖሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መረዳት አለባቸው። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር የእውነት ጠባቂዎች አድርጎ የሾማቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎችን እንዴት



በትክክል ማስተናገድ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው። ሐሰተኛ ትምህርቶችን በትክክል ካላረምን፣ «ተኩላዎች» የእግዚአብሔርን በጎች እንዲነጥቁ እየፈቀድን ነው ማለት ነው። ሐሰትን መከላከል መሪዎች ሊያከናውኑት የሚገባው የአመራር አካል ነው።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በአነስተኛ አስተምህሯዊ ጉዳዮች ላይ ይጣላሉ። የተለያዩ አማኞችና ቤተ እምነቶች በአንዳንድ አስተምህሮዎች ላይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን አሳብ ለመረዳት ይቸገራሉ። አማኞች በእነዚህ ትናንሽ አስተ ምህሯዊ ጉዳዮች ላይ በመለያየት ከቤተ ክርስቲያናቸው ተለይተው አዳዲስ ቤተ እምነቶችን ይመሠርታሉ። አብዛኞቹ ታሪካዊ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት (መካነ ኢየሱስ፣ ባፕቲስት፣ ሙሉ ወንጌል) የተጀመሩት በአነስተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተ ምህሮዎች ላይ በተፈጠሩ ልዩነቶች ሳቢያ ነው። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድነት እንዲኖር ለማድረግ የዚህ ዓይነቱን ልዩነት እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ማወቅ አለባቸው።

27ኛ ጥያቄ:- ሀ) ዛሬ በየቤተ ክርስቲያኑ እየተስፋፉ አማኞችን የሚያታልሉ ሐሰተኛ አስተምህሮዎች ምን ምንድን ናቸው? ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ራሳቸውንና ምእመናንን ከእነዚህ ሐሰተኛ አስተምህሮ ዎች ለመጠበቅ ምን እያደረጉ ናቸው? ሐ) አማኞች ወይም ቤተ እምነቶች የሚለያዩበትን አነስተኛ አስተምህሮ ግለጽ።

1. አስተምህሯዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በታሪክ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ከሚከተሉት ሦስት የተሳሳቱ አቋሞች አንዱን ስትይዝ ኖራለች።

<u>አንደኛ</u>፣ አማኞች ስለአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጡት አተረጓጎም እርግጠኛ የሚሆኑባቸው ጊዜያት አሉ። ከዚያ በኋላ የእነርሱን አቋም የሚቃረኑትን ሁሉ አጥብቀው ይከላከላሉ። ራሳቸውን «የእውነት ጠባቂዎች» አድርገው በመመልከት፣ እውነት የማይመስለውን ማንኛውንም ነገር በኃይል ይቃወማሉ። አንዳንድ ጊዜ እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች የሚወሰዱት በአነስተኛ ጉዳዮች ላይ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ስለ አልኮ